# ፊቴን እሹት ባልህ ጊዜ

በቀለ ብርሃኑ (ዶ/ር)

**2020**

**Copyright © 2020 – Bekele Berehanu**

**All right reserved**

Printed In the United States of America

ካለደራሲው ፍቃድ መጽሐፉን በከፊልም ኾነ በሙሉ ማባዛትና ማሰራጨት አይፈቀድም።

ስለ መጽሐፉ ያላችሁን አስተያየት በ E-mail: beke_abay@yahoo.com ላይ ማድረስ ይቻላል።

For Text message: 2403305004

Title – ፊቴን እሹት ባልህ ጊዜ
Author – Bekele Berehanu (Dr)

**Calvary Publishing**

Parker Memorial Baptist Church, c/o Mark Chartier

1902 East Cavanaugh Road

Lansing, Michigan 48910

Bekele Berehanu ©2020

በቀለ ብርሃኑ (ዶ/ር)
12826 Cloverleaf Center Dr,
Germantown, MD, 20874

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ዕውን ይሆን ዘንድ፣ ጸጋውንና ምሕረቱን ላበዛልኝ እግዚአብሔር ከፍ ያለ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።መጽሐፉን በማዘጋጀት ላይ ሳለሁ፣ ሐሳቦችንና መረዳቶችን ወደ ልቤ ባያመጣ ኖሮ፣ ከመጀመሪያውም መጽሐፉ አይታሰብም ነበር። ስለዚህ ድንቅ ስለ ሆነው ምሪቱ እና ስለ ዋና ደራሲነቱ ከልብ አመሰግነዋለሁ።

በመቀጠል የማመሰግነው ባለቤቴንና ልጆቼን ነው። በዚህ በአገረ አሜሪካ ካለው የጊዜ ማነስ የተነሣ ሕይወት ትሰምር ዘንድ፣ እያንዳንዱ ነፍስ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ኑሮው ግድ ይለዋል። እንደዚያም ሆኖ እንኳ ኑሮው ፈታኝ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እያለን ነው፣ባለቤቴና ልጆቼ መሥዋዕቶችን በግል በመክፈልና የኔን የቤት የሥራ ድርሻዎች በመውሰድ፣ በቂ ጊዜ አግኝቼ ኮምፒዩተር ላይ ጽሑፎችን እንድከትብ የረዱኝ። ስለዚህ ከፍ ያለ ምሥጋናን አቀርብላቸዋለሁ።

ይኼ መጽሐፍ እውን ይሆን ዘንድ የደገፉኝ ሰዎች ነበሩ። ዶ/ር ክፍሌ አድማሱ በገንዘብ ባይረዳኝ ኖሮ፣ መጽሐፉ ለኅትመት አይበቃም ነበርና እጅግ በጣም አመሰግነዋለሁ። እግዚአብሔር ከማያልቀው በረከቱ አትረፍርፎ ይባርከው። ዶ/ር አዳም መጽሐፉ መጽሐፍ ይመስል ዘንድ የፎርማቲግና ዲዛይን ሥራ ሠርቶልኛልና እጅግ በጣም አመሰግነዋለሁ። እግዚአብሔር ይህንን ጸጋ ይጨምርለት፣ ያስፋለትም። ፓስተር ቢኒያም በመጽሐፉ ውስጥ ያያቸውን ግድፈቶች እንዲስተካከሉና የተሻለ እንዲሆን እንደ ወንድም ከአጠገቤ በመሆን አግዞኛል፣ አበረታቶኛልም። እግዚአብሔር እሱንም በማያልቀው ጸጋው በአገልግሎቱ ሁሉ

እንዲያሰፋውና እንዲያበረታው ምኞቴና ጸሎቴ ነው።

በመጨረሻም ለመንፈሳዊ አገልግሎቴ ለሚጸልዩልኝና በተለያየ መንገድ ለሚረዱኝ ሁሉ የከበረ ምሥጋናዬን እንደማቀርብ ይታወቅልኝ። የጌታ ሥም የተባረከ ይሁን!

በቀለ ብርሃኑ (ዶ/ር)

# አበርክቶት

ይህንን መጽሐፍ የጸሎትን ጥቅም ላሳዩኝ፣ እንዴት እንደምጸልይ ላስተማሩኝ፣ በቅርብ ሆነው አብረውኝ በመጸለይ የጸሎትን ዲሲፕሊን ላሳዩኝ፣ እንዲሁም በተለያዩ ችግሮችና ተግዳሮቶች ውስጥ ሳልፍ የእግዚአብሔር አምላክ ጸጋ እንዲበዛልኝ በጸሎት ላገዙኝ ሁሉ ማስታወሻ ይሁን፡፡

# ማውጫ

ጥማቴ........................................................................ 1
መግቢያ ....................................................................... 2
ግለ-ታሪካዊ መንደርደሪያ ዳራ ................................................ 3
ጸሎት የመጸለይ ትግል........................................................ 11
ግሩም ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁ ............................................. 15
የጸጋው ዙፋን ................................................................ 20
እንንቃ፣ እንታጠቅ............................................................ 22
ሰማያዊ ሸክም ................................................................ 26
ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል ............................................... 29
የዕረፍት ምስጢር............................................................. 31
መለኮታዊ ጉብኝት (Holy Encounter) ..................................... 34
ለጌታ ሊኖረን የሚገባ ምላሽ.................................................. 38
ሕዝቤ ሰምቶኝ ቢሆን......................................................... 43
ከልብህ ኀዘንን አርቅ .......................................................... 45
የእግዚአብሔር ጉብኝት ....................................................... 49
በመንፈስ የመጸለይ ጥቅም .................................................... 55
የምጥ (የጣር) ጸሎት (Travailing Prayer)........................... 58
የጸሎት ጥልቀት (ተግባራዊ ርምጃ) ......................................... 61
እግዚአብሔር ይናገራል.......................................................... 66
የምጥ (የጣር) ጸሎት በተግባር ደረጃ ........................................ 71
መዝራት እና ማጨድ .......................................................... 75

እግዚአብሔር ድምፅ ......................................................79
ስለዚህ አንታክትም ......................................................83
የልብ ለውጥ..........................................................90
ድብርት (mild depression) መድኃኒት አለውን?...................94
የተትረፈረፈ ሕይወት ......................................................97
በሕልውናው የመኖር ጥቅም ..............................................102
ውስጥን የሚለውጥ መንፈሳዊ እርምጃ....................................107
የመከራ እሳት እና የእኛ አቀባበል.........................................113
የንስሓ ጥቅሙ .........................................................119
የኃጢአት ሥርና መፍትሔው .................................................125
የምናልፍባቸው ጎዳናዎች ..................................................130
የምሥጋና መጎናጸፊያ .....................................................134
እገሠግሣለሁ ...........................................................137
ጉልበቴን ይያዝ ........................................................139
ለጌታ የመገኘት በረከት...................................................144
መሪውን እንስጠው .......................................................150
የመንፈሳዊ ራብ በረከት ...................................................153
የጸሐፊው ማሳረጊያ .......................................................156
የመዝጊያ ጸሎት........................................................158

# ጥማቴ

ዓይኔን ከፈትና ውበትህን ልየው

የሰገዱለትን አእላፋት ጠልቀው

ውስጤ ተለውጦ ልዕልናህ ገብቶኝ

ልስገድ በግምባሬ ዳር ዳር ማለት ይብቃኝ

ጸጋህን ደርበህ እሳትን ለኩሰህ

አስደንቀኝ ባክህ ወደ ጓዳህ ስበህ

እሱ ነው ናፍቆቴ

እሱ ነው ጥማቴ

ከፍ ባለ ዝማሬ በተዋበ ዜማ

በጠለቀ ጸሎት ልቤ እየተስማማ

ልሰዋ ላንግሥህ

ክብርህን አይቼ በመኖር ላክብርህ!

# መግቢያ

እነዚህ የጥሞና መጣጥፎች ሲዘጋጁ *“ጠብታ ጋን ይሞላል”* እንዲሉ፣ ቀስ በቀስ ነው የተጠራቀሙት። በኋላ ላይ ግን የጽሞና መጽሐፍ (devotional) ሆኖ ቢጠረዝስ የሚለውን ያመለከተኝ ራሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። እኔም የጌታን ምሪት በመታዘዝ፣ መጣጥፎቹን በመጽሐፍ መልክ አስተካክዬ በኮምፒዩተር ላይ አሰፈርኳቸው። በሂደትም እግዚአብሔር ሰዎችን በመንገዱ ላይ ስላዘጋጀልኝ ነው መጽሐፉ እውን ሊሆን የቻለው።

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ሰዎችን ለጸሎት ማነሣሣት፡፡ ታዲያ መጽሐፉ ተነብቦ የሰዎች ጉልበት ለክብር ጌታ ከተንበረከከ፣ መጽሐፉ ግቡን መትቷል ማለት ይቻላል። መጽሐፉ ከዚህ ያነሰ ግብ የለውም፤ በቃ ይኸው ነው ዓላማው።

መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ርዕሶች የተለያዩ ቢሆንም፣ ይዘታቸው እጅግ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ነው። ሰዎችን ለጸሎትና ለቃሉ ይጋብዛሉ። ንስሐን ይጠቁማሉ። እንደ “ሜኑ” ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የእግዚአብሔር ቃል ጥሩ መብል መሆኑን ለተመጋቢዎች ያስገነዝባሉ። የዕረፍት መንገድ የሆነውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳያሉ፣ ያመለክታሉም።

ታዲያ ይህንን መጽሐፍ ለሚያነብቡ ሁሉ አንድ ምክር አለኝ። ይህንን የጽሞና መጽሐፍ ሲያነብቡ፣ እንደ ማንኛውም መጽሐፍ መደዳውን በርከት ያሉ ገጾችን ባያነብቡ ይመከራል። በግሌ እኔ የማቀርበው ሐሳብ

በጸሎትና በጽሞና ጊዜያት አንድ ርዕስ ይዞ ወይም መርጦ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማጣቀስ፣ በማገናዘብና በማስተያየት ቢነበብ ጥሩ ይሆናል ብዬ ነው። አንዱ ርዕስ ተነብቦ ካለቀ በኋላም፣ ርዕሱን መሠረት አድርጎ ጸሎት ቢደረግ መልካም ይሆናል የሚል ምክርን ለመስጠት እወድዳለሁ።

ይህንን የጽሞና መጽሐፍ ጊዜዎን ሰውተው ለማንበብ ፈቃደኛ ስለሆኑ ጌታ ይባርክዎ!

በቀለ ብርሃኑ (ዶ/ር)

# ግለ-ታሪካዊ መንደርደሪያ ዳራ

ለጸሎት ያለኝ ዋጋ እጅግ ከፍ ያለ ነው። በራሴ ሕይወት በጸሎት ብዙ ነገሮች ሲለወጡ አይቻለሁ። በጸሎት የሰዎች ሕይወትም ሲለወጥ አይቼ ደጋግሜ ተደንቄአለሁ። ወደ ጌታ የመጣሁት የዛሬ 22 ዓመት ሲሆን፣ እኔ ወደ እዚህ የከበረ አምላክ እንድመጣ እጅግ በርከት ያሉ የጸለዩ ሰዎች እንደ ነበሩ እርግጠኛ ነኝ። ተግተው የጸለዩልኝ በሚገባ ለይቼ የማውቃቸው ሰዎች አሉ። ጌታ የእነዚህን ወገኖች ሕይወት እንዲባርክ ጸሎቴ ነው።

የወጣሁት ከድቅድቅ ጭለማ ውስጥ ሲሆን፣ ጫት መቃም ብቻ ሳይሆን እበላ ነበር ማለት ይቻላል። ሲጋራ አጨስ ነበር። አልኮል በኃይል እጠጣ ነበር። አልኮል እጠጣ የነበረው አብዛኛውን ጊዜ ጫት በቃምኩ ጊዜ ብቻ ነበር። ለነገሩ አዘውትሬ እቅም ስለ ነበር፣ አዘውትሬ እጠጣ ነበር ማለት ይቻላል። በምጠጣ ጊዜ ደግሞ እራሴን እስክስት ነበር የምጠጣው።

ስለዚህ ኑሮዬ የገሃነም እንጂ የምድር አልነበረም። ከእነዚህ ሱሶች ጋር በተያያዘም የተከሰቱ ብዙ ማኅበራዊ ችግሮች ነበሩ። “ማን ያወጣኛል፣ ማን ይገላግለኛል፣ ከነዚህ ሱሶች ተላቅቄ የሰላም አየር የምተነፍሰው መቼ ነው?” የሚሉ ጥያቄዎች የነፍሴ የረጅም ጊዜ ጥያቄዎች ነበሩ።

በጣም እጅግ በሚዘገንኑ ሁኔታዎች ውስጥ አልፌአለሁ። ያልደረሰብኝ የጭንቀት ዓይነት አልነበረም። እንደ ዳዊት *“በሞትና በእኔ መካከል አንድ እርምጃ ቀርቶ”* (1ሳሙ.20፥3) ነበር። ያንን የበሰበሰና ሊያከትም ምንም ያልቀረውን ሕይወት ነው ጌታ ትንሣኤ የሰጠው። ያንን ያንዣበብኝን የሞት አዋጅ ገልብጦ ነው ጌታ ኢየሱስ ነፍስ የዘራብኝ፤ ብሎም እረፍትና ሰላምን የሰጠኝ። ያንን ሞት ሞት የሸተተ ሕይወት ነው ኢየሱስ በአዲስ መዓዛ የለወጠልኝ።

ከላይ ጠቀስ እንዳደረግሁት፣ የእግዚአብሔር ክንድ ሦስት እላዬ ላይ ተጭነው የነበሩ ቀንበሮችን ነበር ባንዴ በሚገርም ሁኔታ የሠባበራቸው። ሁሌም የሚደንቀኝ ነገር፣ እነዚህ ሱሶች ከላዬ ላይ ሲነሡ ራስ ምታትና ማዛጋት እንኳ የአልነበረኝ መሆኑ ነው። ያገኘሁት ፈውስ ሙሉ ነበር። ከዚህም የተነሣ በጐዳናዎች ስሄድ፣ ከሰዎች ጋር ስገናኝ እና ሥራዬን ስሠራ አዲስ የተቀጠለ ሕይወትና ነጻነት ስለነበር የሚሰማኝ፣ ደስታዬ ወሰን አልነበረውም። ቢሆንም ያንን ጊዜያዊ የደስታ አየር በቀጣይነት እየተነፈሱ ለመቀጠል፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ለማወቅ ምሪት ማግኘት ነበረብኝ። እንዴት መጸለይ እንደሚገባኝም መማር ነበረብኝ።

ወደ ጌታ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቆርጬ ከመጣሁ በኋላ፣ በመጀመሪያዎቹ በርከት ያሉ ወራት፣ ከሱስ በመላቀቄ ደስታና ሰላም ቢኖረኝም፣ ሃይማኖታዊና ታይታዊ ምልልስ ነበር የነበረኝ። ለዘለቄታው

ሊያቆመኝ የሚችል ጠለቅ ያለ ለውጥ ስላልነበረኝ፣ ለረጅም ጊዜ እጅግ ከባድ ፍርሃትና ማመንታት ውስጥ ነበርሁ። በውስጤም ይመላለሱ የነበሩ ጥያቄዎቼ "እንዲሁ እያስመሰልኩ ይሆን? ወደዚያ ድቅድቅ ጭለማ ዳግም እመለስ ይሆን? እንዴት ነው እውነተኛ ውስጣዊ ለውጥ የሚኖረኝ? እንዴት ነው በውስጤ የሚታወቅ ያመለጠ ሰው ጥንካሬ የሚኖረኝ?" የሚሉ ነበሩ።

በዚህ ዓይነት ነውጥ ውስጥ ሳለሁ፣ ስለ ጸሎት ጥሩ አቅጣጫን የሚያስዝ መጽሐፍ እጄ ላይ ወደቀ። ይህ የመጀመሪያው ጌታ ያደረገልኝ መለኮታዊ እርዳታ ነበር። ያነበብኩትም መጽሐፍ ላይ ያገኘሁት መንፈሳዊ መልዕክት፣ *"ይህንን መጽሐፍ የምታነብ ወንድም በጸሎት ሕይወትህ ብዙ ግር የሚልህ ነገር ቢኖርም፣ ተስፋ ሳትቆርጥ ቀጥል። ከተወሰነ የመታገሥና የመጽናት ጊዜ በኋላ፣ ጭለማው እየተገፈፈና መረዳትህ እየጨመረ ስለሚመጣ ብዙ ሳትቆይ አስደናቂ ሕይወት ውስጥ እራስን ታገኘዋለህ።"* የሚል ሲሆን፣ ለእኔ ይህ መልእክት በጊዜው ታላቅ ዕረፍትንና መረጋጋትን የሰጠኝ እና ከውዥንብር ውስጥ በከፊልም ቢሆን ነጻ እንድወጣ የረዳኝ የጊዜው መልዕክት (ምሳ.25፥11) ነበረ።

ጌታ ያደረገልኝ ሁለተኛው መለኮታዊ እርዳታ አስደናቂ ነው። መጸለይ እንዴት እንደምችል በዚያ ውዥንብር ጊዜ ወደ ሕይወቴ የላካቸው ሰዎች ነበሩ። ከእነዚያ የጌታ ባሪያዎችም ጸሎት እንዴት እንደምጸልይ በሚገባ መረዳት ጀመርሁ። ሌላው የጌታ መለኮታዊ ርዳታ፣ በተለያዩ ጊዜያት የመግዛት አቅሙ ባይኖረኝም፣ ለሕይወቴ የሚበጁና በየጊዜው የሚያስፈልጉኝ መልእክቶችን የያዙ መጻሕፍትና የቪዲዮ ትምህርቶች እጄ ላይ በተዓምራዊ መንገድ ሳያሰልስ ማቅረቡ ነበር።

በዚያን ጊዜ በጸሎት ላይ ትኩረት በማድረግ እጅግ ብዙ የጸሎት መጻሕፍትን በማንበቤ ሕይወቴ ወደ ኋላ ላይመለስ ተለውጧል። ከፍ ያለ የማንበብ ጸጋ ስለነበረኝ፣ ታክሲ ውስጥ እንኳ ሳይቀር ብዙ መንፈሳዊ መጻሕፍትን አነብብ ነበር። ከዚያም የተነሣ መጸለይ ከዚያም ማንበብ፣ ማንበብ ከዚያም መጸለይ የማያቋርጥ ተግባሬ ሆነ። ከጌታ በምሕረቱ ያገኘሁት ይህ ግሩም ሕይወትም ይኸው ለሃያ ሁለት ዓመት ቀጥሏል።

በመኖርና ከልምድም እንደ ተረዳሁት፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ብዙ ተግዳሮቶች አሉ። የክርስትና ሕይወት ብዙ ውጣ ውረዶች አሉት። ከእግዚአብሔር ረድኤትን ይፈልጋል፣ ትጋትን ይጠይቃል፣ ጥበብን ይፈልጋል፣ መጠበቅንና ትዕግሥትን ይሻል...ሌላም ሌላም። ከእነዚህ ሁሉ ግን በመሠረታዊነት የጀርባ አጥንት ሆኖ የሚያስፈልገን ጸሎትን ሳያሰልሱ መጸለይ ነው። ጸሎት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ የምንገናኝበት መንገድ ነው።

በጸሎት ብዙ ያስቸገሩንና አናልፋቸውም ያልናቸውን ነገሮች እናልፋለን። ብዙ መንፈሳዊ በረከቶችንም እናገኛለን። ከምናገኛቸው ነገሮች ትልቁና አስደናቂው ነገር እግዚአብሔር አምላካችንን በመንፈስ በሚዳሰስ መልኩ ማወቃችንና ማየታችን ነው (ዮሐ.10፥14-16)። ታዲያ ወደ እዚህ የመረዳትና የማወቅ ደረጃ ከፍ ለማለት የምንከፍላቸው ዋጋዎች አሉ። ከምንከፍላቸው ዋጋዎች ዋናውና ትልቁ ለእዚህ ዲሲፕሊን ጊዜን መስጠት ነው። ይሁን እንጂ፣ ለዚህ ለከበረ ነገር ጊዜን መሥዋዕት ማድረግ ብዙ ተግዳሮቶች እንዳሉት የታወቀ ነው።

ንጉሥ ዳዊት ለእውነተኛ ጸሎት ጊዜ አስፈላጊ እንደ ሆነ በተናገረበት ምንባብ፣ *“ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት፣ እርሱም ዘንበል*

*አለልኝ.....።”* (መዝ.40፥1-3)) በማለት በጌታ ፊት የመቆየትን ጠቃሚነት መስክሯል። አዎ፣ በጌታ ፊት የምናሳልፋቸው ጊዜያት የበረከት እንጂ የባከኑ አይደሉም። በእርሱ ፊት የምንሆንባቸው ጊዜያትን በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው በመንፈሳዊ ሕይወታችን እየተለወጥን እንመጣለን። ቆሻሻውንና አላስፈላጊውን የመጣል ጉልበት እናገኛለን። እየተለየንና እያደግን ስለምንሄድ ብዙ መንፈሳዊ ፍሬዎችን በሕይወታችን እናያለን።

በመጸለይ ብዙ የተማሩት ኢ.ኤም.ባውንድስ የሚባሉ የእግዚአብሔር ሰው *“ጸሎትን የምንማረው በመጸለይ ነው”* ብለው ተናግረዋል። እውነታቸውን ነው። እርግጥ ስለ ጸሎት በማንበብ፣ በመስማት እና በመማር ብዙ ግንዛቤ ሊኖረን ይችላል። ቢሆንም ግን ጸሎትን በልባችን ጽላት ላይ በሚጻፍ መልኩ የምንማረው ወደ ጓዳችን በመግባት ነው። አዘውትረን በመጸለይ ነው። ፊቱን ተግተን በመፈለግ ነው።

ለትውልዳችንና ለምድራችን በረከት ለመሆን ከፈለግን፣ አንዱና ዋነኛው ማድረግ ያለብን ነገር መጸለይ መሆኑን በሚገባ ልብ ማለት ያስፈልገናል። በምድራችን ላይ በጸሎታቸው ታሪክ ሠርተው ያለፉ የጸሎት ሰዎች ብዙ ነበሩ። ቢሾፕ አንድሩ የሚባሉ የእግዚአብሔር ሰው በቀን አምስት ሰዓት በጉልበታቸው ተንበርክከው ይጸልዩ ነበር። የጸሎት ሰው የነበሩት ጆን ዌስሊይ ከቀኑ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ሰዓቶችን በጸሎት ያሳልፉ ነበር። የእሳቸውን ግለ-ታሪክ ያዘጋጅ የነበረው ጓደኛቸው *“ጸሎት ከምንም በላይ ቢዝነሱ እንደ ሆነ ነበር የሚያስበው። ከጸሎት ጓዳው ሲወጣም ፊቱ ያበራ ነበር”* ብሏል። በጸሎት ሕይወታቸው የሚታወቁት ከላይ የጠቀስኳቸው ኢ ኤም ባውንድስ፣ በጸሎት ሕይወታቸው ብዙዎችን ነክተዋል። ግለ-ታሪካቸውን የጻፉ ሰው *“ለአካላችን መኖርና ጤንነት መተንፈስ የግድ*

*እንደ ሆነ፣ መጸለይም ለእሱ እንዲሁ ነበር። ሳታቋርጡ ጸልዩ የሚለውን ቃል እንደ ወረደ ነበር የተገበረው”* ብለው ተናግረዋል።

ጆን ኔልሰን ሃይድ ከፍ ያለ የምልጃ ሕይወት የነበረው፣ ሕንድን በጸሎቱ የለወጠና ብዙ ተፅዕኖ ያስመዘገበ ሰው ነበር። ለረጅም ሰዓታት ለምልጃ በግምባሩ ተደፍቶ የሚያሳልፍ ሰው ነበር። ፕሬዪንግ ሀይድ (praying Hyde) የሚባል ቅጥያ ስም የተሰጠው ለጸሎት ራሱን የለየ ሰው ስለ ነበር ነው። በምልጃዎቹ ከሚያዘወትራቸው ጸሎቶች አንዱ፣ *"ነፍሳትን ስጠኝ ወይም እሞታለሁ/ Give me souls, oh God, or I die!”* እንደ ነበረ በቅርብ የሚያውቁት ይናገራሉ።

ማርቲን ሉተርም የሚገርም የጸሎት ሕይወት የነበረው ሰው ሲሆን፣ *“የጸለየ ሰው በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅቷል ወይም አጥንቷል (He that has prayed well has studied well)”* የሚል ከአንደበቱ የማይጠፋ አባባል ነበረው። ጆን ዌልች የሚባሉ የጸሎት ሰው በርከት ያሉ ሰዓት ወለል ላይ ተዘርግተው ይጸልዩ ነበርና *“ለምን እንዲህ ትሆናለህ፣ ይበቃሃል”* ብላ ባለቤታቸው ታጉረመርም ነበርና *“ምን ነካሽ ሴትዮ የ 3000 ነፍሶች ጥያቄ አለብኝ፣ ጥቂቱን እንኳን የመመለስ ብቃት የለኝም”* ብለዋታል። አዶኒራም ጃድሰን ከቢሮአቸው ሰባት ጊዜ ለጸሎት ይወጡ እንደነበር አንብቤአለሁ።

በመንፈሳዊው ዓለም ተፅዕኖን ያመጡና በፍሬያቸው ያስደመሙና ጌታቸውን ያስከበሩ እጅግ ብዙዎች ቢሆኑም፣ ጸሎትን “ሀ” ብለው እንደ ጀመሩ ግን በፍጹም መካድ የለበትም። አዎ፣ ጸሎት በብዙ ትግል ይጀመራል። ጸሎት ሲጀመርም ዳገትን የመውጣት ዓይነትን ትግል ሊመስል ይችላል። ግራም ሊገባ ይችላል። ያደክማል፣ ቋንቋም ይጠፋል፣ የሚባል ነገር ያልቃል፣ ብቻን እንደ እብድ ማውራትም ሊመስል ይችላል

ወዘተ። አዎ ጅማሬ ሁሉ ከባድ ነው። ተስፋ ሊያስቆርጠን ይችላል። ይህንን የተግዳሮት ጊዜ በተስፋ ታግሠን ብንቀጥል ግን፣ ጸሎታችን ብርሃንን እየፈነጠቀ መሄዱ የማይቀር ነው። ቀስ በቀስ ብዙ ነገሮችን እየተረዳንና እያስተዋልንም እንመጣለን፤ ቅዱስ ቃሉ *"የጻድቃን መንገድ እንደ ንጋት ብርሃን ነው፤ ሙሉ ቀን እስኪሆን እየተጨመረ ይበራል"* (ምሳ.4፥18) ይላልና!

የጸሎት ሕይወታችን ስኬታማና ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ፣ ራስን ለመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ መስጠትን ይፈልጋል። በእራሳችን ምንም ማድረግ እንደማንችል ማወቅንና መረዳትን ይጠይቃል። ሙሉ በሙሉ የእርሱ ጥገኞችና ረድኤቱን ፈላጊዎች መሆናችንንም ልናምን ይገባል። ይህ አመለካከትና አተያይ ለጸሎታችን እጅግ ወሳኝ ነው። *"በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።"* (ማቴ.5፥3) የተባልነውም ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሠጣል" (ያዕ.4፥6) ተብሎም ተጽፏል።

በአግባቡ ከተጠቀሙበት ጸሎት ሕይወትን ያስተካክላል፣ ኑሮን ያስውባል፣ ነፍስን ያረጋጋል፣ ያስተከዙንንና አንገት ያስደፉንን ነገሮችም ይለውጣል። ከሁሉ የጸሎት መልሶች ይልቅ የነገሮች ሁሉ ደራሲ የሆነውን እግዚአብሔርን መንፈሳዊ ዓይኖቻችን እንዲያዩት ያደርጋል። ይህንን ሳስብ፣ ጸሎት በሚገባ መታወቅ ያለበት የምድራችን ዕንቁ ነው ብዬ እላለሁ።

አንድ በዚህ አገረ አሜሪካ ፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚማር ተማሪ *"በምድራችን ኦሪጂናል የሆነ ገና ያልተሠራ ምን ዓይነት የጥናት ዓይነት ቀርቷል?"* ብሎ አልበርት አንስታይንን ጠይቆ ነበር ይባላል።

አልበርት አንስታይንም ሲመልስለት *"ስለ ጸሎት ብዙ መታወቅ ስላለበት ዋጋ ከፈሉና እሱን ለማወቅ ቆፍሩ"* ብሎ መልሶለታል አሉ። ትክክል ነው። ስለ ጸሎት ነው ብዙ መታወቅ ያለበት። በብዙዎች ዘንድ የጠፋው ድሪም እሱ ነውና (ሉቃ.15፥8-9)። ሊፈለግ እና ሊታወቅ የሚገባው! ዋናውን ትተን ወደ የት?

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*"ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና። መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ። የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።"* (1ተሰ.5፥17-24)

## አይ ብታገኘው

እንቊውን ፈልገህ ብታገኘው

ተግተህ ቆፍረህ ብታወጣው

ድሪሙ ተፈልቅቆ ቢገባህ

የሕይወትን ማገር ቁልፉ.....

ውስጥህ በርቶ ቢታይህ

ቢለወጥ ልብህ መንፈስህ

ደግሞም ከማር ወለላው ብትበላ

ነፍስህ በጥበቡ ብትሞላ

መልካም ይሆን ነበር ፍጻሜህ

አይጠፋም ነበረ ተስፋህ!

—

*"ልጄ ሆይ መልካም ነውና ማር ብላ፣ ወለላም ለጣምህ ጣፋጭ ነው። ጥበብም ለነፍስህ እንዲሁ እንደሚሆን እወቅ፤ ብታገኘውም ፍጻሜህ መልካም ይሆናል፣ ተስፋህም አይጠፋም።"* (ምሳ.24፥13-14)

# ጸሎት የመጸለይ ትግል

*ጸሎት ጥያቄ ማቅረብ ብቻ አይደለም። ጸሎት እራስን በእግዚአብሔር ፊት በመጣል በውስጡ ሰውነታችን ድምፁን መስማት ነው። ማዘር ተሬዛ*

የእግዚአብሔር ኃይል ድንቅ ነው። ይህንን ኃይል የምንስበው ደግሞ ከቃሉ ጋር ባለን ቁርኝትና ጸሎት መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ነገር ግን እውነተኛ የሆነ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ጸሎት መጸለይ እንደ ቀላል መታየት የለበትም፤ ትግል አለውና። አንደኛው ተግዳሮት የጨለማው ጥላ በጸሎት ላይ ያለ የሌለ ኃይሉን ማሳረፉ ነው ብዬ አስባለሁ።

በተለይ በዚህ በምዕራቡ ዓለም ካለው የሥራ ጫናና ባተሌነት የተነሣ፣ ጉልበትን ለጸሎት ማጠፍ እጅግ ከባድ ነው። ከዚህም የተነሣ

አንዳንዴ የጭለማው ዓለም ተጽዕኖ በሕይወታችን ላይ በግልጽ ይታያል። ከሚታወቁት ተጽዕኖዎች አንዱ ነፍሳችንን ማዋከቡና መረጋጋትና ሰላም እንዳይኖረን ማድረጉ ነው። ታዲያ ከዚህ ወከባ ለመዳን የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ጨክኖ በእርሱ ፊት መሆንን ግድ ይለናል–መሰናክሎችን ተቋቁሞ! ጌታ በምሕረቱ የዕረፍት ጊዜዎችን ሲያመቻችልን ደግሞ፣ ሳይሰስቱ ለጸሎት መጠቀሙ አስተዋይነት እላለሁ።

ሰይጣን ምንጩን በማናውቀው ምክንያት በኀዘንና በድብርት ሊመታን ይችላል። እርካታ የለሽና ቅብጥብጥ ሊያደርገንም ይችላል። ከአፋችንም የምስጋና ቋንቋ በማራቅ ነፍሳችን ከማትወጣበት ወኀኒ ሊያኖራት ይችላል። ለዚህ ነው በተለያዩ ነገሮች ሊውጠን ያሰፈሰፈ ባላጋራ በየደጃችን እንደሚገኝ መገንዘቡ አስተዋይነት የሚሆነው። ለዚህም ነው *"በመጠን ኑሩ ንቁም"* (1ጴጥ.5፥8) የተባልነው። *"አንተ የምትተኛ ንቃ፣ ክርስቶስም ያበራልሃል"* (ኤፌ.5፥14) ተብለንም ተመክረናል።

ለመጸለይ ስናስብ የማይመጣ የአዚም ዓይነት የለም። ስልኩ ይንጫጫል፤ ሰውነታችንን እንቅልፍ እንቅልፍ ይለዋል፤ ጆሮአችን ወሬ ያምረዋል፤ ሌሎች የሚሠሩ ነገሮች ትዝ ይሉናል፤ ሌላም ሌላም። እኒህን ተግዳሮቶች አሽቀንጥረን ነው ለጸሎት በጌታ ፊት የምንወድቀው። ቢሆንም ተግዳሮቱ ጸሎት ጀምረንም አያባራም፤ እየጠነከረ ይቀጥላል። እንዳውም ከምንጸልይበት ሳያስነሣን አያርፍም። ስለዚህ ሲያስፈልግ በኃይል በእምነት እየተቃወሙ የጠላትን ሥራ ማፍረስ ጥሩ ነው ብዬ እመክራለሁ፤ በተደጋጋሚ ጠቅሞኝ አይቻለሁና።

በጸሎት ውስጥ ሳለን መንፈሳችን እንዲዋልልና እንዲባክን የሚያደርጉ የጠላት ሥራዎችና ደባዎች ስለማይጠፉ በመንፈስ እያስተዋልን

በጸሎት መጽናቱ ጥሩ ነው። ከልምዴም እንዳየሁት፣ ጠላት እንዳንጸልይ በአዚም፣ በስንፍና፣ በማሰላቸት፣ ባተሌ በማድረግ፣ ግርግር በማብዛት፣ ስልኮቻችንን ከወትሮው ጥሪ እንዲኖሩት በማድረግ ወዘተ ይዋጋናል። እኔ አንዳንዴ በርከት ላሉ ጊዜያት የኢየሱስን ስም ደጋግሜ ጮክ እያልኩ የምጠራበት ጊዜ አለ። ስሙ ከስሞች ሁሉ በላይ ነውና፣ ለጠላቶቻችንም እሳት ነውና ጸሎቴ በአዎንታዊ መልኩ ሲለወጥ ደጋግሜ አይቻለሁ።

አእምሮአችንን መሰብሰብና ጸሎት ላይ ትኩረት ማድረግ ሲያቅተው፣ የጸሎት መዝሙሮችን መክፈት ጥሩ ነው። እኔ አዘውትሬ የጸሎት መዝሙሮች ወደ ጸሎት ሲወስዱኝና ሲረዱኝ አይቻለሁ። መንፈስን የሚያረጋጉ የጸሎት መዝሙሮችን ከፍቶ በጌታ ፊት መሆን ጥሩ ነው ብዬም እመክራለሁ። ቀስ እያልንም ጠንከር ያለ ጸሎት ውስጥ ስንገባ መዝሙሩን ማጥፋት እንችላለን። ሌላው አእምሮአችን ለጸሎት እንዲሰባሰብ የሚያደርገው፣ በመኻል በመኻል የእግዚአብሔርን ቃል ማሰላሰልና የእግዚአብሔርን ቃል ራሱን ደጋግሞ መጸለይ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ማሰላሰል ለምንጸልይባቸው ነገሮች እምነታችን ይጨምረዋል። በተጨማሪ እንዴት እንደምንጸልይ አቅጣጫን ያሳየናል። ደግሞም የበለጠ እንድንጸልይ መንፈሳችንን ያነቃቃዋልና ነው።

ይህንን ጽሑፍ ላዘጋጅ እየተንደረደርሁ ሳለሁ፣ ባልተሳኩልኝና ባልሆኑልኝ ነገሮች ኀዘንና ድብርት ተጫጭኖኝ ከአልጋዬ ላይ መነሣት አቅቶኝ የነበርሁበት አስገራሚ ክስተት ውጊያው እንዴት ከባድ እንደ ሆነ ግሩም ምሳሌ ሊሆነን ይችላል።

በዚያ ከባድ መንፈስ ውስጥ እያለሁ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ቃል ወደ መንፈሴ አመጣና አነበብኩት። ያነበብሁት ክፍል *“የሚቀጠቅጥ*

*በአንተ ላይ ወጥቶአል፤ ምሽግን ጠብቅ፥ መንገድንም ሰልል፤ ወገብህን አጽና፥ ኃይልህንም እጅግ አበርታ።"* (ናሆ.2፥1) የሚለውን ነው። ደስ የሚለው ነገር፣ የጊዜው መልእክት ነበር።

አዎ፣ እጅግ ገራሚ የሆነ የሰዓቱ የመንፈስ ቅዱስ መልእክት ነበር። ለመጣልኝ መልእክትም ጌታን አመስግኜ፣ በመኻል በመኻል በኃይል በእምነት እየተቃወምኩኝ ቢያንስ ለሁለት ሰዓት ጸለይኩ። ከዚያም የሆነ የአዚም ጉም ከላዬ ላይ ሲነሣ ታወቀኝ። መለቀቅና መፈታት ተሰማኝ። የምስጋና ዝማሬም ከአፌ መውጣት ጀመረና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እጅግ አስደነቀኝ። ያ የነበርሁበት ድባብ ተለውጦ ውስጤ በኃይል መታደሱን ሁሌም ባሰብኩት ቁጥር ዛሬም ድረስ ለጸሎት ትልቅ መነቃቃት ይፈጥርልኛል፡፡

ዋናው መልእክቴም ይኼ ነው። ቃሉ *"እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ"* (ዕብ.4፥16) ይላልና፣ በራሳችን መታገሉን ትተን፣ የተትረፈረፈ ዕረፍትና ሰላምን በሚሰጠው አምላክ ፊት እራሳችንን ሳናቅማማ እንጣል!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*"መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።"* (ሮሜ.8፥26-27)

# ግሩም ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁ

*"በምድር ላይ ሊረካ የማይችል መሻት ካለን፣ ለዚያ ትክክለኛ ገለጻው፣ ለሌላ ዓለም መፈጠራችን ነው ሊሆን የሚችለው።/ If we find ourselves with a desire that nothing in this world can satisfy, the most probable explanation is that we were made for another world."– ሲ.ኤስ ሌዊስ*

"ሳይንስና እምነት አብረው አይሄዱም፣ አይስማሙም" ተብሎ ሲነገር እሰማለሁ። እኔ ግን ሳይንስና እምነት ይደጋገፋሉ ብዬ ነው የማምነው። ዕውቁ ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን፣ *"Science without religion is lame, religion without science is blind"/ "ሳይንስ ያለ እምነት አንካሳ ነው፤ እምነት ያለ ሳይንስ እውር ነው።"* ብሏል፤ ሳይንስና እምነት አብረው እንደሚሄዱና እንደሚደጋገፉ ለማሳየት! ይህንን ሐሳብ በሚገባ እጋራዋለሁ። ሳይንስ የእግዚአብሔርን *ሥራ* ጎልቶ እንዲታይ ያደርጋል የሚልም ዕይታ አለኝ።

የሕክምና ባለሙያ ስለሆንሁ ስለ ሰው አፈጣጠር፣ የአካል ቅንብርና አሠራሮችን ለማጥናት ዕድለኛ ሆኛለሁ። በእነዚያ አጋጣሚዎች የሰው ልጅ እጅግ ከፍ ባለ ጥበብ እንደተፈጠረ ለመገንዘብ ችያለሁ። ከአእምሮ በላይ የሆነ እውቀት እንደሠራውና እንዳበጀው ምንም ጥርጥርም የለኝ።

ዘወትርም የሰውን አካላዊ ቅንጅትና አሠራር ሳስብ፣ እግዚአብሔርን በነገሮቹ ውስጥ ስለማይ በምስጋናና በግርምት እሞላለሁ። እጅግ የሚገርመው እያንዳንዱ በየቦታው የተሰካካው የአካል ክፍል በዓላማ የተሰካና ከሌላው *ጋራ* በሕብር ተስማምቶ የሚሠራው *ሥራ* መኖሩ ነው። እነዚህን የላቁ አካላዊ ቅንብሮችና ቅንጅቶች ማሰላሰሌም ለእምነቴ

መጠንከርና መነቃቃት ግሩም ምክንያት ሆኖኛል። ብዙ ጊዜም ምስጋና ፈንቅሎኝ፣ "ተመስገን የጥበብ ሁሉ አምላክ ተባረክ" እላለሁ። እስቲ የእጁን ሥራዎች በተናጠል ለአብነት ልዳስስ።

የልብ ያለ ማቋረጥ መምታቱ፣ ደም ከአንዱ የልብ ክፍል ወደ ሌላው ሂደቱን በጠበቀ መልኩ መፍሰሱ፣ እያንዳንዱ የልብ ክፍል ክዳኖች በራሳቸው ጊዜ መከፈት መዘጋታቸው፣ እናም ልብ ያለ ማቋረጥ እየሠራ አለ መድከሙ እጅግ ይገርመኛል።

አንድ ሳይንቲስ "ኩላሊት እጅግ በጣም የረቀቀ የኬሚካል እንደስትሪ ነው" ብለው ተናግረዋል። በሰውነታችን ውስጥ ባለው ሂደት ደም ውስጥ ያለው አብዛኛው ንጥረ ነገር ቆሻሻን ጨምሮ፣ መጨረሻ ላይ የሚያልፈው በኩላሊት በኩል ነው። ኩላሊት ደግሞ ለሰውነት የሚጠቅምና የማይጠቅመውን ለይቶ፣ የማይጠቅመውን ብቻ ያስወግዳል። ሰውነታችንን የሚጠቅሙ ንጥረ ነገሮችና ኬሚካሎች፣ ወደ ደም ተመልሰው ሰውነታችንን ያገለግላሉ።

ሌላ እጅግ የሚገርመኝ ነገር፣ አእምሮአችን እንዲሠራ የተከሸነበት ጥበብ ነው። አንድ ሰው ስለ አንድ ጉዳይ ጠይቆን ለጊዜው ማስታወስ ባንችልም፣ ከተጠየቅንበት ሰዓት ጀምሮ አእምሮአችን ያንን ጉዳይ ሊያስታውሰን በመፈለግ ይባትላል። ከዚያም ያ ለማስታወስ የተቸገርነው ነገር ከሰዓታት ወይም ከቀናት በኋላ ትዝ ይለናል። እንዴት ትዝ ሊለን ቻለ? አእምሮ ከድብቅ ማኅደሩ (subconscious files) ሲፈልግ ከርሟላ!

ሴት ልጅ ዘጠኝ ወር ማርገዟን እናውቃለን። የሚደንቀው ነገር የሚከተለው ነው። ሳይንቲስቶች ሴትየዋ ልክ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ፣

ምጧ የሚጀመርበትን ዋና መንሥኤ እስከ አሁን በቅጡ ሊያውቁት አልቻሉም። እንደ ቀጠሩት ሰው፣ ሰዓቱን ጠብቆ ከች ማለቱ እጅግ ገራሚ ነው።

የምጥ አጀማመር ቅንብሩ፣ እየጨመረ የሚሄደው የማህፀን አከፋፈት፣ ማህፀን ከላይ ልጁን እየገፋ ጸንሱ እስኪወጣ ድረስ አለ ማቋረጡ ይገርማል። ማህፀን ጽንሱን ካስወጣ በኋላ ወደ ቀድሞ ቦታው፣ ቅርጹና መጠኑ መመለሱ ሌላው ገራሚ ነገር ነው። ጽንሱ በማህፀን ሳለ የአመጋገብ ሥርዓቱ፣ በተመቸ ከባቢ ሳይጨናነቅ ተመችቶት በውኃ ላይ እየተንሳፈፈ ማደጉም እጅግ አስደናቂ ጥበብ ነው።

በሰውነታችን ላይ የምግብ የማንሸራሸር ስርዓት ይገርመኛል። ሰው በአፉ ጐርሶ ማኘክ የጀመረውን ምግብ መድቀቅ የሚጀመረው እዚያው አፉ ውስጥ ነው። በተለያዩ ተፈጥሮአዊ ኬሚካሎች (ኢንዛይሞች) መሰባበርና መላም ቢጀምርም፣ ብዙ ርቀት እየላመ ይጓዛል። ጨጓራ ውስጥ አሲድ ባለው ከባቢ በማለፍ የበለጠ እየላመና እየተጨመቀ ይሄዳል። በትንሹ አንጀትም ውስጥ እንዲሁ። ብዙ በኬሚካላዊ ሂደቶች ውስጥ አልፎ፣ እጅግ የላሙ፣ ለሰውነታችን የሚጠቅሙ ነገሮች ሁሉ፣ አንድም ሳይቀሩ ወደ ደማችንን ይገባሉ። የማይጠቅመው ነገር በትልቁ አንጀታችን በኩል አልፎ ወደ ውጭ ይወጣል። አይደንቅም?!

ሳይንቲቶች የአእምሮአችንን ውስብስብ ተፈጠሮአዊ አሠራር፣ ገና በሚገባ እንዳልተገነዘቡት በተለያዩ ጽሑፋቸው ላይ ይናገራሉ። ባንዴ በጣም ውስብስብ ሥራን ከሚሠሩ ብዙ ኮምፒዩተሮች የበለጠ ልቀት አለው። ከልጅነት እስከ ሽምግልና ያሉ ያወቅናቸውንና ያየናቸውን ክስቶቶች፣ ታሪኮችን፣ ቃሎች ወዘተ ማስታወስ ይችላል። በአንዴ በርከት ያሉ

ሥራዎችን የመሥራት ብቃት አለው። እጆቻችን፣ እግሮቻችን፣ ዓይኖቻችንንና ጭንቅላታችን በሕብር እንዲንቀሳቀሱ ይመራል፣ ያቀናጃልም። እስቲ አስቡት አንድ መኪና የሚነዳ ሰው፣ በውጭ ያሉ የሌሎች መኪናዎችን እንቅስቃሴ እያየ አነዳዱን ይቆጣጠራል። በእግሩ ደግሞ የነዳጅ መስጫና ፍሬኑን በእግሩ ይቆጣጠራል። እግረ መንገዱን ሙዚቃ ወይም ዜና ከፍቶ እያዳመጠ ይሄዳል። እጆቹ መሪ ይዘው የመኪናውን አቅጣጫ ይቆጣጠራሉ። ይህንን ሁሉ በሕብር የሚያቀናጀው አእምሮ ነው። ባንዴ ከስድስት በላይ ሥራዎችን። ይገርማል!

ይህ ሁሉ የጠቀስሁት የጥበብ ሥራ ከላይ ፈጣሪና አቀናባሪ እንዳለ ይናገራል። እንዲሁም ከፍ ያለ እጅና ጥበብ እንዳለ በሚገባ ይመሰክራል። ለዚህ ነው ዳዊት ይህንን በመንፈስ አስተውሎ *"አቤቱ፣ አንተ ኵላሊቴን ፈጥረሃልና፣ በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛል። ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ድንቅ ነው፣ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች። እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፣ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም። ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ፤ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።"* (መዝ.139፥13-16) ብሎ የተናገረው።

*"ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁ"* ሲል ከላይ የጠቃቀስኳቸውን የሰው ልጅ ውስብስብ ተፈጥሮአዊ አሠራሮችን በመንፈሱ ተረድቶ እንደ ሆነ እገምታለሁ። *"ነፍሴም ታውቀዋለች"* ብሎ ሲናገር፣ ውስጣዊ መረዳት እንደሚያስፈልገን መጠቆሙ ነው። እርግጥ ነው፣ ይህንን ለመረዳት እውቀት (revelation knowledge) ይፈልጋል። የዓይን ብርሃን ያስፈልጋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር ጥበብ እጅግ አስደንቆት፣ የጀመረውን መልዕክቱን አቋርጦ ትልቅ ውዳሴን አቅርቧል፡-*“የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም። የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።”* (ሮሜ.11፥33-36) ብሎ!

እግዚአብሔር ረድቶትና ዓይኑ ተከፍቶ ላስተዋለ፣ የእግዚአብሔር የጥበብ *ሥራ* እጅግ አስገራሚ ነው። አንድ ሽማግሌ እንዳሉት “ልበ ብርሃን” መሆን ነው የሚያስፈልገው። አዎ፣ የልቡና ዓይኑ የበራለት ሰው፣ እነዚህን የጥበብ *ሥራዎች* ዐይቶ ተገቢው የሆነውን ክብር ለአምላኩ ይሠጣል። የምስጋና ሰው ይሆናል። ሕይወቱ በአድናቆትና በመገረም ይሞላል። ይህንን የጥበብ ጌታም ለማወቅ ከፍ ያለ ራብ ያድርበታል። እናም ጌታውን በሚገባ እስኪያውቅና ነፍሱ በእውቀት እስትጥለቀለቅ ድረስ አይተኛም!

ጌታ ሆይ እንድናውቅህ እርዳን!!

**መዝጊያ ምንባብ፡-**

*“ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል። ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፥ ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች። ነገር የለም መናገርም የለም፥ ድምፃቸውም አይሰማም። ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፥ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።”* (መዝ.19፥1-4)

# የጸጋው ዙፋን

*“እጅግ ብዙ የምሠራቸው አሉኝና ከቀኑ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ሰዓታት በጸሎት ማሳለፍ ይገባኛል።/ I have so much to do that I shall spend the first three hours in prayer.” —ማርቲን ሉተር*

የጸጋው ዙፋን የምሕረት መቀበያ ቦታ፣ የመታደሺያ እና የፈውስ ስፍራ ነው። ታዲያ ይህንን ቦታ ልዩ የሚያደርገው የእግዚአብሔር ሕልውና መገኘቱ ነው።

በዚህ ዘመን ሰይጣንና አጋንንቱ ሌሎች ተግባሮችን ስናከናውን ምንም ግድ አይሰጣቸውም። ለመጸለይ ስናስብ ግን አዚማቸውንና ጦርነታቸውን ይለቅቃሉ። ደፍረን ለጸሎት ስንበረከክ ደግሞ ስልቹ ሆነን እንድናቋርጥ፣ እንድንታክት፣ እንቅልፍ እንዲጫጫነን እናም ቶሎ ጸሎቱን ጨርሰን ወደ ሌላ ጉዳይ እንድንሄድ የማያደርጉት ነገር የለም። የጸሎትን ጥቅም ማሳነስም ትልቁ መዋጊያ መሣሪያቸው ነው።

በግል ሕይወቴና ጥሩ የጸሎት ልምድ ካላቸው ሰዎች እንደታዘብኩት፣ ጸሎት እጅግ ብዙ ጥቅም አለው። ከሁሉም ሊተኮርበት የሚገባው ጥቅም ግን ውስጣችን መለወጡ ነው። ውስጣችን ዕለት ዕለት መታደሱ ነው (2ቆሮ.4፥16)። ልባችን በደስታና በሰላም መረጋጋቱ ነው። ልባችን በመንፈስ ፍሬዎች መሞላቱ ነው። መንፈሳችን መጠንከሩ ነው።

እንዳንጸልይ የማይመጣ የጠላት ተፅዕኖ የለም። ነገር ግን እነዚህን ተግዳሮቶች ሁሉ ተቋቁመን ብንጸናና፣ በጸሎት በጸጋው ዙፋን ፊት በቂ

ጊዜን ብናሳልፍ፣ ሕይወታችን እንደ እርሱ ፈቃድ ይለወጣል። ቃሉ *"ታምነን በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስም"* (2ቆሮ.5፥6) እንደሚል፣ ሁኔታዎችን ሳንመለከት በእምነት በፊቱ ብንሆን ሕይወታችን ይለመልማል። አቅም ባጣንባቸውም ነገሮች ላይ ጉልበት እናገኛለን።

ጌታ አምላክ *"ዕረፉ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ"* (መዝ.46፥10) ብሎ ተናግሯል። ቃሉ *"ዕረፉ"* ሲል እሱን ታምነን፣ በፊቱ እየጸለይን፣ ቃሉን እየተመገብንና በእግሩ ስር ሆነን እሱን እየጠበቅን መሆኑን ልብ ይሏል። ነቢዩ በእግዚአብሔር ፊት ሰከን ያለ ጊዜ ወስዶ *"ዕርፍ"* ማለት ያለውን ጥቅም ሲናገር፣ *"በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ፤ በጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንላችኋል።"* (ኢሳ.30፥15) ብሏል። በሌላ ቦታም *"እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ኃይላቸውን ያድሳሉ"* (ኢሳ.40፥31) የሚል የተስፋ ቃል አለልን። ስለዚህ ዓይነት ዕረፍት ጌታ ኢየሱስ ሲናገር፣ *"ማርያም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርሷም አይወሰድባትም"* (ሉቃ.10፥42) ብሎ ነግሮናል። አዎ፣ በሚገባ ከተዘወተረ የማይወሰድ ዕድል!

በግሌ እንዳልጸልይ ተግዳሮት ሲበዛብኝና ጊዜዬ ሲባክን እጅግ በጣም አዝናለሁ። ለተወሰኑ ቀናት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አሳልፌ፣ ተግዳሮቶቹን ሁሉ ጥሼ በመንበርከክ፣ የመለቀቅና የመፈታት መንፈስ ሳይታወቀኝና በቂ ሕክምና ሳላገኝ አልነሣም ብዬ እወስናለሁ። ጸሎት መሰጠትንና ውሳኔን ይፈልጋልና፣ ሁሉን እርግፍ አድርጌ ትቼ በፊቱ እሆናለሁ። እናም እንዲህ ዓይነቱ የውሳኔ ጸሎት እጅግ ብዙ የተደረገ ነው ባይባልም፣ የተደረገው ግን በማልረሳው መልኩ ባርኮኛል። ያ ዓይነቱም የውሳኔ ጸሎት ዘወትር ሳይቋረጥ ቢቀጥል ሕይወቴ እንዴት

እንደሚለወጥና እንደሚያድግ በማሰብ አምላኬን በእንደዚህ ዓይነት ጊዜዎች እንዲባርከኝ ነው የዘወትር ተማጽኖዬ።

የምር የሆነ ጸሎት (authentic prayer) ከምር የሆነ የጽድቅ ራብንና ጉጉትን ይፈልጋል። ለዚህ ነው ቃሉ *“ጽድቅን የሚጠሙና የሚራቡ ብፁዓን ናቸው፣ ይጠግባሉና።”* (ማቴ5፥6) የሚለው። ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ራብና ጥማት እያየለ ሲሄድ፣ ሌላውን ረብ የሌለውን ራብና ጥማት ይውጠዋል። ወደ ጸጋው ዙፋን በቀረብን ቁጥር፣ የበለጠ እየተሳብን፣ የጸሎት ጸጋ በሕይወታችን እየጨመረና፣ አስደናቂ ኡደት (positive cycle) ውስጥ ጠልቀን እየገባን እንሄዳለን። ሆኖም ግን በመቅረብ ነው የሚጀምረው!

*“እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን **<u>በእምነት እንቅረብ!</u>”*** (ዕብ.4፥16፤ አጽንኦት የእኔ)

**መዝጊያ ምንባብ፡-***“እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት።”* (ዕብ.5፥7)

# እንንቃ፣ እንታጠቅ

*“ጸሎት ብዙ ችግሮችን ያስወግዳል፤ ብዙ ስቃዮችን ያስወግዳል፤ ብዙ መተላለፎችን ይከላከላል፤ እናም በሌላ በምንም መንገድ የማይገኝን ታላቅ*

*ሰላም እና ርካታ ያጎናጽፈናል።” —ቶማስ ሞንሰን*

ስለዚህ ዘመን ክርስትና የምር የምሩን እንነጋገር ከተባለ፣ ቢያመንም በውስጤ የማምንበትን ልበላችሁ። በአሁኑ ወቅት ጠላት ሸርሽሮን፣ ጉልበታችን በእንግዶች ተበልቶ እየተንገዳገድን ነው ያለነው። አፋችን ያወራል። ዝማሬ ሞልቷል። ጥቅስ መጥቀስ እንደ ልብ ነው። የሚዳሰስ ክርስትና ግን በብዙዎች ዘንድ አይታይም። ሕይወታችን በቃሉ ብርሃን ሲታይ እጅግ ብዙ የቤት ሥራ ይጠበቅብናል። ይህንን ፀሐይ የሞቀ ሃቅ መቀበልና፣ ምን እናድርግ የሚለው ላይ ትኩረት ማድረጉ አስተዋይነት ነው እላለሁ። አለበለዚያ ግን አስመሳይነቱ ይቀጥላል፤ ጉዳታችንም ሌሎች ጉዳቶችን እየወለደ ነው የሚሄደው።

የእግዚአብሔር ቃል ባላጋራ እንዳለን ደጋግሞ ያስጠነቅቀናል። እንዳውም “ሊውጠን” እንደሚፈልግ ተፅፏል፤ *“ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጐ እንደሚያገሣ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራል። በመጠን ኑሩ ንቁም፡ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።”* (1ጴጥ.5፥8-9) !!

ለረጅም ጊዜ ትኩረቴን እየሳበው ያለው “ይዞራል” የሚለው ቃል ነው። እውነት የሚገርም ነው እኮ! እርግጥ ነው፤ ባላጋራችን እረፍት የለውም ይዞራል። ትጉሕ ነው፤ የሚጥለውን ሰው እስኪያገኝ ድረስ አይተኛም። አንዴ ከጣለን በኋላ ብዙ ነው ጉዱ። እግዚአብሔር በምሕረቱ እስኪያነሣን ድረስ፣ ያለው ስብራት ቀላል አይሆንምና። እንዲህ የሚያደባና የማይተኛ ጠላት ካለን፣ የሌላው ወገናችን ጉድ ላይ ጊዜ

መግደሉ ምን ይጠቅመናል? ከሚዋጡ ተረኞች መኻል አንዱ ተረኛ ላለመሆን መጋደሉ ነው ሊታሰብበት የሚገባው።

ሕይወቱ ኃይለኛ መሆንን ይፈልጋል (ማቴ.11፥12)። ቆራጥነትን ይጠይቃል። እምቢተኝነትን ግድ ይለናል። ብዙውን ጊዜ በጌታ እግር ስር በጽሞና መሆን፣ ቃሉን ማሰላሰል እናም ደግሞ በተግባር ቃሉን በድርጊት በሕይወታችን መተርጐም ይጠይቀናል። ደግሞም "ተው፣ተመለስ" እያለ በለሆሳስ የሚናገረንን የጌታን ድምፅ ስንሰማ  መታዘዝ ይገባናል።

ወገኖቼ እጅግ ንቁ መሆን ይገባናል ብዬ አምናለሁ። በብዙ ተማፅኖና ጩኸት በፊቱ መሆን ይገባናል፤ እንዲህም እየተተጋ እንኳ ድጡ ከባድና አስፈሪ እየሆነ ነውና! ብዙ ሰዎች በዝማሬና በስብከት ብቻ ነው የሚኖሩት። የሰዎችን የንባብ ሕይወት በግሌ እሰልላለሁ። በዙሪያዬ ያሉ በርከት ያሉ ሰዎች፣ የማንበብና የጸሎት ልምዱ የላቸውም። በቅንጥብጣቢ ስብከትና የትንቢት መልእክት ተንጠልጥለው፣ በጠኔ ያሉም አይጠፉም። አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሊሸጡ የተዘጋጁትን የመጻሕፍት ብዛት ሲነግረኝ፣ ማመን አቅቶኛል። የረጅም ጊዜ መንፈሳዊ ልምምድና ብስለት ያላቸው ደራሲያን መጻሕፍት በመደርደሪያ ላይ ተሰድረው እንደሚገኙ አሳይቶኛል። ገንዘብ የሚያደርጋቸውና ይዟቸው የሚሄድ ሰው አጥተው ለረጅም ጊዜ እንደ ተረሱ ነው የነገረኝ። "ሰው የመዝሙር ካሴት ብቻ ነው የሚገዛው" ብሎ እጅግ እያዘነ አጫውቶኛል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታቸው በኃይል እንዲጠነክሩ እጸልይላችኋለሁ" ብሎ ነግሯቸዋል (ኤፌ.3፥16)። ይህ ጸሎት በእኛም ሕይወት  መጸለይ የሚገባው ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈሳዊ ሕይወታችን መጠንከራችንን መንፈስ ከሆነው

ቃል ጋር ያለን ቁርኝት እንደሚወስነው በገለጸበት ክፍል፣ *"ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምሥጢር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን።"* (ሮሜ 16፥26) ብሎ ተናግሯል። ሐዋርያው እንዳለው፣ እንደ ተገለጠልን መጠን ነው መንፈሳችን የሚጠነክረው። ቆመን በጽኑነት መራመድ የምንችለው፣ የቃሉ ብርሃን ባገኘን መጠን ነው። እስቲ አስቡት መንፈሳችን ካልጠነከረ፣ እንደ ጐርፍ እየመጣ ያለውን የጠላት ከበባ እንዴት እንቋቋመዋለን? መንፈሳችን የሚጠነክረው ደግሞ ቃሉን ሳናሰልስ በመብላት ነው። በማሰላሰል ነው። ከጾምና ከጸሎት ጋር በማጣመር በልባችን ላይ ሲጻፍ ነው። አለበለዚያ ግብዞችና አስመሳዮች ሆነን እንቀጥላለን። ፈተና ሲመጣም ተልፈስፍሰን መውደቅ ብቻ ይሆናል ዕጣ ፈንታችን።

የእግዚአብሔር ቃል *"ስለዚህ ቅዱስ ሁሉ በምቹ ጊዜ ወደ አንተ ይለምናል፣ ብዙ የጥፋት ውኃም ወደ እርሱ አይቀርብም/ therefore every godly person should pray to you at such a time. Surely a flood of great waters will not reach him (ISV)"* (መዝ.32፥6) ይላልና አስቀድመን በበቂ ሁኔታ እንታጠቅ! እንንቃ !

**መዝጊያ ምንባብ፡-** *"የሚቀጠቅጥ በአንተ ላይ ወጥቶአል፤ ምሽግን ጠብቅ፥ መንገድንም ሰልል፤ ወገብህን አጽና፥ ኃይልህንም እጅግ አበርታ።"* (ናሆ.2፥1)

# ሰማያዊ ሽክም

*“ጸሎት ግልጽ የሆነ በራሳችን ምንም ማድረግ እንደማንችል አውቆ መረታት ነው። ጸሎት በእግዚአብሔር ላይ በመታመን ከራሳችን ወደ እርሱ መዞር ነው።” ጆን ፓይፐር*

በውስጣችን እውነተኛ የሆነ ከአርያም የተቀበልነው ሸክም ሲኖር አያስተኛንም፤ በፍጹም ዕረፍት አይሰጠንም። ስለሆነም የመንፈስ መለቀቅ እስኪመጣና እስኪሰማን ድረስ ያስቃትተናል፣ ያስጮኸናል። የእግዚአብሔርን ፊት እንድንፈልግ ያደርገናል። ታዲያ በመሰጠት፣ በጽኑነት፣ በትጋትና በውሳኔ የሚጸለይ ጸሎት ብዙ ፍሬን ማፍራቱ አይቀሬ ነው፤ ባለፉት ዘመናት በነበሩ ብዙ የእንባ ሰዎች ታይቷልና። ለምሳሌ ያህል ሞኒካ በዓለማችን በመንፈሳዊ ሕይወቱና *ሥራው* እጅግ ታዋቂ የነበረውና፣ አሁንም ከሞተ በኋላ እንኳ በተወልን ወደር የሌላቸው የጽሑፍ *ሥራዎቹ* የሚባርከን የቅዱስ አውግስጦስ (Augustine of Hippo) እናት ነበረች። ይኼ ሰው ወደ ዓለም መድረክ ብቅ ከማለቱ በፊትና ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ ተጽእኖ ከማምጣቱ በፊት፣ ለልጇ የሕይወት ለውጥ የሷ ለረጅም ጊዜ የማያቋርጥ፣ የውሳኔና የእንባ ጸሎት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደ ነበረው ታሪክ ዘክሮታል።

ወደ ጌታ ከልብ የሆነ ጩኸትና መቃተት እውነተኛ ትሕትናን ያሳያል። ያለ ምንም ሁኔታ ራስን ለጌታ መስጠትንም ያመለክታል። *“ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም”* (ዮሐ.15፥5) የሚለውን የጌታ የኢየሱስን ቃል አጥብቆ መረዳትንም ያሳያል። ንጉሥ ዳዊት በእንደዚህ ዓይነት የልብ ይዘት ሆኖ ነበር *“በጨነቀኝ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት፣ ወደ*

*አምላኬ ጮኽሁ፣ ከመቅደሱ ቃሌን ሰማኝ፤ ጩኸቴም ወደ ጆሮው ገባ።"* (መዝ.18፥6) በማለት በእውነትና በመንፈስ የተጸለየ ጸሎት ከጣሪያ እንደሚያልፍ፣ ደግሞም ውጤትና ፍሬ እንደሚኖረው የመሰከረው።

አዎ፣ እንደ ንጉሥ ዳዊት እውነተኛ ሸክም ያላቸው፣ በዙሪያቸው የሚያዩት አሳዛኝ ነገር ግድ የሚላቸው፣ ራእይን ያረገዙ፣ ላሉበት ትውልድ የሕይወት ጉዞ የሚያስቡና ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚጨነቁ ሰዎች እንቅልፍ አይኖራቸውም። ስለዚህም ይማልዳሉ፣ ይቃትታሉ፣ ይጮኻሉ፣ ያለቅሳሉ፣ በመንፈስ ኃይል ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ ይገሠግሣሉ። እንደዚህ ዓይነት የተሰጡ ሰዎች ሲበዙ፣ ቤተ ክርስቲያን በፍሬ እንደምትሸፈን ምን ጥርጥር አለው? ቃሉ *"ወይም ጒልበቴን ይያዝ፣ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ፤ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ። በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፣ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።"* (ኢሳ.27፥5-6) ይላልና!

ከየትኛውም ዘመን ይልቅ የጌታ ጉልበት በጸሎት ሊያዝበት የሚገባው ዘመን መቼ ነው ካላችሁኝ፣ ይህ የአሁኑ ዘመን ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ሁኔታው ሁሉ እጅግ እየጨላለመና አስፈሪ እየሆነ ነውና ነው። ሰይጣንም በታላቅ ቁጣ ምድሪቷን ሊያተራምስ እንደ ወጣ ግልጽ እየሆነ መጥቷልና ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ እጅግ ብዙ ቅጥሮች ፈርሰዋል። ብዙ አሳዛኝ ነገሮችን በየዕለት ኑሯችን ማየታችን እጅግ ተለምዷል።

በዚህ ሰዓት እግዚአብሔር ከአማኞች ምን ይፈልጋል? የተባለ እንደ ሆነ፣ የፈራረሱ ቅጥሮችን በመንፈስ ዐይተው፣ አያሌ ቀን የሚያዝኑ፣ በሰማይ አምላክ ፊት የሚጾሙና የሚጸልዩ (ነህ.1፥4) ሰዎችን እንደሚፈልግ

ምንም አያጠያይቅም። እርሱ ከክርስቲያኖች ተግባራዊ ርምጃዎችን ይፈልጋልና። በልቅሶና በምጥ በእርሱ ፊት ወድቀውና በመቃተት ጨርሰው፣ በተግባር ለሥራ የሚነሡ ሰዎችን ይፈልጋል፤ ለሕዝቡ የሚገድደው ጌታ አምላክ በኢሳይያስ መጽሐፍ ላይ እንዲህ ብሏልና፡- *"ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ጉበኞችን በቅጥርሽ ላይ አቁሜአለሁ፤ ቀንና ሌሊት ከቶ ዝም አይሉም፤ እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ፣ ኢየሩሳሌምን እስኪያጸና በምድርም ላይ ምስጋና እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ ለእርሱም ዕረፍት አትስጡ።"* (ኢሳ.62፥6-7)!

አዎ! ጌታ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ ጉዞ፣ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተጽእኖ፣ ቀንና ሌሊት ዝም የማይሉ ትጉሕ ጉበኞችን ይፈልጋል። በረድኤቱ ታምነው የሚጠሩት፣ የሚጮኹ፣ የሚቃትቱ፣ ያለ መታከትና ያለ መሰልቸት ፊቱን ተግተው የሚፈልጉ የተሰጡ ሰዎችን ይሻል። *"በመከራ ቀን ጥራኝ፣ አድንህማለሁ፣ አንተም ታከብረኛለህ።"* (መዝ.50፥15) የሚል የከበረ የተስፋ ቃል የሰጠንም ለዚህ ነው። ስለሆነም ታማኝ የሆነው ጌታ እስኪጐበኘንና ቤተ ክርስቲያንን የምስጋናና የተጽዕኖ ስፍራ እስኪያደርጋት ድረስ ሸክሞቻችንን ይዘን በፊቱ እንውደቅ!

**መዝጊያ ጥቅስ፡-** *"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።"* (ማቴ.11፥28-30)

# ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል

*“ራሳችንን በቃሉ ማጠንከር አለብን።/ “We need to fortify ourselves with the Word of God.” ቢሊ ግራሃም*

የእግዚአብሔር ቃል *“ልጄ ሆይ፥ መልካም ነውና ማር ብላ፤ ወለላም ለጣምህ ጣፋጭ ነው። ጥበብም ለነፍስህ እንዲሁ እንደሚሆን እወቅ፤ ብታገኘውም ፍጻሜህ መልካም ይሆናል፥ ተስፋህም አይጠፋም።”* (ምሳ.24፥13-14) ብሎ ይናገራል። ልክ እንዲሁ፣ የእግዚአብሔር ቃል በሌሎችም በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ስፍራዎች በወተት፣ በእንጀራ፣ በማር እና በጮማ ተመስሎ እናገዋኛለን። ለነገሩ ከዚያም በላይ ነው፤ ለጣፋጭነቱ ወደር የለውምና። የነፍስ ምግብ ነው፤ ሕይወትን ያስውባልና። ተስፋ የቆረጠችን ነፍስ ያለመልማል። ውስጥን በብርሃን ይሞላል። ልብን በደስታና በተስፋ ያሞቃል ወዘተ።

በበኩሌ ወደ ጌታ የመጣሁት ከድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ነው። ወደ እርሱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከመጣሁ በኋላ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሕይወቴን እንዴት እንዳስተካከለውና ቅርጽ እንዳስያዘው በቃላት መግለጽ ያቅተኛል። ቃሉ *“የጻድቃን መንገድ ቅን ናት። አንተ ቅን ነህ፣ የጻድቃንን መንገድ ታቀናለህ።”* (ኢሳ.26፥7) ይላል አይደል? የተወላገደ አስተሳሰቤን፣ ፈጽሞ የተጣመመ ዕይታዬንና ያልተስተካከለ የሕይወት ምልልሴን ጠርቦና አርሞ፣ ሰው አድርጎኛል፤ ገና እጅግ ብዙ የሚቀረኝ ነገር ቢኖርም።

ንጉሥ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን ፍቅር ሲገልጽ፣ *“እጅግ በወደድኋቸው በትእዛዝህ ደስ ይለኛል።”* (መዝ. 119፥47) ይላል። ቋንቋ

ያጠረው አይመስልም? እርግጥ ነው ስለ እግዚአብሔር ቃል ጣፋጭነትና ግሩምነት ለመግለጽ ቃላት ያጥራል፣ ያንሳልም። ይህ መዝሙረኛ በሌላ ቦታ ደግሞ ስለ ቃሉ ውድነት ሲናገር፣ *"ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል፤ ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል።"* (መዝ.19፥11) ብሎ ተናግሯል።

*"ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል"* የሚለውን አስምሩልኝ። ለዚህ ነው ይህ ምስጢር እንዲታየን፣ በኃይል መጮኽና መጸለይ የሚያስፈልገን። አለበለዚያ ግን የሚገባውን ክብርና ትኩረት ላንሰጠው እንችላለን የሚል ምልከታ አለኝ። መዝሙረኛው በሌላም ቦታ *"ምስክርችህ ድንቆች ናቸው፣ ስለዚህ ነፍሴ ፈለገቻቸው።"* (መዝ.119፥129) በማለት ከቃሉ ጋር ያለውን ቁርኝት፣ ፍቅርና ትስስር ይገልጻል።

በግሌ ሁልጊዜ መዝሙር ዳዊት ምዕራፍ 119 ላይ ደርሼ ለቃሉ የተሰጠውን ከበሬታ፣ ዘማሪው ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን ፍቅርና ራብ ሳይ *"እንዴት መታደል ነው?"* እላለሁ። ለቃሉ የሚገባውን ክብር እንድሰጥ *"እባክህ ጌታ ሆይ ዓይኖቼን ክፈት"* ብዬም እጸልያለሁ።

የእግዚአብሔር ቃል ሕይወትን በመለወጥ ረገድ ወደር የለውም። ወደ ግድያ የሚገሠግሥን ልብ ይለውጣል። በቂም የተሞላን ሕይወት ያሳርፋል። ከክፋት ያስጥላል። ስስትን በለጋሥነት ይለውጣል። ጥላቻን በፍቅር ይቀይራል። ቸልተኛን በትጋት ይሞላል። ኀዘንተኛንና ቆዛሚን በዝማሬ፣ በምስጋናና በሐሤት ያዘልላል። የተከፈተና በትሕትና የቀረበ ልብ ያግኝ እንጂ፣ ኧረ ምን የማያደርገው ነገር አለ?

**መዝጊያ ጥቅስ፡-***"ልጄ ሆይ፥ መልካም ነውና ማር ብላ፤ ወለላም ለጣምህ*

*ጣፋጭ ነው። ጥበብም ለነፍስህ እንዲሁ እንደሚሆን እወቅ፤ ብታገኘውም ፍጻሜህ መልካም ይሆናል፥ ተስፋህም አይጠፋም።”* (ምሳ.24፥13-14)

# የዕረፍት ምስጢር

*“እግዚአብሔር ሆይ አንተ ለራስህ ፈጠርኸን፤ ስለሆነም ነፍሳችን ባንተ እስካላረፈች ድረስ ዕረፍት አልባ ናት።/ Thou hast created us for Thyself, and our heart is not quiet until it rests in Thee.” – ቅዱስ አውግስጦስ*

ሰው ሲፈጠር ነፍሱ በሰዋዊ፣ ምድራዊና *ሥጋዊ* በሆነ ነገር እንዳትጠግብ ተደርጋ የተሠራች እንደ ሆነች ነው የምረዳው። ለሰው የፈለጋችሁትን ገንዘብ፣ ልብስ፣ ክብርና ዝና ስጡት፣ ካለው ነገር ላይ ትንሽ መጨመር ይሻል። ሮክፌለር “ሰው ምን ያህል ገንዘብ ቢኖረው ይረካል?” ተብሎ ተጠይቆ ነበር ይባላል። እርሱም “ካለው ጥቂት ቢጨምር” ብሎ መልሷል አሉ። ንጉሥ ሰለሞን “የሰው ድካም ሁሉ ለአፉ ነው፣ ነፍሱ ግን አትጠግብም” (መክ.6፥7) ያለው ለዚህ ነው። አዎ፣ ነፍስ ከፈጣሪዋ ሳትገናኝና መንፈሱ ሳያረሰርሳት እንኳን ጥጋብና እፎይ ማለትስ እንዴት ይታሰባል?

የሰው ልጅ የሦስት ነገሮች ሕብር (ሥጋ፣ ነፍስና መንፈስ) መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ። ለዚህም ነው ሰው የውስጥ ማንነቱን ዘልቆ ወይም ከመንፈሱ ደርሶ ሊነካውና ሊያረካው የሚችልን ነገር ለማግኘት ብዙ ነገር የሚሞክረው። ቢሆንም የሚያደርጋቸው ነገሮች ነፍሱ ድረስ ይደርሱ እንደ

ሆነ ነው እንጂ፣ በውስጡ በመንፈሱ ላይ ያለውን ባዶነት በፍጹም አይሞሉለትም። ለዚህ ነው የአይሁዶች የዳስ በዓል ማብቂያ ላይ፣ በተለያዩ ግብዣዎች ሲንበሸበሽ ለከረመ ሕዝብ፣ ጌታ ኢየሱስ “ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ፣ መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ምንጭ ከሆዱ ይፈልቃል።” (ዮሐ.7፥37) ብሎ ያልተጠበቀ ግብዣ ያቀረበው። ይገርማል! እንደ ጉድ ዘና ሲል፣ ሲበላና ሲጠጣ የከረመን ሕዝብ፣ “ማንም የተጠማ ቢኖር” እንዴት ይባላል? እየጠጡ ጥማት አለ እንዴ?

በግሌ ምድራዊ ነገር እንደማያጠግብና እንደማያረካ በሚዳሰስ መልኩ አይቼዋለሁ። ርካታ፣ ዕረፍትና እፎይታ የማገኝ መስሎኝ ጫቱን፣ መጠጡን፣ ፊልሙን፣ ወሬውን ምኑ ቅጡ…ያልሟጠጥኩት ነገር የለም። ምን ያልነካሁት ነገር ነበረ? አሁን ምሕረቱ በዝቶልኝና አንዱም እንደማያረካ ገብቶኝ በአምላኬ ተረጋግቼአለሁ። አሁን፣ “እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ፤ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ። ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፥ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? አድምጡኝ፣በረከትንም ብሉ፣ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው። ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ፤ ስሙ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች።” (ኢሳ.55፥1-3) ለምን እንደ ተባለ በጥቂቱም ቢሆን ገብቶኛል።

ዘወትር ለሰው ልጆች ሁሉ የሚቀርበው ጥያቄ “የድካማችሁን ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ?” (ክርስቲያኖችንም ጨምሮ) የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ እስክንሰጥ ደረስ መባከናችን ይቀጥላል። ይህ እስኪገባንና ዓይኖቻችን እስኪከፈቱ ድረስ፣ ብዙ የነፍስ

መዳከር አለ፤ ብዙ ማውጣትና ማውረድ አለ፤ ብዙ ዘዴዎችን መዘየድም ይኖራል። ብዙ መታለልና መሳትም እንደ ልብ ነው። ብዙ የከበሩ የሚመስሉ ነገሮችን መሞከርና መቀያየር እንደ ብልሃት ተቆጥሮ፣ ገንዘብን፣ ኃይልንና ጊዜን መጨረስም ይኖራል። ትልቁ እውነታ ግን ይህ ነው። ሰው ወደ ነፍሱ እረኛና ጠባቂ በትሕትና መጥቶ እራሱን ካላስረከበ በስተቀር እፎይታ የለም፤ እረፍት የለም። ሁከት ብቻ፤ መቅበዝበ ብቻ፤ መንከውከው ብቻ!

የሰው ልጅ እጅ ወደ ላይ ብሎ ከአምላኩ ጋር ሲስማማና አብሮ ለመሄድ ሲወስን፣ የሚያገኘው መንፈሳዊ ሕክምና እጅግ ነፍስን የሚያሳርፍና የሚያጠግብ ይሆናል፤ እጅግ የሚያረካና የተወጠረውን ውስጣችንን የሚያረግብና ዘና ብለን እንድንኖር የሚያደርግ ይሆናል። እንዲህ ብሎ እንደ ተጻፈ፡- *“እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ከኔም ተማሩ፤ለነፍሳችሁም እረፍትን ታገኛላችሁ።”* (ማቴ.11፥28)!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*“አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጒልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፥ ጐበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፤ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደክሙም።”* (ኢሳ.40፥28-31)

# መለኮታዊ ጉብኝት (Holy Encounter)

*“ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ (ኢየሱስ) አንዴ ካገኘን በኋላ፣ ማንኛውም ነገር ወደ ኋላ ተመልሶ እንደ ቀድሞው አይሆንም።/ After an encounter with the living Son of the living God, nothing is ever again to be as it was before.” —ጀፍሪ ሆላንድ*

ባለፉት ዘመናት በጽሑፍ ላይ ያየናቸው መለኮታዊ የሆኑ ጉብኝቶች (divine encounters)፣ አሁንም በዚህ ዘመን በሚገባ ይከሰታሉ። ማለትም ከእግዚአብሔር የሆኑ መለኮታዊ ጉብኝቶች ጊዜ አላለፈባቸውም። ጉብኝቱ ያልጠበቅነውና ጌታ ራሱ ባቀደው ሰዓት ስለሚሆን፣ በፍጹም በሕይወታችን ልንረሳው የማንችል ትውስታን ጥሎልን ያልፋል። እኛ ልናቅደውና በፈቃዳችን ልንለማመደው የማንችል መሆኑ ግን ሊሰመርበት ይገባል። ከእኛ የሚጠበቀው አንድ ነገር ነው፤ ባርኮቱን ለመቀበል መንፈሳዊ ጆሮአችንንና ልባችንን ከፍተንና ራሳችንን ንቁ አድርገን መጠበቅ ነው።

“መለኮታዊ ጉብኝት (holy encounter) ሲመጣ ምንድነው የሚሆነው?” ለሚለው ጥያቄ አንድ የእግዚአብሔር ሰው *“መለኮታዊ ጉብኝት የእግዚአብሔርን የማይደረስ ከፍታ እንድናውቅ ዐይኖቻችን ይከፍታል/ an encounter with God opens our eyes to recognize His unapproachable superiority.”* ብለዋል። በሌላ አገላለጽ እንዲህ ነው የሚሆነው። ሕልውናውና ክብሩ በሚገርም ሁኔታ ሲታወቀን፣ ያለ እርሱ የማንረባ ሰዎች መሆናችን እንረዳለን፤ የእግዚአብሔርን መሐሪነትን እንገነዘባለን፤ በተግባር ደረጃ ታዛዦች እንሆናለን። ቋንቋችን

*"ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?"* (የሐዋ.9፥6) የሚል ብቻ ይሆናል።

በኢዮብ መጽሐፍ ላይ ኢዮብ ወደ መጀመሪያ አካባቢ የነበረው መንፈሳዊ አቋም በሚቀጥለው ጥቅስ ተንጸባርቋል። *"ጽድቄን አይዛለሁ፥ እርሱንም አልተውም ከቀኖቼ ሁሉ ስለ አንዱ ልቤ አይዘልፈኝም።"* (ኢዮ.27፥6) በሚል። ከጓደኞቹ ጋር በርከት ያሉ ምዕራፎች ሲከራከር ከቆየ በኋላ፣ ወደ መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር ክብሩንና ማንነቱን በተለየ መንገድ ሲገልጽለት ከመጀመሪያው አቋሙ እጅግ የሚለይና የልብ መሰበር የታየበት ምላሽ ነበር ከአፉ የወጣው፤ *"መስማትን በጆሮዬ በመስማት ሰምቼ ነበር አሁን ግን አይኔ አየችህ ስለዚህ እራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ"* (ኢዮ.42፥5-6) በማለት። እጅግ የሚገርም ትሕትና እና ለጌታ የተንበረከከ ሰው ቋንቋ ነው! ታዲያ ለዚህ ምላሽና መንበርከክ ያበቃው ምንድነው? የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ሁሉን ቻይነት ከቀደመው ልምምዱ በላቀ ሁኔታ በመንፈስ ማየቱ ነዋ!

እግዚአብሔርን በግርማውና በክብሩ ማየት አስደንጋጭና አስፈሪ ልምምድ ቢሆንም፣ ክስተቱ በሕይወታችን የማንረሳውና በውስጣችን ታትሞ የሚቀር ስለሚሆን፣ ለመንፈሳዊ ርምጃችን እጅግ ጠቃሚ ነው ብዬ አስባለሁ። አንድ የእግዚአብሔር ሰው በጻፉት መጽሐፋቸው ላይ *"የእግዚአብሔር ሰዎች ጌታን ለማገልገል ሲነሡ እንዲህ ዓይነት ገጠመኝ (traumatic experience) ቢኖራቸው መልካም ነው"* ብለው ተናግረዋል። እኔም ይህንን ሐሳብ በሚገባ እጋራዋለሁ።

እንዲህ ዓይነት ገጠመኝ ወይም ጉብኝት (holy encounter)

በሕይወታችን ትልልቅ ለውጦችን ያመጣል። ለምሳሌ፡-

- የልብ መሰበር፣
- ጥልቅ ንስሐ፣
- በቃላት መናገር የማይቻል መረጋጋት፣
- ታዛዥነት።

በነቢዩ ኢሳይያስ ሕይወት ላይ (ኢሳ.6፥1-8ን ያንብቡ) የተከሰተው ነገር በኢዮብ ላይ ከተከሰተው ሁኔታ ጋር ቢለያይም፣ የሚያመሳስላቸው ነገር ግን ላዩት ነገር የሰጡት ምላሽ ነበር። በሁለቱም የእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት የልብ መሰበር ታይቷል። ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በሚገርም ግርማና አስፈሪ ክብር ሲያይ፣ *"ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ።"* (ኢሳ.6፥5) ነበር ያለው። ልቡ የተሰበረ የትሑት ሰው ቋንቋ አይደል?!

በእኛም ሕይወት እንዲህ ነው የሚሆነው። የጌታን ግርማ፣ ኃያልነት፣ ቅድስናና ክብሩን እስክናይ ድረስ ሰዎችን አብጠልጣይ፣ ትዕቢተኛ፣ ኩሩ፣ አትንኩኝ ባይ፣ ተናጋሪ፣ ከሳሽና ግትር ነን። እርሱን በክብሩ ስናየው ግን ነገሮች በመጠንም በዓይነትም ይቀየራሉ። በሚገርም ሁኔታ አስተሳሰባችን፣ አመለካከታችንና ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ይቀየራል። ለራሳችን ያለን ግምትም ይቀየራል። እናም በቀጣይነት በምናሳልፋቸው የሕይወት ጎዳናዎች እያደገ መሄድ ቢያስፈልገውም፣ እውነተኛ ትሕትና በሕይወታችን መታየት ይጀምራል።

ከላይ የተገለጸው ዓይነት መለኮታዊ ገጠመኝ ወይም ጉብኝት (holy encounter) ሲያገኘን በማይረሳ ሁኔታ ሕይወታችን ስለሚለወጥ እንደ ኢዮብ፣ *"እራሴን እንቃለሁ"* (ኢዮ.42፥6) ወይም እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ፣ *"ጠፍቻለሁ ወዮልኝ"* (ኢሳ.6፥5) እንላለን እንጂ ሌላ ቋንቋ አይኖረንም። ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ባርኮት እንዲያገኘን ምን እናድርግ? ይህንን መሰል ጉብኝት (holy encounter) ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲያገኘን፣ በፊቱ በጽኑ ፍለጋና ጉጉት እንውደቅ!

***መዝጊያ ምንባብ፡-****"መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ።"* (ኢዮ.42፥5-6)

# ማንስ ይመስለዋል?

መንፈሱ ሲመጣ ክብሩ ከተፍ ሲል

መገኘቱ ደምቆ ቅርብነቱ ሲያይል

በኃይል በችሎታው ቀንበር ሲሰባበር

የቆዘመው ሁሉ ሲነሣ ሲዘምር

ምስጋናና አምልኮ በሕብር ሲወጡ

የአምላክ ልጆች በአንድ ውዳሴን ሲያመጡ

ልቦች ሲፈወሱ ምንኛ ይጥማል?

እርሱ ይገኝ እንጂ፣

ምን የማይሆን አለ?

ማንስ ይመስለዋል?

# ለጌታ ሊኖረን የሚገባ ምላሽ

*"ጸሎት ያለ ምንም ጥርጥር እጅግ ከፍ ያለው የሰው ልጅ ነፍስ ክንውን ነው። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፊት ለፊት በጉልበቱ ሲንበረከክ ትልቁንና ከፍተኛውን ተግባር አከናውኗል።/ Prayer is beyond any question the highest activity of the human soul. Man is at his greatest and highest when upon his knees he comes face to face with God." ማርቲን ሎይድ ጆንስ*

የእግዚአብሔር ቃል *"የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ። መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና።"* (ኤፌ.5፥17-18) ብሎ ይመክራል። አዎ፣ *"መንፈስ ይሙላባችሁ"* ነው አንዱ ትልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት። ከዚህ ርካታ በሚመነጭ ኃይልና ረድኤት ነው ጌታ አምላክ እንድናገለገለው የሚፈልገው።

እስቲ በመኃልይ 5፥1-6 ያለችው ሴት ተመልከቷት። ስለ ውዷ በቂ ዕውቀት የነበራት ሴት ነበረች። እርሱ ሊጎበኛት ሲመጣ ግን በቂ ምላሽ ለመስጠት ዘገየች። አጥጋቢ ምላሽን ባለመስጠቷም ጥሏት ሄደ፤ ከዚህም የተነሣ የደረሰባትን መከራ ነው ምንባቡ የሚያሳየን።

ለዚች ባለ ዕድል ሴት የቀረበው ግብዣ *"እስክትረኪ ድረስ ጠጪ"* (መኃ.5፥1) የሚል ነበር። ይሁን እንጂ በሩን እንድትከፍትለት ቢጋብዛትም፣ ሳትከፍትለት ቀረችና በረከቱ አመለጣት። በእኛም ሕይወት የጌታ ከፍ ያለው ሐሳብ ከእርሱ ጋር ከሚኖረን ኅብረት የተነሣ፣ ርካታና ዕረፍት ወደ ሕይወታችን እንዲመጣ ነው። ይህ ዕረፍትና ርካታ በሕይወታችን ሲኖር፣ ባልዳኑና ጌታን ባላገኙ ሰዎች መካከል ጠንካራና የሚታይ ምስክሮች ያደርገናል። ቢሆንም ግን አሁን እንደሚስተዋለው፣ እኛ ክርስቲያኖች ለጌታ አጥጋቢ ምላሽ እየሰጠን ያለን አይመስለኝም።

የጌታ መንፈስ በምድረ በዳ ሲጓዝ ለነበረው የእርሱ ሕዝብ፣ *"...ተቆጥቼ 'ዘወትር በልባቸው ይስታሉ መንገዴን ግን አላወቁም አልሁ' ፤ እንዲሁ 'ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ።"* (ዕብ.4፥10-11) ብሏል። የጌታችን የልብ ሐሳብ ለሕይወታችን መልካም ሆኖ ሳለ፣ በእኔም በራሴ ሕይወት ብዙ ጊዜ ልቤ ሲያፈነግጥ፣ ሳስቸግረው እና ስንጋደድ እራሴን ደጋግሜ አየዋለሁና እጅግ አዝናለሁ። ማለትም የኔና የብዙዎች ወገኖቼ ሕይወት፣ ከዚች ሴት ምላሽ ጋር በሚገባ ይመሳሰልብኛል።

ጌታ ኢየሱስ ራሱ *"እኔ ሕይወት እንዲሆናችሁ እንዲበዛላችሁ መጣሁ።"* (ዮሐ.10፥10) የሚል ትልቅ የተስፋ ቃልን ሰጥቶናል። የእርሱ ዋና ሐሳብም፣ ሕይወቱ በዝቶልን ለሌሎች እንድንተርፍ ነው። ነገር ግን እንደምታዘበው ከእኔም ሆነ ከብዙ ክርስቲያኖች፣ በቂ ምላሽ እያገኘ እንዳልሆነ በመንፈሴ አያለሁ። ብዙ መንፈሳዊ ነገሮችን በቀለም ደረጃ እናውቃለን። ሆኖም ግን እያንዳንዳችን ራሳችንን የሚከተሉትን ጥያቄዎች እስቲ እንጠይቅ፡-

- ጌታን በሚገባ በግል እናውቀዋለን?
- ከእርሱ ጋር ባለን ኅብረት ረክተናል ወይ?
- ለመሆኑ ሕይወቱ በዝቶልናልን?
- ከዚህ የተነሣ ሰዎች በእኛ ሕይወት ክርስቶስን እያዩ ነውን?

ክርስትና እነዚህ ከላይ ያሉት ጥያቄዎች በበቂ ሁኔታ በሕይወታችን ምላሽ እንዲያገኙ ግድ ይለናል። ቅዱስ ቃሉ *"ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ይቀርባችኋል።"* (ያዕ.4፥8) እንደሚል፣ በእኛ በኩል የምንወስዳቸው የመቅረብ ውሳኔዎችና እውነተኛ ተግባሮች በሕይወታችን እነዚህ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል። እናም ወደ ጌታ በቀረብን ቁጥር በመንፈሱ እየታደስንና፣ ከፍ ያሉ ዕይታዎችን እያገኘንና ግንኙነታችን እየጠለቀ ይመጣል። በዚህ በጠለቀ ግንኙነት ስንቀጥል፣ መንፈሳዊ ርካታ ወደ ሕይወታችን መምጣቱ አይቀሬ ይሆናል። ይህ ርካታ ደግሞ ምድራዊና ረብ ለሌላቸው ነገሮች እንዳናጎነብስና እንዳንሰጥ ኃይል ይሆነናልና ለውጡ ቀላል አይደለም የሚሆነው።

የጌታችን ለእኛ ያለው ዓላማ በመኃልይ 5፥1 እንደተጠቀሰው እስክንረካ ድረስ ከመንፈሱ እንድንጠጣ ነው። ለዚህ ቃል ማረጋገጫ የሚሆነን ደግሞ *"ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጻሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል።"* (ዮሐ.7፥37) የሚለው ድንቅ ግብዣ ነው። ይህንንም ኢየሱስ የተናገረው ታላቁ የአይሁዶች የዳስ በዓል ሊያልቅ ትንሽ ጊዜ ሲቀረው ነበር። ሰው ሁሉ በግብዣ ተንበሽብሾ ከከረመ በኋላ በመሆኑ፣ በሌላ መንገድ የቆያችሁበት ግብዣ ውስጣዊ እና ዘለቄታዊ ርካታ የለውም ማለቱ ይመስላል። እውነት

ነው፤ ለጊዜው እንሸነገል ይሆናል እንጂ፣ በየትኛውም ድል (ጠብቆ ይነበብ) ያለ ምድራዊ ግብዣ ላይ ብንገኝ፣ ውስጣዊ የሆነና ዘለቄታ ያለው ርካታ አናገኝም።

*“ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጻሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል።”* (ዮሐ.7፥37) ምንባብ እንደሚጠቁመን፣ የሰው ልጅ ውስጥ የሆነ *‹‹ጥማት››* እንዳለ እንገነዘባለን። ይህንን *‹‹ጥማት››* ደግሞ በተለያየ ነገር ለማርካት የሰው ልጅ የማያደርገው ነገር የለም። ነገር ግን የሰው ልጅ ወደ ነፍሱ እረኛና ጠባቂ በሚገባ ካልተመለሰ በስተቀር በዚህ ምድር ነፍሱን የሚያረካ፣ ከጥማትና ከመቅበዝበዝ የሚያወጣውና የሚገላግለው ምንም ነገር የለም። የጌታ መንፈስ *“እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ። ገንዘብን እንጀራ ላይደለ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ለምን ትመዝናላችሁ አድምጡኝ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው።”* (ኢሳ.55፥1-2) በሚል እጅግ አስደናቂ ግብዣ የሚወተውተን ለዚህ ነው።

በተለያየ ምድራዊ በሆነና ከሰዓታት በኋላ በሚበን ደስታ መሳይ ነገር፣ ጊዜያችሁን አታጥፉ ይልቁንም *‹‹ልባችሁ በጮማ ደስ ይበለው››* ነው ቃሉ እያለን ያለው። *‹‹ጮማ››* የሚለው ቃል በዚህ ዐውድ መሠረት ከእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ጋር ግንኙነታችን ሲጠልቅ የምናገኘውን ባርኮት ነው የሚጠቁመን። በግሌ ሁልጊዜ ይህንን ቃል ሳነብብ፣ ከባድ መንፈሳዊ ጉጉትን ነው የሚፈጥርብኝ። ይህ በረከት ደግሞ ልባችንን ከምናስበው በላይ እጅግ ያረካዋልና፣ የሚመጣው ለውጥ ቀላል

አይደለም። የሚገኘው ደስታ ደግሞ፣ በሰዓታት የሚበንን ሳይሆን እያደር የሚግልና እየበረከተ የሚሄድ መሆኑን ልብ ይሏል። ይህንን በሕይወቴ ስላየሁ ሕያው ምስክር ነኝ። በቃ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ዓላማና ፍቃድ ከመንፈሱ ጠጥተን እንድንረካ ነው! ሌላው ነገር ሁሉ ከዚህ የመነጨ ይሆናል!

ስለዚህ ያለ ምንም ማወላወልና ማመንታት ወደ ጺጋው ዙፋን በመምጣት፣ በፊቱ በቂ ጊዜን በመወሰንና በመጨከን እናሳልፍ። ከእግዚአብሔርም ቃል ጋር በቂ ጊዜ ይኑረን። ያኔ አስደናቂ የሆነ ሕይወት ውስጥ እራሳችንን እናገኘዋለን!

**መዝጊያ ምንባብ፡-***"በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል፥ ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ፥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል። እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁንም ምንም ባታዩት በእርሱ አምናችሁ፥ የእምነታችሁን ፍፃሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ፥ በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ይላችኋል።"* (1ጴጥ.1፥6-9)

# ሕዝቤ ሰምቶኝ ቢሆን

*“እኔ እንደምረዳው፣ መንፈሳዊ ዕድገት በወግ የምናውቀውን እግዚአብሔር በግላችን በሕይወታችን ወደ ማወቅ መሸጋገር ነው።/ Spiritual growth is the gradual, I would say, transition from a God of tradition to a God of experience.” —ነቪል ጎዳርድ*

የጌታን ድምጽ ሰምቶ መራመድ ስኬታማ እንደሚያደርግ ምንም ጥርጥር የለውም። የጌታን ድምጽ ደግሞ በተለያዩ መንገዶች እንሰማለን። ለምሳሌ ቃሉን ስናነብ፣ ስንጸልይ፣ ከነቢያት፣ ከአስተማሪዎች እና ከሰባኪዎች መልእክቶችን ስንሰማ፣ በሕልም ወዘተ። በሕይወታችን የጌታ ምሪት እንዲበዛ፣ ከእርሱ ጋር ያለን ኅብረት እያደገና እየጠለቀ መምጣት አለበት። ለዚህ ስኬት ደግሞ በእግሩ ሥር መገኘትና ከቃሉ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መፍጠሩ ምርጫ ያለው ጉዳይ አይደለም።

በዚህ ረገድ የእግዚአብሔር ቃል *“ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የ እግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።”* (ሮሜ.12፥1-2) የሚለን ያለ እንደዚህ ዓይነት መሥዋዕትነት መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት እንደማንችል ሊነግረን ፈልጎ ነው፡፡

የጌታን ድምጽ ሰምቶ ስለመራመድና በመንገዱ መሄድ

ስላለው በረከትና ጥቅም መዝሙር 81፥13-16 ግሩም ምንባብ ነው ብዬ አስባለሁ።

በግሌ ይህ ክፍል ያስደንቀኛል። ከዚህ ቃል አንጻር ሕይወቴን ሳየው እጅግ አዝናለሁ። የእግዚአብሔር ቃል ትእዛዝ አለው፤ በመታዘዝ ቃሉን ስንተገብር ደግሞ የሚመጣ በረከት አለ። ይህ ምንባብ ስለዚያ ነው የሚያስተምረን። ክፍሉ እንዲህ ይላልና፡- *"ሕዝቤስ ሰምቶኝ ቢሆን፣ እስራኤልም በመንገዴ ሄደው ቢሆን፤ ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባዋረድኋቸው ነበር፤በሚያስጨንቋቸውም ላይ እጄን በጣልሁ ነበር፤ የእግዚአብሔር ጠላቶችም በተገዙለት ነበር፤ ዘመናቸውም ለዘላለም በሆነ ነበር፤ ከስንዴም ስብ ባበላቸው ነበር፤ከዓለቱም ማር ባጠገባቸው ነበር።"*

ከላይ የጠቀስኩት ቃል ላይ ትእዛዞቹ ሁለት ናቸው፡-

- ሕዝቤ ሰምቶኝ ቢሆን፤
- እስራኤል በመንገዴ ሄደው ቢሆን።

ትእዛዞቹን በእግዚአብሔር ጸጋ ስንተገብር፣ ወደ ሕይወታችን የሚመጡ በረከቶችን በራሴ አተያይ ጠቅለል አድርጌ በሦስት ነጥቦች አስቀምጫቸዋለሁ፡-

1. የጠላቶቻችን መሸነፍና መዋረድ፤
2. ዘለቄታዊነት ያለው ጤናማ መንፈሳዊ ሕይወት፤

3.ከጌታ ጋር ከሚኖረን ኅብረት የተነሣ፣ የምናገኘው አእምሮን የሚያልፍ

መንፈሳዊ ጉብኝት (ከዐለቱ ማር መጥገባችንና ከስንዴው ስብ መብላታችን የሚለው ሐሳብ ያንን ነው የሚያሳየው)።

ይሄ ቃል ልካችን (this is our standard) ነውና ወደዚህ ቃል ልክ ለማደግና፣ ድምፁን በመስማት የሚገኘውን በረከት ለመካፈል፣ ቃሉን መብላት፣ ማሰላሰል እናም ባልተከፋፈለ ልብ ማጥናት ያስፈልገናል። በተጨማሪም ጠበቅ ያሉ መንፈሳዊ ጸሎቶችን ማድረግ ይጠበቅብናል። አጣምረንም ጾምን መለማመድ በጣም ጠቃሚም ነው ብዬ አምናለሁ።

ከላይ ባለው አንቀጽ ላይ ያሉትን፣ ሦስቱን ተግባሮች በጌታ ጸጋ ያለማቋረጥ ብንተገብር እርግጠኛ ነኝ፣ ሕይወታችን ካሰብነው በላይ ይባረካል ያድጋልም። ጌታ ሆይ ድምፅህን ሰምተን እንድንራመድ እርዳን!

**መዝጊያ ምንባብ፦** *"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።"* (ዮሐ.10፥27-28)

# ከልብህ ኀዘንን አርቅ

*"እግዚአብሔር እኛ በእርሱ ስንረካ ይከብራል።/ God is most glorified in us when we are most satisfied in Him" —ጆን ፓይፐር*

ወደ ስምንት ዓመት ገደማ ይሆናል። በአንድ ከፍ ያለ የልብ ስብራት ውስጥ ሆኜ ለረጅም ጊዜ ቆዝሜ ነበር። ኀዘኔ ከበድ ያለ ስለ ነበር ከሰው ጋር መገናኘት፣ ማውራትና አብሮ መሆን እጅግ አስጠልቶኝ ነበር። በዚያ

ሁኔታ ውስጥ ሳለሁ የጌታ መንፈስ ደረሰልኝ ማለት እችላለሁ። አንድ ቃል በማልረሳው መንገድ በራልኝና ያለሁበትን ሁኔታ በትጋት እንድለውጥ አነሣሣኝ። የበራልኝም ሐሳብ፣ ያንን የነበርኩበትን ሁኔታ በእግዚአብሔር ጸጋ የማራገፍ ኃላፊነት የእኔ እንደ ነበር ነው። ሁኔታዬንም የለወጠው *"ከልብህ ኀዘንን አርቅ"* (መክብብ 11፥10) የሚለው ምንባብ ነበር።

ይህ ቃል በጊዜው ለእኔ መድኃኒቴ ነበር (ምሳ.25፥11) ማለት ይቻላል። አዝኜ የጨለማው መጫወቻ ሆኜ እያላዘንሁ መቀመጥ እንደሌለብኝ በምረዳው መንገድ ገባኝ። ከዚያም ከነበርሁበት ሁኔታ ለመውጣት፣ ጌታ ጠንከር ያሉ ጸሎቶችን በመያዝ ትግል መጀመር እንዳለብኝ አመለከተኝ።

በአጋጣሚ የምኖርበት ቤት አጠገብ አንድ የመሠረተ ክርስቶስ አጥቢያ ቤ/ክ ነበር። እዚያ በፈረቃ ግቢውን የሚጠብቁትን ሠራተኞች እያስፈቀድሁ በጣም ረጅም ሰዓታት ባዶ አዳራሽ ውስጥ መጮኽ ጀመርሁ። መጀመሪያ ይህንን ትግል ስጀምር ልክ ግምብ የመግፋት ያህል ይሰማኝ ነበር። ሆኖም ግን የሚሰማኝ ስሜት ሳይበግረኝ የጸሎት ግብግቡን ቀጠልሁ።

በመኻል በመኻል አንዳንዴ ካለሁበት ሁኔታ ጋር የሚሄዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እያጠናሁና እያሰላሰልሁ፣ ከዚያ ደግሞ ቀጥዬ በመቃተትና የጌታ መንፈስ እንዲረዳኝ በመማጸን፣ ሳልፈወስ ከምሽጌ ላልወጣ ለራሴ ቃል ገባሁ። በርከት ላሉ ቀናት እንዲህ ባለ ሁኔታ ካሳለፍኩ በኋላ፣ ሁኔታው ሁሉ ተገልብጦ ሰላምና ደስታ በማያቋርጥ ሁኔታ በልቤ ውስጥ ይፈስ ጀመር። ዝማሬ፣ አምልኮ፣ ስግደትና ውዳሴ በሕይወቴ ተትረፈረፈ። ከዚያማ እየጸለይኩ ውዬ፣ ስለ ጌታ አውርቼና

አመስግኜ የማልረካበት ሕይወት ውስጥ ገባሁ።

ይቅርታ አድርጉልኝና ለተወሰኑ ቀናት እዚህ ምድር ላይ ሁሉ የምኖር አይመስለኝም ነበር። የእግዚአብሔር ሕልውና በሚገርም ሁኔታ እላዬ ላይ ነበር። ዕብደት የጀመረኝ እስኪመስለኝ ድረስ፣ ብቻዬን ሆኜ ማንም ሳያወራኝ ሳቅ ያስፈነድቀኝና ይፈነቅለኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል። በጥቅሉ የነበርኩበትን ሁኔታ በቃላት መግለጽ ያዳግተኛል። ያ የጌታ ጉብኝት እንደ መልሕቅ ነፍሴ ላይ ላይፈታ ታስሯል። ጉብኝቱ እጅግ ድንቅ ነበርና እንዴት ይረሳል?

የእግዚአብሔር ቃል *"....የዘላለም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል፤ ሐሤትንና ደስታን ያገኛሉ፣ ኀዘንና ትካዜም ይሸሻሉ።"* (ኢሳ.35፥10) ብሎ ይናገራል። በእኔም ሕይወት እንዲያ ነበር የሆነው:: ያ እንደ ቡልኮ የሸፈነኝ ኀዘንና ትካዜ የት አንደ ገባ እስሚገርመኝ ድረስ በሐሤት ተጥለቀለቅሁ። አሁን *"በዚያም ቀን ሸክሙ ከጫንቃህ ቀንበሩም ከአንገትህ ይወርዳል ቀንበሩም ከውፍረት የተነሣ ይሰበራል።"* (ኢሳ.10፥27) የሚለው ቃል በመጠኑም ቢሆን ይገባኛል።

ጠንከር ያሉና ጥልቅ የሆኑ ጸሎቶችን ገፍተንና ሳንታክት ስንጸልይ የእግዚአብሔር ኃይል በውስጣችን እየጨመረ ስለሚሄድ፣ ማንኛውንም አዚም ለመስበር የምንችልበትን አቅምና ጉልበት ስለምናገኝ ሕይወታችንን ይቀየራል። በጽኑነትና በቀጣይነት ሳንደክምና ሳንሰላች፣ በምንጸልየው ጸሎት ብዙ ድንቅ መለኮታዊ ነገሮችን እናያለን። ስለሆነም ከነካ ነካ የጸሎት ሕይወት ጌታ ወደ ጠለቀ ልምምድ እንዲከተን፣ ያለማቋረጥ ፊቱን እንሻ። እንዲህ ብናደርግ ጌታ አምላክ በእርግጠኝነት ያስደንቀናል!

**መዝጊያ ምንባብ፡-** *"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፍትላችሁማል። የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልግም ያገኛል፥ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል። አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን? ወይስ እንቍላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?"* (ሉቃ.11፥9-13)

# መፍትሔው

ጉልበት ሲከዳ መጸለይ ሲያቅት

ባዶነት ሲነግሥ ሲሞላ ጭንቀት

ያለፉት ጊዜያት የድል ምስጋና

ሁሉም ተረስተው ውስጥ ሆኖ ኦና

እጅግ ከባድ ነው ያሸማቅቃል

ያለ ሕልውናው ትርጉም አልባ ነው ምኑስ ይጥማል?

መፍትሔው ታዲያ ውል መድኃኒቱ

ባይጥም ባይመስል ጊዜን መውሰድ ነው ሆኖ በፊቱ

በቸርነቱ ዘንበል እስከሚል

ነፍስ አለምላሚ ኩልል ዘይቱን እስከሚያቀብል

ከውስጥ ፈንቅሎ ምስጋና                    እስኪፈልቅ

ልባችን ረክቶ በሐሤት ክብር እስኪጥለቀለቅ

ድካም በሕይወት ተውጦ እስክናይ

ያለንበቱ መስሎ እስኪታየን የምድር ሰማይ!

# የእግዚአብሔር ጉብኝት

*"ጸሎት መነቃቃትን ይወልዳል፣ መነቃቃት ደግሞ የጨመረ ጸሎትን ይወልዳል።/ Prayer begets Revival, which begets more prayer.."-ጂም ሲምባላ*

መነቃቃት/ "Revival" ማለት በውጤት ደረጃ የሞተ ነገር ወደ ሕይወት መመለሱን ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ መነቃቃት ማለት በአጭሩ *"እግዚአብሔር ወደ ግለሰብ ወይም ወደ ጉባዔ መጣ"* ማለት ሊሆን ይችላል።

በትንቢተ ዕንባቆ መጽሐፍ *"እግዚአብሔር ከቴማን ቅዱሱም ከፋራን ይመጣል።"* (ዕን.3፥3) የሚለው ምንባብ በወደፊት ጊዜ ነው የተገለጸው። በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ግን *"God came..."* ብሎ በኀላፊ ጊዜ ነው ዓረፍተ ነገሩ የተጻፈው። ለዚህም ነው ዕንባቆ ምዕራፍ ሦስት ላይ ያለውን ክፍል፣ በመነቃቃት ዙሪያ የሚጽፉ የእግዚአብሔር ሰዎች አዘውትረው የሚጠቅሱት። ምዕራፉ ከቁጥር 4 ጀምሮ *"እግዚአብሔር ሲመጣ (በሕዝቦች መኻል ሲገኝ)"* የሚሆኑ ድንቅ ክስተቶችን እስከ ቁጥር 16 ድረስ በስፋት ይዘረዝራል (እናንተ በግላችሁ ሙሉውን በሚገባ

አንብቡት)።

እግዚአብሔር በክብሩ ሲገለጥ ሊታዩ የሚችሉ ክስተቶችንና መንፈሳዊ ለውጦችን ቃሉ፣ *“ቆመ ምድርንም አወካት፤ ተመለከተ አሕዛብን አናወጠ፤ የዘላለም ተራሮች ተቀጠቀጡ፤ የዘላለም ኮረብቶች ቀለጡ፤ በቃልህ እንደማልህ መቅሰፍትን አወጣህ ቀስትንም ገተርህ ምድርንም ሰንጥቀህ ፈሳሾችን አወጣህ፤ ተራሮች አንተን አይተው ተጨነቁ፤ ፍላጾችህ ከወጡበት ብርሃን የተነሣ ከሚንቦገቦገውም ከጦርህ ፀዳል የተነሣ ፀሐይና ጨረቃ በመኖሪያቸው ቆሙ፤ በምድር ላይ በመዓትህ ተራመድህ አሕዛብን በቁጣ አሄድሃቸው፤ የኃጢአተኛውን ቤት ራስ ቀጠቀጥህ መሠረቱን እስከ አንገቱ ገለጥህ፤ የአለቆችን ራስ በገዛ በትራቸው ወጋህ፤ ፈረሶችህን በባሕር፣ በብዙ ውኆችም ላይ አስረገጥግህ።”* እያለ በሚገርም አገላለጽ አስፍሯቸዋል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ክስተቶች ጠቅለል ባለ ሐሳብ ለመግለጽ ያህል፣ እግዚአብሔር በክብሩ ሲገለጽ፡-

- በፊቱ የሚቆም አይኖርም፤ ፍጥረት ሁሉ ይንበረከካል፤
- የሠይጣን ሠራዊትና አጋንንቶች መግቢያ ያጣሉ፤
- የተሰወሩ ነገሮች ሁሉ ይገለጣሉ፤
- ብዙ ለውጦችና ንውጥውጦች ይስተዋላሉ።

ዕንባቆ በዚህ ክፍል፣ እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ እንደሚመጣ በመንፈሱ አስተውሎ፣ *“እኔ ሰምቻለሁ ልቤም ደነገጠብኝ ከድምፁ፣ የተነሣ ከንፈሮቼ ተንቀጠቀጡ፤ መንቀጥቀጥ ወደ አጥንቶቼ ውስጥ ገባ*

*በሰፍራዬ ሆኜ ተናወጥሁ።"* (ዕን.3፥16) ብሎ ተናግሯል።

ልክ እኮ ነው፣ የእግዚአብሔር መገለጥ እጅግ ያስፈራል እኮ! እግዚአብሔር በክብሩ በሰዎች መኻል ሲገኝ፣ ብዙ መንፈሳዊ ነውጦች እንደሚከሰቱ ከላይ ጀምሮ ያሉት ሥዕላዊ አገላለጾቹ ያሳዩናልና። የእግዚአብሔር መንፈስ ወርዶብኝ ከንፈሬ ተንቀጥቅጦና መናገር አቅቶኝ ያውቃል። ለአገልግሎት መድረክ ላይ ወጥቼ ለተወሰነ ደቂቃ መስበክ እና ቃል ማውጣት አቅቶኝ ያውቃል። ስለዚህ ይህ አገላለጽ በትንሹም ቢሆን ይገባኛል።

በመዝሙር 68፥1-35 እግዚአብሔር ሲነሣ ወይም ክብሩን በሰዎች መኻል ሲገልጥ፣ የሚሆኑና የሚታዩ ድንቅ ነገሮች በስፋት ይዟል። ይህ ክፍል ሲጀምር፣ *"እግዚአብሔር ይነሣ"* ብሎ ነው የሚጀምረው። እናም እግዚአብሔር በክብሩ ሲገኝ የሚታዩ ነገሮችን ከዚህ ምንባብ አለፍ አለፍ ብዬ እዘረዝራለሁ (የራሴን አገላለጾች አልፎ አልፎ እንድጠቀም ይፈቀድልኝ)፡-

- ጠላቶቹ መግቢያ ነው የሚያጡት፤ ሰም በእሳት እንደሚቀልጥ ይቀልጣሉ፤ ጢስ እንደሚበንን ይበናሉ፤
- ጻድቃን በእርሱ ፊት ሐሤት ያደርጋሉ በኃይልም ደስ ይላቸዋል፤
- እስረኞች ከተጠፈነጉበት (እንደ ሱስ ካሉ) ወኅኒዎች ይፈታሉ፤
- ምድር ትናወጣለች ሰማያት ያንጠባጥባሉ (የቃሉንና የመንፈሱ በሕዝብ መኻል መዝነብን ነው የሚያሳየን)፤
- የደከሙ ይበረታሉ፣ ይጽናናሉ፣ ይጸናሉም፤

- እግዚአብሔር ቃሉን ይሰጣል (የጠፋው ቃል ይገኛል) ብሎም ብዙ እንቆቅልሾች ይፈታሉ፤
- በቤት የምትኖር ምንም ተሳትፎ ያልነበራት ሴት እንኳን ምርኮ ተካፈለች ይላል (የሚመጣውን የበረከት ሰፊነት ነው የሚያመለክተን)፤
- ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይቀበላሉ (የጸጋ ስጦታዎችን)፤
- ብዙ ሰዎች ከብዙ ጉድ ይድናሉ፣ ይወጣሉም (ከሞት መውጣትም በእግዚአብሔር ነው የሚለው ይህንን ያመለክታል)፤
- ኃይል ያለው ቃል፣ የሚፈታ፣ የሚፈውስ ቃል ይለቀቃል፤
- ብዙ ሰዎች ኃይልንና ብርታትን ይቀበላሉ፤
- ጸሎት ይበዛል ወይም ጸሎት የጉባዔዎች መገለጫ ይሆናል (ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው ይህንን ይጠቁማል)።

ወገኖቼ የእግዚአብሔር መገኘት ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ይዞ ይመጣልና፣ እጅግ የሚያጓጓ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ትልቅ ሊስተዋል የሚገባው ነገር፣ የእግዚአብሔርን በጉባዔና በሕዝብ መካከል መገለጥ ሰው ሊያቅደውና ሊያደራጀው አይችልም። ቢሆንም ክርስቲያን ወገኖች የሚከተሉትን ሁለት ግሩም መርሖዎች በልባቸው በመጠበቅ፣ በእነርሱ በኩል ማድረግ የሚገባቸውን ነገሮች እያደረጉ መጠበቅ አለባቸው የሚል አስተሳሰብ አለኝ። እነዚህ ሁለት መርሖዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1.የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት (God's sovernity):-ጌታችን ይህንን ዓይነት

ክስተት በወደደው ሰዓት ያደርጋል፤

2.የሰው ኀላፊነት (man's responsibility):-ሰው ይህ ክስተት መቼ እንደሚመጣ ባያውቅም፣ በብዙ ናፍቆትና በጋለ ጸሎት እየተጋ መጠበቅ አለበት።

የእግዚአብሔር ጉብኝት ወደ እኛ እንዲመጣ ልንኮተኩታቸው የሚገቡ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1.ከልብ የሆነ እውነተኛ መመለስ ያስፈልገናል (2ዜና.7፥13-15 ያንበቡ)፡-ይህንን ቃል ቢል ብራይት የሚባሉ የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ብለውታል፡-*«the final and finished formula for revival»*።

2.መንፈሳዊ ጥማትና ራብ (ማቴ.5፥6)፡-አንድ ሰው በመነቃቃት ዙሪያ የጻፉት ጽሑፍ ላይ የማልረሳው ድንቅ ሁለት ነገሮች በልቤ ተጽፈው ቀርተዋል–«fasting and feasting»። ትርጉማቸውም መጾምና የእግዚአብሔርን ቃል በብዛት መመገብ ነው። ሰውየውም እነዚህ ሁለት ርምጃዎች መንፈሳዊ ጥማትንና ራብን ያቀጣጥላሉ ብለው ነው ጽሑፉ ላይ የሚያስገነዝቡት።

3.ዊሊያም ቡዝ የሚባሉ ትልቅ የእግዚአብሔር ሰው፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በቤተ ክርስትያኑ ለውጥ አጥቶ ሲያማክራቸው፣ *«try tears/ እስቲ እንባን ሞክር»* ብለውታል። ይህ አባባል ባሰብኩት ቁጥር እንዴት እንደሚነካኝ አትጠይቁኝ። እንባ ደረቀብን እንጂ መፍትሔው በጌታ ፊት አብዘተን በቅን ልብ መጮኽ እንደ ሆነ ምንም አያጠያይቅም።

ቅዱስ ቃሉ *"የሚያስተውል እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ*

*እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ።"* (መዝ.14፥2) እንደሚል፣ የክብር ጌታ መሰጠታችንን አይቶ እንዲራራ እሱው ነው መደረግ ያለበት። በመገኘቱ እንዲባርከንና እንዲያስደንቀን ለዚህ ለከበረ ነገር ዋጋ የሚከፍሉ ትጉሕ የሆኑና የጸሎት ምስጢር የገባቸው፣ *"አቤቱ፥ ጸሎቴን ስማ፥ ጩኸቴንም አድምጥ፥ ልቅሶዬንም ቸል አትበለኝ፡፡"* (መዝ.39፥12) እያሉ ለቤተ ክርስቲያን መነሣት የሚያነቡ ሰዎች እጅግ በጣም ያስፈልጋሉ።

4.የተሰበረ ልብ (ኢሳ.57፥14-15)፡-እግዚአብሔር የልብ መሰበርንና ትሕትናን ስለሚወድድ፣ በፊቱ ባዶነታችንና ያለ እርሱ ምንም ማድረግ የማንችል መሆናችንን ዕውቅና መስጠት ይገባናል። እርሱ ከእኛ የሚፈልገው ከልብ በሚመነጭ ፍርሃትና ትሕትና ውስጣችንን ዘክዝክን እንድናሳየው ነው። *"እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፤ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።"* (መዝ.34፥18) የሚል ትልቅ ተስፋ ስላልን፣ የልብ መሰበር በሕይወታችን እንዲመጣ በፊቱ በትሕትና አዘውትረን መቅረብ አለብን። "እነሆ፣ አግዘኝ፣ አንሣኝ" ማለት ይኖርብናል።

ለመሆኑ እንዲያ በልብ መሰበር የሚጠብቁትን ሰዎችን እግዚአብሔር ምን ያደርጋቸዋል? ከላይ የጠቀስሁት ቃል እንደሚናገረው፣ *"ያድናቸዋል"* ። ማለትም የባርኮቱ እሽግ (package) ብዙ ነገሮችን ይዞ ነው የሚመጣው ለማለት ነው!

በመጨረሻም የእግዚአብሔር ጉብኝት ሲመጣ ከሚታዩ ለውጦች መካከል የሚከተሉትን በዋናነት መጠቀስ ይችላሉ፡-

- በቤተ ክርስቲያን ኃይል ይጨምራል፤
- ቤተ ክርስቲያን ትጠራለች፤
- ቅድስና የሕይወት መሠረት ይሆናል፤
- ንጹሕ መለኮታዊ ፍቅር በአማኞች መካከል መታየት ይጀምራል፤
- ቤ/ክ በውጭው ዓለም ማኅበራዊ ተጽዕኖን ማምጣት ትጀምራለች።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ጉብኝትና መልካሚቱ እጁ በትውልዳችን መካከል መጥታ ክብሩን እንድናይ፣ ያለማሰለስና ያለመታከት እንጸልይ! በብዙ ንስሓና የልብ መሰበር እንፈልገው!

**መዝጊያ ምንባብ፡-***"አቤቱ፥ ትመለሳለህ ታድነንማለህ፤ ሕዝቡም በአንተ ደስ ይላቸዋል።"* (መዝ.85፥6)

# በመንፈስ የመጸለይ ጥቅም

*"በጸሎት ጊዜ ቃሉ ኖሮን ውስጣችን ባዶ ከሚሆን ይልቅ፣ ምንም ቃላት ሳይኖረን ልባችን መነካቱ ይሻላል።/ In prayer it is better to have a heart without words than words without a heart." — ጆን ቡንያን*

በጭንቀት፣ በኀዘን ውስጥ፣ ወይም ግራ በሚገባ ሁኔታ ውስጥ ሆነን እንዴት እንደምንጸልይ አናውቅም። አንዳንዴም የምናወጣቸው ቃላቶች ልንጸልይ የምንፈልገውን መግለጽ ሊያቅታቸው ይችላል። ቃላት

ጸሎታችንን መግለጽ ሲያቅታቸው፣ ትግሉን አቁመን፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ብንደገፍና መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን ብንፈቅድለት፣ ከፍ ያለ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ጸሎት መጸለይ እንችላለን (ሮሜ.8፥26-27) ።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሐና የጸሎት ግሥገሣ ሲመሰክር፣ *"ሐናም በልብዋ ትናገር ነበር፤ ድምፅዋም ሳይሰማ ከንፈርዋን ታንቀሳቅስ ነበር፤ ዔሊም እንደ ሰከረች ቈጠራት። ዔሊም 'ስካርሽ እስከ መቼ ነው? የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው' አላት። ሐናም 'ጌታዬ ሆይ፥ አይደለም፥ እኔስ ልብዋ ያዘነባት ሴት ነኝ፤ ጠጅና ሌላ የሚያሰክር ነገር አልጠጣሁም፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ነፍሴን አፈሰስሁ፡፡"* (1ሳሙ.1፥13-15) ብሎ ይናገራል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ሐና በውስጥ በመንፈሷ በመቃተት እንደ ጸለየች ይስማማሉ። ከሩቅ ሲታይ የሐና ከንፈር እየተንቀሳቀሰ የነበረ ቢሆንም፣ ነገር ግን ድምጽዋ አይሰማም ነበር። ስለዚህም ነበር ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ኤሊ ተሳስቶ ጠጥታ የሰከረች የመሰለው። እርሷ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት፣ የጠለቀ ጸሎት ውስጥ ነበረች፤ ነፍሷንም በአምላኳ ፊት አፈሰሰች። የተሰማም ጸሎት ጸለየች!

በሳሙኤል መጽሐፍ ላይ እንደምንረዳው፣ የሐና ችግር እጅግ ከባድ ነበር። ጣውንቷ ታበሳጫት ስለ ነበር፣ አዘውትራ ታለቅስ ነበር፤ አንዳችም አትቀምስም ነበር (በጾም ላይ እንደ ነበረች አምናለሁ)። አዎ፣ ሐና ከበድ ባለ ጭንቀት ውስጥ ስለ ነበረች፣ በመንፈስ ታምጥና ትቃትት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸለየችው ብርቱ ጸሎት ሲመሰክር፣ "እርስዋም በልብዋ ትመረር ነበር፤ በእግዚአብሔር ፊት ጸለየች፤ ጽኑ ልቅሶም

አለቀሰች።” (1ሳሙ.1፥10) ብሎ ነው የሚናገረው። ጽኑ ልቅሶ!

ሐና እየደረሰባት ከነበረው የመሃንነት ፈተና የተነሣ ምሬት ውስጥ ነበረች። ስለዚህም እግዚአብሔርን በጽኑ ፈለገችው። በመንፈስ ብርቱ ጸሎትን ጸለየች። ሳትታክት በጌታዋ ፊት ተጋች። ትልቅ ዋጋን ከፍላ ነበርና ያገኘችው ፍሬም ቀላል አልነበረም። ስለዚህም በዘመኑ በቃልና በሥራ ብርቱ የነበረውን ነቢዩ ሳሙኤልን ወለደች።

እኛም አዳጋች ነገሮች ሲገጥሙን፣ በሰዋዊ ዘዴዎች ለመፍታት ከመሞከር፣ አቋራጭ መንገዶችን ከመፈለግና በሥጋችን ከመፍጨርጨር ይልቅ በእርሱ ፊት መውደቁ ነው የሚበጀን። ከላይ እንዳየነው ሐና መፍትሔው እግዚአብሔር ጋ እንደ ሆነ በሚገባ ስለተረዳች፣ ጌታን ሙጭጭ ብላ ያዘች። እኛም እጅ ወደ ላይ ብለን፣ ወደ ጸጋው ዙፋን መጥተን፣ በመንፈስ ብንጸልይና ረዘም ላሉ ሰዓታት በጌታ ፊት ወድቀን ብንቃትት፣ ጸሎቱ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚያገናኘን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነን ጸሎት እንጸልያለን።

ያስጨንቁንም ችግሮች በእግዚአብሔር ክንድ ይንከባለላሉ። በጌታ ጊዜም ብዙ ፍሬዎችን እናጭዳለን። እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ መንፈሳዊ ድሎች ሲበዙልን ደግሞ፣ የበለጠ ወደ ጌታ እየተጠጋን እንሄዳለን። በሂደት በምናገኘው መንፈሳዊ ለውጥም፣ ለብዙዎች ከሩቅ ሳይቀር የሚነበብ ግሩም ምስክር እንሆናለን።

እግዚአብሔር ሆይ እባክህ የጸሎትን ሚስጥር ግለጥልን!

*መዝጊያ ምንባብ፡- “እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤*

*እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።"* (ሮሜ.8፥26-27)

## የምጥ (የጣር) ጸሎት (Travailing Prayer)

*"እግዚአብሔርን የመፈለግ ምስጢሩ (ፈላጊው እኛ ብንሆንም) የሚያገኘን እርሱ መሆኑ ነው።/ The mystery of seeking God is that HE is the One who finds you." — ኪንግስሊ ማኑኤል*

የምጥ ጸሎት በተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ምሪቶችና መረዳቶች የሚከናወን ጸሎት ነው። ይህንን የጸሎት ዓይነት ብዙ ጊዜ ከፊት ለፊት ተግዳሮቶች፣ መከራዎች እና ልብን የሚሰብሩ ክስተቶች በሕይወታችን ሲያልፉ ልንጸልየው እንችላለን። ይህ ጸሎት ለአጭር ጊዜ ብቻ ሊጸለይ ይችላል፤ ወይም ረዘም ላሉ ቀናት እየተጸለየ ሊቆይ ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ የጸሎት ሸክሙ መንፈሳችን ውስጥ እስካለ ድረስ አያሳርፈንም። እኛም በውስጣችን መለቀቅ እስኪመጣ አናቆመውም።

ፍሬውና በረከቱ ደስ ቢያሰኝም የምጥ ጸሎት ሕመም አለው። ለምሳሌ ነቢዩ ኢሳይያስ ከባድና አስደንጋጭ መንፈሳዊ መልዕክት ሰምቶ የጸለየው የምጥ ጸሎት ያስደንቀኛል። ቅዱስ ቃሉ የነበረበትን ሁኔታ *"...ስለዚህ ወገቤ ሕመም ተሞላ እንደምትወልድ ሴት ምጥ ያዘኝ፤ ከሕመሜ የተነሣ አላይም። ልቤ ተንበደበደ ድንጋጤ አስፈራኝ ተስፋ ያደረግሁት*

*ድንግዝግዝታ መንቀጥቀጥ ሆነብኝ።”* (ኢሳ.21፥8) በማለት ይገልጸዋል። የሚገርም ሁኔታ ውስጥ እንደ ነበረ ምንም አያጠያይቅም።

ብዙ ጊዜ ሰዎች እንዲህ ዓይነትን ጸሎት ሲጸልዩ በጉልበታቸው ተንበርክከው ልክ እንደምትወልድ ሴት እያማጡና እየቃተቱ ለብዙ ሰዓታት ይጸልያሉ። እንዲህ ዓይነት ጸሎት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጠለቀ መንገድ በመተባበር የሚጸለይ ጸሎት ስለሆነ፣ ብዙ ድንቅ ነገሮችን እናይበታለን የሚል እምነት አለኝ። ይህንን ጸሎት ለብዙ ለተለያዩ ጉዳዮች ልንጸልየው እንችላለን። ለምሳሌ ለነፍሶች መዳን፣ ለቤ/ክ ማደግ፣ ከተለያዩ አደገኛ ሁኔታዎች ለማምለጥ፣ ከምንታገልባቸው ኃጢአቶች ለመውጣት ወዘተ።

እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቤ/ክ መወለድና ማደግ በእኩል ሁኔታ ያማጠ ሰው በምድር ላይ ያለ አይመስለኝም። ጳውሎስ እንዲህ ዓይነት ጸሎት ውስጥ ያሳልፍ እንደ ነበረ፣ *”ልጆቼ ሆይ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሳል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል።”* (ገላትያ 4፥19) የሚለው አገላለጹ ይጠቁመናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን የካደና የክርስቶስ ልብ የነበረው ሰው እንደ ነበር የጻፋቸው መልዕክቶች ከበቂ በላይ ይናገራሉ። በዚህ ዓይነት ጸሎት ውሎ የሚያድር የነበረ ሰው እንደ ነበረም ምንም ጥርጥር የለውም።

በእንዲህ ዓይነት ጸሎት የጌታን ፊት መፈለግ፣ ብዙ በረከቶች አሉት። ትልቁ በረከትም የቤተ ክርስቲያን ማደግ ነው። እራሳችንን በሰጠንበት ልክ እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት እየሰፋና እየጠለቀ፣ ማቆሚያ ወደሌለው መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ስለምንገባ ለብዙ ሰዎች በረከት እንሆናለን።

ዮሐንስ 16፥20-22 ኢየሱስ ካረገ በኋላ፣ እነዚያ 120 ክርስቲያኖች በሰገነት (upper room) ስላከናወኑት የጸሎት ምጥ የተነገረ ትንቢታዊ ቃል እንደ ሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ጌታ ኢየሱስ *"እናንተ ታለቅሳላችሁ ሙሾም (ከበድ ያለ ለቅሶ ነው) ታወጣላችሁ...እናንተም ታዝናላችሁ ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል....እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ ነገር ግን እንደገና እያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል...ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።"* ብሎ ነበርና!

*"ታለቅሳላችሁ ሙሾም ታወጣላችሁ"* የሚለው ሐረግ ከበድ ያለ የጸሎት ትንቅንቅ ላይ እንደ ነበሩ ይጠቁመናል። በእርግጥም የሚገርም የምጥ ጊዜ ውስጥ ነበሩ። በፍርሃት ተከብበው፣ የሚያደርጉት ጠፍቷቸው፣ በብዙ ጭንቀት ውስጥ ነበሩ። ከዚህም የተነሣ ልቅሶአቸው ልክ አልነበረውም። በኃይል አነቡ፤ ቃተቱም። እናም ታማኙ ጌታ ባልጠበቁት መንገድ ተገልጦ በመንፈስ ቅዱስ ጎበኛቸው፤ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችም አንበሸበሻቸው (የሐዋ.2)። ከዚያም የጸሎት መልስ በኋላ በማያባራ ሁኔታ፣ ለፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ በረከት እንደ ሆኑ እናውቃለን።

በእንዲህ ዓይነት ጸሎት የምናሳልፈው ጊዜ በጣም ከባድና የማያልፍ እስኪመስል ሊያስምጠንና ሊያስለቅሰን ይችላል። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ታማኝ ነውና፣ በባርኮቱ ሲመጣና ሲጎበኘን ሁለት ነገሮች ይፈጸማሉ፡-

- በሚዳሰስና ግር በማይል መልኩ እናየዋለን፤
- ለሰዎችም የሚኖረን ምስክርነት ግሩምና ጠንካራ ይሆናል።

በግሌ በእዚህ በዮሐንስ ላይ የተጠቀሰው ቃል መጨረሻ ላይ ያለው ተስፋ ነው የሚያስደንቀኝ፤ *"ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም"* የሚለው።

እንግሊዝኛው *“no one rob you of that joy”* ብሎ ይገልጸዋል። በሌላ አገላለጽ “ማንም ይህንን ደስታ ሊዘርፋችሁ ወይም ሊገፍፋችሁ አይችልም’ ማለት ነው። ለምን መሰላችሁ? እውነተኛ፣ ኃይለኛ፣ ከውስጥ ከጥልቁ ከመንፈሳችን የተቀዳ ደስታ ስለ ሆነ ነው። ጌታ ሆይ በእንደዚህ ዓይነት ጸሎት ባርከን!

**መዝጊያ ምንባብ፡-** *“አቤቱ፥ በመከራ ጊዜ ፈለጉህ፥ በገሠጽሃቸውም ጊዜ ልመናቸውን ወደ አንተ አፈሰሱ። የፀነሰች ሴት ለመውለድ ስትቀርብ እንደምትጨነቅና በምጥ እንደምትጮኽ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ በፊትህ ሆነናል።”* (ኢሳ.26፥16-17)

# የጸሎት ጥልቀት (ተግባራዊ ርምጃ)

*“የተዘውታሪ ጸሎት ትልቁ ዋጋው እግዚአብሔር እኛን መስማቱ ሳይሆን፣ እኛ እርሱን መስማታችን ነው።/ The value of consistent prayer is not that [God] will hear us, but that we will hear Him.” —ዊሊያም ማክጊል*

የእግዚአብሔር ቃል *“ቀላይ ቀላይን ትጠራለች። Deep calls deep.” (መዝ.42፥7)* እንደሚል፣ ጸሎት በተዘወተረ ቁጥር እየጠለቀ ይሄዳል። ያ ይሆን ዘንድ ግን መሰጠት፣ ትዕግሥት፣ ትጋት፣ ቁርጠኝነትና ዲሲፕሊን ወሳኝ ናቸው። በሌላ በኩል የጸሎታችን ጥልቀት ከሚወስኑ ነገሮች አንዱ የጊዜው ርዝመት ነው። በዚህ መሥዋዕት ደግሞ ዋናው ደስ የሚሰኘው ጌታ ኢየሱስ ነው። መሰጠታችንን  እናሳየዋለንና!

ረዘም ያለ ጸሎትን አቅደን ስንነሣ፣ ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ በአእምሮ በመጸለይ ቢሆንም የምንጀምረው፣ በመንፈስ እንደምንጨርሰው በመተማመንና በጸሎታችንም ድንቅ ነገርን እንደምናይ ተስፋ በማድረግ በጌታ ፊት እንውደቅ። ቶሎ እንድናቋርጥ እና ወደ ሌሎች ጉዳዮች እንድንሄድ ወደ ነፍሳችን ግብዣዎች ይመጣሉና፣ እነዚህን መንፈስን የማያረጋጉ መልእክቶች ወደ ጎን በማድረግና በመጨከን በጸሎት እንገሥግሥ።

አንዳንድ ስለ ጸሎት የጻፉ መንፈሳዊ ሰዎች፣ ጸሎት ከሦስት በላይ እርከኖች (dimensions) እንዳሉት ይናገራሉ። እነርሱም፡-

1. የውጨኛው አደባባይ (the outer court)
2. መካከለኛው አደባባይ (the middle court)
3. ውስጠኛው አደባባይ (the inner court)

ብዙዎቻችን በጸሎት ጊዜያችን፣ *ውጨኛውን አደባባይ* ተሳልመንና የጌታን ጸጋ በሚገባ ሳንካፈልና በረከቱን ሳናይ ነው የምናቋርጠው፤ ምንም እንኳ ዲሲፕሊን እንደሚያስፈልገን ብናምንም። ለእዚህ መፍትሔው  የጌታን ጸጋ በሚገባ ሳንካፈል ከመሠዊያችን ላለመነሣት መወሰንና መጨከን ነው። ውሎ አድሮ ደጋግመን ስናደርገው ትግል መሆን ይቀራልና። ብዙ ጊዜ በውጨኛው አደባባይ የሚጸለዩ ጸሎቶች በአእምሮ የሚጸለዩና ራስ ተኮር ናቸው። ገና የእግዚአብሔር መንፈስ በሚገባ ስላልታወቀን ጸሎታችን ትግል ይበዛዋል። የአእምሮ አለመሰባሰብም አንዱ ዋና ፈተናችን ነው።

*መካከለኛው አደባባይ* የጌታ ሕልውና/ አብሮነት ይታወቀናል፤ ለቀጣይ ጸሎትም እንገፋፋለን። በዚህ ጊዜ *"ሳበን ካንተም በኋላ*

*እንሮጣለን”* (መጵ.4፥1) እያልን የጌታን ፊት በጋለ ጉጉት የምንፈልግበት የጸሎት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ላይ የረካንና የጌታን ጸጋ በሚገባ የተካፈልን መስሎን ተቻኩለን ከጸሎት ልናቋርጥ አንችላለን። ነገር ግን ጨክነን ከጸናን ወደ ሦስተኛው እርከን እንሻገራለን።

*ውስጠኛው አደባባይ* ብዙ ዝምታ የሚበዛበት፣ በመንፈስ የምንቅታትበትና እንባ ቋንቋችን የሚሆንበት የጸሎት ደረጃ ነው። በዚህ ጊዜ ሮሜ.8፥26-27 ተግባራዊ ይሆናል። ጥልቅ ጸሎት ስለምንጸልይም፣ ድንቅ ነገሮችን የምናይበት ጊዜ ነው። ጸሎቱም በውስጣችን የሚታተምና የማይረሳ ለውጥን ያመጣል። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለምንጸልይ ጸሎታችን በሚገባ ይሰማል የሚል እምነት አለኝ። ይህ የጸሎት ደረጃ በሕይወታችን ሲበዛም ዕድገትና ለውጣችን በዚያኑ መጠን ሰፊ ይሆናል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የጸሎት እርከኖች/ ደረጃዎች (dimensions) በሉቃስ 11፥9 በሌላ መንገድ ተገልጸዋል። እነርሱም እንዲህ ነው የተገለጹት፡-

1.መጠየቅ፡-የመጀመሪያው የጸሎት ደረጃ ነው። በዚህ ጊዜ በአእምሮአችን እንጸልያለን። የምንጸልያቸው ጸሎቶችም እንዲሆኑልን የምንፈልጋቸውን ጉዳዮች በአንደበታችን የምናሳውቅበት የጸሎት ደረጃ ሲሆን፣ ባብዛኛው ጸሎቶቻችንም በራሳችን ዙሪያ ያጠነጠኑ ናቸው።

2.መፈለግ፡-የጌታን ፊት ተጠናክረን የምንፈልግበት ጊዜ ሲሆን፣ በመጠኑም ቢሆን ጠንከር ያለና የጌታ ሕልውና እስኪሰማን (recognize) ድረስ የምንጸልየው ጸሎት ነው።

3.ማንኳኳት፡-በዚህ ጊዜ ወደ ጠለቀ ጸሎት ውስጥ ለመግባት እንቃትታለን። በዚህ ጊዜ መንፈሳችን በሚገባ ንቁ ስለሚሆን፣ አብረን ለመፍሰስ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በንቃት እንከተላለን። በዚህ የጸሎት ደረጃ የጌታን ድምፅ የምንሰማበት ዕድል ከፍ ያለ ነው። ጸሎታችንም እየጠለቀ ሲሄድ ምሥጋና፣ ንስሓና እንባ ተፈራራቂ ይሆናሉ። የጸሎቱ ጥልቀት እየጨመረ ሲሄድ ዝምታ ይበዛል። እናም በማይነገር መቃተት እንደ ጌታ ፈቃድ የምንጸልበትና የምንማልድበት ጊዜ ይሆንልናል።

በዚሁ በሉቃስ 11 ላይ ከጠቀስኩት ምንባብ ወረድ ብሎ *"የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ መዝጊያን ለሚያንኳኳውም ይከፈትለታል።"* (ቁ.10) የሚል ቃል እናገኛለን። እጅግ የሚገርም የተስፋ ቃል ነው። ይህ ክፍል በትንሹም ቢሆን፣ በጸሎት ሕይወቴ ሲሠራ አይቼዋለሁና ሁሌም የሚያስደንቀኝ ምንባብ ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚመራን ሆነን ድምጹን እየሰማን፣ እየታዘዝንና እጃችንን ይዞ እንዲመራን ከፈቀደልንለትና እርግት ብለን በቂ ጊዜ በፊቱ ከሆንን፣ ጸሎታችን እየጠለቀ ይሄዳል የሚል እምነት አለኝ። በአጭሩ ልንወስድ የሚገባን ተግባራዊ ርምጃዎች (የራሴን ልምድ ላካፍላችሁ፤ እናንተ ከእኔ የተሻሉ መንገዶች ሊኖሯችሁ ይችላል)፡-

- ብዙ ጊዜ የጠለቁ ጸሎቶችን እንዳንጸልይና የእግዚአብሔርን ሙሉ በረከት በጸሎት እንዳንቀበል የሚያደርገን የጠላት ተጽዕኖ ሊሆን ስለሚችል፣ በመንፈስ በመለየት በኃይል እየተቃወምን መጸለይ ይገባናል፤
- ወደ ጸሎታችን መጀመሪያ አካባቢ፣ የጸሎት መዝሙሮችን ከፍተን

መንፈሳችን እንዲነቃቃ፣ እንዲቀጣጠልና አእምሮአችን እንዲሰበሰብ ማድረግ ጥሩ ነው፤

- ሌላው በመኻል በመኻል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምንጸልይባቸው ሁኔታዎች ጋር የሚሄዱ ቃሎችን በማንበብና በጸሎት መንፈስ ሆነን በማሰላሰል የበለጠ መንፈሳችንን ለቀጣይ ጸሎት እንዲነሣሣ ማድረግ ይገባናል፤
- አእምሮአችን እንዳይሰባሰብ የሚያደርጉ በግል የምናውቃቸውን ነገሮች በውሳኔ ከአካባቢያችን ማራቅም (ለምሳሌ ሞባይላችንን ማጥፋት) ወሳኝ ነው።

ትልቁ ነገር ውሳኔ ነው። እኔ ቢሰማኝም ባይሰማኝም አልነሣም ከጸሎት ብዬ የምወስንባቸው ጊዜዎች አሉ። እንዳውም እንዳልጸልይ በከበደኝ ጊዜ ገፍቼ ብዙ ሰዓት በውሳኔ ስጸልይ፣ ካሰብሁት በላይ አስደናቂ ጊዜን አሳልፌ አውቃለሁ። ባብዛኛው በራሴ ሕይወት እንደማየው ጸሎታችንን እንድናቋርጥ ወደ አእምሮአችን የማይመጣ የፈተና ዓይነት የለም፤ ነገር ግን ተቁነጥንጠን ስንነሣ ያንኑ የምናውቀውን ሕይወትና ኑሮ ነው የምንቀጥለው። ከጌታ ጋር ግን ብናሳልፍ፣ ሕይወታችን እየተለወጠና የጌታ ጸጋ በሕይወታችን እያደገ ይመጣል።

ወገኖቼ እንዲያ ወስነን በጸሎት ካልተጋን በቀር፣ ልንመኝ፣ ልናስመስል እና ዝም ብሎ በባዶው ልንጓጓ እንችል ይሆናል እንጂ፣ በነካ ነካ ጸሎት የእግዚአብሔርን ክብርና ጉብኝት አናይም። ስለዚህ መልካሚቱ እጁ በመካከላችን እንድትበዛ በጸሎት እንጋደል! ጌታ ሆይ ከዳር ዳር ጸሎት እባክህ ክብርህን ወደምናይበት ጥልቅ ጸሎት ውስጥ ክተተን!

*መዝጊያ ምንባብ፡-“እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።”* (ያዕ.5፥16-18)

# እግዚአብሔር ይናገራል

*“በጸጥታ ውስጥ እግዚአብሔር ለልብ ይናገራል። በእግዚአብሔር ፊት በጸሎትና በጸጥታ ከሆንህ፣ እግዚአብሔር ይናገርሃል። ያኔ ኢ-ምንት መሆንህን ትረዳለህ። ያለ እርሱ የማትረባና የተራቆትህ መሆንህ ስታስተውል ብቻ ነው እርሱ በራሱ የሚሞላህ።” –ማዘር ተሬዛ*

የእግዚአብሔር ቃል በመዝሙር 19፥1-14 እግዚአብሔር በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ሊናገረን እንደሚችል ጽፎልናል፡-

1.በሚታየው ዓለም ባሉ ግዙፍና ድንቅ የእጁ ሥራዎቹ ይናገረናል።

*“ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይምም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል። ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፤ ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች። ነገር የለም መናገርም የለም ድምጻቸው አይሰማም። ድምጻቸውም ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።”* (መዝ.19፥1-4)

*“ሰማያት ቃል የላቸውም ግን ሰሚ ከተገኘ ድምጻቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ እያስተጋባ ነው።”* ብሏል አልርበት አንስታይን። *“the more I study science, the more I believe God/ ሳይንስን ብዙ ባጠናሁ ቁጥር፣ እግዚአብሔርን እንዳምን ተገድጃለሁ”* ብሎም ተናግሯል። በሌላ አገላለጽ *“ሰማያትን ባየሁና በተመራመርሁ ቁጥር የበለጠ ጌታን እንዳምነው እያደረጉኝ ነው”* ማለቱ ነው። ምክንያቱም ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር በሚገባ ሁኔታ እንዲናገሩ ሆነው ተፈጥረዋልና ነው።

2. መጽሐፍ ቅዱስን ገልጠን ስናነብ ይናገረናል።

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በትሕትና ቀርበን በሰከነ ሁኔታ ብናነበውና ብናጠናው ያስደንቀናል። ቃሉ *“በእውቀት ከከበረውና ካማረው ሀብት ሁሉ ጓዳዎች ይሞላሉ።”* (ምሳ.24፥4) ይላልና፣ ጊዜ ሰጥተን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ብናጠና አፍሰን የማንጨርሰው ዕውቀት ተዘጋጅቶልናል። የጌታን መንፈስ “እነሆኝ” ካልነው፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በታጨቁ ወርቃማ መልእክቶቹ ለነፍሳችን ይናገረናል። ጆሮአችንን አዘንብለን ድምፁን በርጋታ ከሰማን፣ የሰማነው መልእክት አካሄዳችንን በማስተካከል ፍጻሜያችንን ይቀይረዋል።

የሚያስፈልገን አንድ ነገር ብቻ ነው እንዲናገረን ፈቃደኛ መሆን። ልባችንን ከከፈትንለት፣ የሚገርም ለውጥ በውስጣችን ይከናወናልና። የእግዚአብሔር ቃል ሲናገረን ደግሞ ውጤት አለው፤ ሕይወታችንን የመቀየርና የማስዋብ ችሎታ አለው። ከላይ መግቢያ ላይ የጠቀስሁት ምንባብ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገረንና ወደ ውስጣችን ዘልቆ ሲገባ

ያሉትን ለውጦች በሚደንቅ ሁኔታ ዘርዝሯቸዋል፡-

- ነፍስን ይመልሳል /ነፍስን ከጥፋት ያስመልጣል/ (ቁ.7)፤
- ሕጻናትን ጠቢባን ያደርጋል፤ ብስለት ከፈለጋችሁ ወደዚህ ቃል መምጣት ነው፤ ከምትገምቱት በላይ ይቀይራችኋልና (ቁ.7)፤
- ልብን ደስ ያሰኛል (ቁ.8)፤
- ዓይንን ያበራል (መንፈሳዊውን ዓለም በቅጡ እንድንረዳውና ይህንን የክብር ጌታ እንድናየው ያደርጋል (ቁ.8)፤
- ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል (በምድራዊ ቋንቋ መግለጽ የማይቻል ሐሤትና ደስታ አለው (ቁ.10)፤
- የሰማነውን ቃል ስንጠብቀው፣ ብሎም በተግባር ስንተረጉመው በሁሉም የሕይወታችን አቅጣጫ ይጠቅመናል (ቁ.11)።

3. በመንፈሱ ለልባችን ይናገረናል።

በመዝሙር 19፥12-14 መዝሙረኛው በጸሎት ቋንቋና ተማጽኖ የሚገርም መንፈሳዊ ምስጢርን ይናገራል። *"ስሕተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ። የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ፤ የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ። አቤቱ ረድኤቴ መኃድኒቴም የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።"* ብሎ!

እዚህ ምንባብ ላይ ያለው ቃል እየተናገረ ያለው፣ መንፈስ ቅዱስ ውስጣችንን እየፈተሸና እየመረመረ በብርሃኑ ካልስታወቀን በስተቀር፣ ብዙ ከእኛ የተሰወሩ ጸያፍ ነገሮች በውስጣችን እንደሚኖሩ ነው። እዚህ ክፍል

ላይ የሚታዩ ሦስት የኃጢአት ዓይነቶች አሉ፡-

- የተሰወረ ኃጢአት፣
- የድፍረት ኃጢአት (‘ታላቁ ኃጢአት’ ተብሏል)፣
- ግብዝነት፣ ሽንገላናና አስመሳይነት (የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን የሚለው ይህንን ያሳየናል)።

እጅግ አስደንጋጩ ነገር ይህ ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ካላሳየንና ካልተናገረን ንጹሕ የሆንን መስሎ ልንታለልና ራሳችንን ልናታልል እንችላለን። ነገር ግን በጌታ ፊት ከምር ወድቀን፣ “እባክህ በልባችን ተሰውረው ያሉ አንተ የማትወዳቸውን እርሞችን አሳየን” ብለን በቅንነት ብንጮህ በሚገባን መንገድ ይናገረናል፣ ያሳየናልም። እነዚያን እርም የሆኑ ነገሮች፣ በመታዘዝ አንቅረን ስንተፋቸው ደግሞ ከእርሱ ጋር ያለን ኅብረት እየጠለቀ ይመጣል። እናም እየተቀደስን ከዓለም እየተለየን እንመጣለን፤ ትልቁ የጸሎት ትርፋችን ቅድስና ነውና!

ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት በቀጣይነት ተግተን ብንቀጥልና ከቃሉ ጋር ያለንን ቁርኝት ብናሰፋው፣ እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወታችን እየጨመረ ስለሚመጣ የድፍረት ኃጢአቶችን የመተው አቅም እናገኛለን። ከዚህም የተነሣ መንፈሳችን እጅግ ንቁ (sensitive) ስለሚሆን፣ እርሱን በየትኛው መልኩ መበደል እየከበደን ይመጣል ብዬ አስባለሁ። ይህ ሕይወት ሲቀጥልም፣ ለብዙዎች የሚታይ፣ የሚነበብ እና እርሱን የሚገልጥ እውነተኛ የክርስቶስ መልእክተኛ እንሆናለን።

ከላይ መግለጽ እንደሞከርኩት፣ ኢየሱስ ክርስቶስን አምነን እንደ ግል አዳኛችን የተቀበልን ሰዎች እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት

በሦስት መንገዶች ይናገረናል፡-

1. በሕሊናችን (through our conscience)

--------›የእግዚአብሔር መንፈስ ቀድመን ያነበብናቸውን ምንባባት ወደ ሕሊናችን በማምጣትና ድርጊቶቻችን እንድናመሳክር በማድረግ ይናገረናል፤ ደግሞም ስሕተቶቻችንን እንድናስተካክልና በራሱ መንገድም እንድንራመድ ያደርገናል።

2. በለሆሳስ ድምጽ (through subtle small voice)

--------›የእግዚአብሔር መንፈስ በተለያዩ የሕይወት ሁኔታዎች ስናልፍ አቅጣጫ ሊሰጠን፣ ሊያጽናናን፣ ሊያቀናን ወዘተ ኩልል ባለች ልብን በምታሳርፍ ድምጹ ለልባችን ይናገረናል።

3. ጮክ ባለ ድምጽ (authoritative voice of the Holy Spirit)

--------›መስመራችን ተንጋድዶ፣ እየሄድንበት ያለው መንገድ አደጋ ከሆነና አልሰማ ካልነው፣ ወይም መንታ በሆነ መንገድ ላይ ሆነን ስንቸገር፣ አንዳንዴ ጮክ ባለ ድምጽ ሊናገረን ይችላል። በግሌ ጌታ በዚህ መልኩ ተናግሮኝ ያውቃል። ሆኖም ግን ይኼኛው ሁልጊዜ የሚሆን ክስተት አይደለም።

የእግዚአብሔር ቃል ጌታ አምላክ *"በአንድም በሌላም ይናገራል ሰው ግን ኢያስተውልም።"* (ኢዮ.33፥14) ይላል። ይህ ቃል እውነት ነው። ሰው በአብዛኛው በእንቅልፍ ውስጥ ስላለ ነው እንጂ፣ እግዚአብሔር ያልተናገረበት ዘመን የለም። በዚህ ዘመን ደግሞ ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በኢየሱስ እየተናገረን ነው። ስለዚህ እባክህ ጌታ ሆይ ጆሮዬን

ከፈተው፣ ዓይኔን ግለጠው፣ መንፈሴን አንቃው እና ተናገረኝ ብሎ ወደ እርሱ መቅረብ ነው የሚያዋጣው። እርግጠኛ ነን ልባችን ከተዘጋጀና በሰከነ ሁኔታ በእግሩ ስር ከተቀመጥን፣ በሚገባን መንገድ ይናገረናል፣ ያሳርፈናልም።

***መዝጊያ ምንባብ፡-"ጌታም የጭንቀትን እንጀራና የመከራን ውኃ ቢሰጥህም አስተማሪህ እንግዲህ ከአንተ አይሰወርም፤ ዓይኖችህ ግን አስተማሪህን ያያሉ፥ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ። መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ።"*** (ኢሳ.30፥20-21)

# የምጥ (የጣር) ጸሎት በተግባር ደረጃ

*"ጸሎት ነገረ መለኮትን ወደ ልምምድ ይቀይረዋል።/ Prayer turns theology into experience."* ቲሞቲ ኬለር

ጌታ ኢየሱስ *"አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝ ግባ መዝጊያን ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህ በግልጽ ይከፍልሃል።"* (ማቴ.6፥6) ብሎ ተናግሯል። ይህ ምንባብ ለጸሎት እጅግ ትልቅ መርሕን የያዘ ነው። እልፍኛችን (our closet) ውስጥ ነው ሥራው ያለው። እዚያ ክፍላችን ውስጥ በፊቱ ሆነን ስናምጥ፣ በጸሎት ስንገሠግሥ፣ ስንቃትትና ስንተጋ የሚመጣ በረከት እንዳለም ምንባቡ ይጠቁመናል። ባርኮቱም *"በግልጽ ይከፍልሃል"* የሚለው ቃል ነው። እጅግ አስደናቂ ተስፋ ነው። ወገኖቼ ክፍያው ምን መሰላችሁ? አንዱ ትልቅ ክፍያ በስውር የሚያየንን አባታችንን በመንፈስ ማየታችን ነዋ! ከዚያማ ምሕረት፣ ጸጋ፣

ደስታና እረፍት ወዘተ ወደ ሕይወታችን ይመጣሉ። የምንጸልይበት ጉዳይም መልስ ያገኛል።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ጌታ ኢየሱስ የጸሎት ሕይወት ሲገልጽ፣ *"እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ።" (ዕብ.5፥7-8)።* ብሎ ይናገራል። *"ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ"* የሚለው አገላለጽ እጅግ አስደናቂ ነው። እውነተኛ ጸሎት ቀላል ሥራ እንዳልሆነ ነው የሚያስረዳው፤ የጣር ጸሎት ደግሞ ከጸሎት ዓይነት ሁሉ ከባድ መሆኑን ነው የሚናገረው።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ምጥ ጸሎት ውጤት ሲናገር፣ *"ጽዮን እንዳማጠች ልጆችን ወልዳለችና በውኑ ወደ መውለድ የማደርስ እኔ አላስወልድምን? የማስወልድስ ማኅፀንን እኔ እዘጋለሁን?" (ኢሳያስ 66፥8-9)* ይላል። በዚህ ክፍል ከብዙ ምጥ በኋላ መውለድ እንዳለ እናያለን። አዎ፣ ራእይ ያላቸውና የሚያምጡ ሰዎች በጌታ ጊዜ ጠንካራ ለትውልድ የሚሆንን በረከት ይወልዳሉ። እኔም በግሌ በምጥ ጸሎት ብዙ ነገሮች ሲወለዱ አይቻለሁ።

በዚህ ኢሳይያስ ላይ ባለው ክፍል ጌታ እግዚአብሔር *"ራእይ ሰጥቼ ወደ ፍጻሜ አላመጣውምን?"* እያለ እያንዳንዳችንን የሚጠይቀን ይመስለኛል። እርግጥ ታማኝ ነውና የተረገዙ ነገሮች በእርሱ ጊዜ ይወለዳሉ። እኛ ከስስት የራቀና ከራስ ወዳድነት የተፋታ ሕይወት ይኑረን እንጂ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ሐሳብ ይውረሰን እንጂ፣ እግዚአብሔር ነገሮችን በጊዜው ውብ

አድርጎ ያሳየናል፤ ሊረዳን፣ ሊደግፈንና ሊመራን አብሮን ነውና!

- ስለዚህ የከበደንን ሁኔታ ስም ሰጥተነው ወደ ጌታ እንቅረብ (let us be specific)፤
- ለጸሎት የሚመች ቦታ መርጠን ክፍላችንን እንዝጋ (የሚረብሹንን እንደ ሞባይል የመሰሳሉ ነገሮችን ዘግተን)፤
- ጸሎትን ብዙ ጊዜ በአእምሮ ብንጀምርም ጸሎቱ እየጠለቀ ሲመጣ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር እንሆናለን። ስለዚህ ለጊዜው የሚሰማን ነገር ባይኖርም እንኳ፣ በእምነት ከጸሎት ቦታችን ሳንነሣ በጽናት ረዘም ላለ ጊዜ እንቀጥል፤
- መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራን ለመሆን መንፈሳችንን እናንቃ። ነፍሳችንን በፊቱ እናፍስስ። ማልቀስ ካለብን እናልቅስ፤ መዘመር ካለብን እንዘምር። ማለትም እንደሚመራን እንሁን፤
- በመኻል አእምሮአችንን እየተከፋፈለ ካስቸገረንና ጸሎት ላይ ትኩረት ማድረግ ካቃተን በኃይል እየተቃወምን እንጸልይ፤
- አእምሮአችን እንዲሰባሰብና በቀላሉ የጸሎት መንፈስ ውስጥ እንድንገባ ያደርገናልና፣ ለረጅም ጊዜ በልሳን መጸለይም ጥሩ ነው (እኔ ይህንን አብዝቼ አደርጋለሁ)፤
- በጽናት እየቀጠልን ስንመጣ፣ ቃሎቻችን እያነሱ በመቃተት እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሆነ፣ የጠለቀ ጸሎት መጸለይ እንጀምራለን፤
- መንፈስ ቅዱስ እየመራን የጠለቀ ጸሎት የመጸለይ

ደረጃ ላይ ስንደርስ፣ የምንጸልየው ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያለ ጸሎት ስለሚሆን ጸሎቱ የእግዚአብሔርን ልብ ያዘነብላል፤ ድንቅ ነገሮችንም እናይበታለን (ሮሜ.8፥26-27)።

እባክህ እግዚአብሔር ሆይ የጸሎትን ጸጋ አፍስስልን፤ የጸሎትንም ሚስጥር ግለጽልን!

**መዝጊያ ምንባብ፡-** *"ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና። እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን።"* (ሮሜ.8፥22-23)

## እኔን ደስ የሚለኝ

በጥላው ስር ስሆን መንፈሱ ሲያገኘኝ

ቃሉን ሳሰላስል ትንፋሹ ሲነካኝ

የመንፈስ ዝማሬ ሲመጣ ከሰማይ

ነፍሴ በምስጋና ባምልኮ ስትጋይ

ጠልቄ በጸሎት ጌትነቱ ገብቶኝ

በሚሰጠኝ ምሪት አብሮ መፍሰሴ ነው

እኔን ደስ የሚለኝ!

# መዝራት እና ማጨድ

*"የምታጭደውን መኸር ካልወደድኸው፣ የምትዘራውን መለወጥ ነው የሚሻልህ።/ If you don't like what you are reaping, you had better change what you have been sowing." ጂም ሮን*

የእግዚአብሔር ቃል *"አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት።"* ብሎ፣ ከዚያም የምንዘራው ዘር ሲጠቁመን፣ *"እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።"* (ገላ.6፥7-10) ብሎ ይናገራል። ሳይዘሩ ማጨድ የለምና!

መዝራት እና ማጨድ የተፈጥሮ ሕግጋት ናቸው። ሳንዘራና ዋጋ ሳንከፍል በፍጹም አናጭድም። ለምሳሌ ፍቅርን ሳንዘራ ፍቅርን አናጭድም። በዘፍጥረት መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል *"በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ ..........አያቋርጡም።"* (ዘፍ.8፥22) ብሎ ይናገራል። ትልቅ መርሕ ነው። በዚህች ምድር ስንኖር ይህ ሂደት በፍጹም አያቋርጥም።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ሊሰበን የሚያደርግልን አንዳንድ መልካም ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ መልካም ነገሮች ያለ እኛ ጥረት የምናገኛቸው ነገሮች ሲሆኑ፣ እርሱ ፍቅሩንና ቸርነቱን አሳይቶ ሊሰበን ሲፈልግ ይጠቀምባቸዋል። እነዚህ ሁኔታዎች ግን ሁልጊዜ የሚቀጥሉ ነገሮች

አይደሉም። በክርስትና ሕይወታችን ማጨድ ከፈለግን ያለ መታከት መዝራት ይኖርብናል። ለምሳሌ ቃሉን መስበክ፣ መጸለይ፣ ለሰዎች በጎ ማድረግ፣ ማስታረቅ ወዘተ የምንዘራቸው ነገሮች ናቸው። እነዚህ ዘሮች ደግሞ እንደ ወገኑ ፍሬን በጊዜው ያበቅላሉ። በሕይወታችን የእግዚአብሔር ቃል እንዲሠራና ፍጻሜያችን እንዲያምር ከፈለገን የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ላይ ያለ ማቋረጥ መዝራት አለብን። የተዘራው ቃል ተመችቶት እንዲበቅል ደግሞ በቅድስና መኖር፣ መጸለይ፣ ቃሉን ማሰላሰል እና ቃሉን ደጋግመን ማጥናት ይኖርብናል።

ከላይ ከጠቀስኳቸው ሐሳቦች ጋር የሚሄድና፣ ስለ መዝራት፣ መብቀል እና ማጨድ በሚገባ የሚያስረዳን ምንባብ፣ *"በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፤ እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማልም፡፡ ድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛለው ፍጹም ሰብል ታፈራለች። ፍሬ ግን ሲበስል መከር ደርሷልና ወዲያው ማጭድ ይልካል።"* (ማር.4፥26-29) የሚለው ነው።

ምድር ምሳሌያዊ (symbolic) ቋንቋ ሲሆን፣ ልብን ነው የሚወክለው። ልብ ላይ የሚዘራው ዘር ደግሞ የተወሰኑ ሂደቶች እንዳሉት ከቃሉ እንረዳለን። የእግዚአብሔር ቃል ውስጣችን ገብቶና ተመችቶት ሲያድግ ብዙ አስደናቂ ፍሬዎችን ያፈራል። አንድ አትክልት ፍጹም ሰብል ላይ ሲደርስ በውበቱ፣ በቁመቱና በሁለንተናው የሚያምር የደረሰ ተክልን እንደሚያሳይ ሁሉ፣ በውስጣችን በሚገባ ያደጉ የመንፈስ ፍሬዎች (ክርስትና ከውስጥ ወደ ውጭ ስለሆነ) ለሚመለከቱን ሁሉ የደመቀ መልእክት እንሆናለን ማለት ነው።

ይህ ሂደት ግን ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል እና ከቃሉ ጋር የተጣበቀ ሕይወትን ይጠይቀናል። *"እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ" (ቁ.27)* የሚለው አባባል የማብቀል እና የማሳደግ ብቃትና ችሎታ የሉዓላዊው የእግዚአብሔር እንጂ የሰው ጣልቃ ገብነት እና ችሎታ እንደሌለበት ነው የሚያስገነዝበን።

የምናፈራቸው ፍሬዎች የመንፈስ ፍሬዎች፣ የወንጌል *ሥራ* ፍሬዎች ወይም የበጎ *ሥራ* ፍሬዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በመጀመሪያ ከቃሉ የምናገኘው ውስጣዊ ለውጦችን ነው። የምናጭዳቸው ውስጣዊ ፍሬዎችም *"ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት"* (ገላ.5፥22-23) ናቸው። እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች በክርስትና ሕይወታችን ስኬታማ እንድንሆን እና የተጽዕኖ ሰዎች እንድንሆን ያደርጉናል። በእኔ ግምት ሌላም ተጨማሪ ነገር የሚያስፈልገን ሁሉ አይመስለኝም፤ እነርሱ ራሳቸው ከበቂ በላይ ናቸውና።

በመጨረሻም ስለ መዝራትና ስለ ማጨድ መግቢያ ላይ ያነሣሁትን ምንባብ ልድገመው፡- *"አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት።"* (ገላ.6፥7-9) የሚለውን።

ይህ ቃል በተግባር ደረጃ እየሠራነው ያለነውን ነገሮች እንድንፈትሽ ግድ ይለናል። እየሠራናቸው ያለነውም ነገሮች ከእነዚህ ከሚከተሉት ከሁለት ዕጣ ፈንታዎች አይወጡም፡-

- በሥጋ ስንዘራ--------›መበስበስን (ማለትም ኀፍረትን፣ ጭንቀትን፣ ጸጸትን፣ ሁከትን፣ ሕመምን፣ ድካምን፣ ስንፍናን ብሎም መንፈሳዊ ሞትን እናተርፋለን።)

- በመንፈስ ስንዘራ--------›የዘላለም ሕይወት (ማለትም ስኬትን፣ ዕረፍትን፣ መረጋጋትን፣ መጽናናትን፣ ተስፋን፣ ደስታን፣ ሰላምን፣ በረከትን ወዘተ እናጭዳለን።)

ስለዚህ ከቃሉ ምን እንማራለን? ዋናው ልንቀስም የሚገባን ትምህርት ውስጣችን የምንዘራው ዘር ላይ በሚገባ ልንጠነቀቅ እንደሚያስፈልገን ነው። ምክንያቱም የምንዘራው ዘር ነው ስኬታችንን፣ ምልልሳችንን፣ ተጽዕኖአችንን እና ፍጻሜያችንን የሚወስነው።

ሳናስተውል በሥጋ የምንዘራቸው ነገሮች የክርስትና ሩጫችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩበት፣ ከምንሄድበት ጉዞ በብዙ ልንዘገይ ስለምንችልና የለፋንባቸውንም ነገሮች ልናጣ ስለምንችል፣ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ማስተዋል ነው ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር የመርሕ አምላክ ስለሆነ፣ በሥጋ መጥፎ ነገሮችን እየዘራን በፍጹም መልካም ነገሮችን አንጠብቅ፤ ቅዱስ ቃሉ “ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ያጭዳል።” (ቁ.7) ይላልና!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*“በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፥ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም። በተነ፥ ለምስኪኖች ሰጠ፥ ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ እግዚአብሔር፥ ሁልጊዜ በነገር ሁሉ ብቃትን ሁሉ*

*አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ፥ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል።"* (2ቆሮ.9፥6-9)

# እግዚአብሔር ድምፅ

*"የተዘውታሪ ጸሎት ዋጋ እግዚአብሔር እኛን መስማቱ ሳይሆን፣ እኛ እርሱን መስማት መቻላችን ነው።/ The value of consistent prayer is not that [God] will hear us, but that we will hear Him."*
*— ዊሊያም ማክጊል*

ቃሉን በማሰላሰል፣ በማጥናትና በመጸለይ መንፈሳችን ንቁ ስናደርገው፣ እግዚአብሔር እርሱን ልንረዳው በምንችለው ሁኔታ ድምጹን ያሰማናል። የእግዚአብሔር ድምፅ ደግሞ፣ ወደ እኛ ለተለያዩ ዓላማዎች ማለትም አቅጣጫ ሊያሳየን ወይም ሊያስቀይረን፣ ተስፋ ሊሰጠን፣ እንደማይተወን ሊገልጽልን፣ ከፍ ያለ ተልዕኮ ሲኖረን ወዘተ ሊመጣ ይችላል።

የእግዚአብሔር ድምፅ ወደ ሕይወታችን ሲመጣ የሚከሰቱ ብዙ ለውጦች ይኖራሉ። ይህንን ሐሳብ በሚገባ የሚያብራራልን መዝሙር 29፥4-11 ላይ ያለው ቃል ሲሆን፣ የሚጀምረው *"የእግዚአብሔር ድምፅ በኃይል ነው፤ የእግዚአብሔር ድምፅ በታላቅ ክብር ነው።"* ብሎ ነው። ይህ አገላለጽ አዘውትረን ከምንሰማቸው ድምጾች፣ የእግዚአብሔር ድምፅ ለየት ያለ መሆኑን ያስገነዝበናል። የእግዚአብሔር ድምፅ ሲመጣም ብዙ ለውጦች ይከሰታሉ፡-

- አልቻል ያለን፣ ያስቸገረን ሁኔታና ባሕርይ ይለውጣል (ቁ.5)፤
- ደካሞችን በኃይል እንዲበረቱ ያደረጋል (ቁ.9)፤
- ወደ እኛ የሚመጣን የእሳት ነበልባል ይቆርጣል (ቁ.7)፤
- በሰላም ይባርከናል (ቁ.)፤
- ኃይል ይሰጠናል፣ ያጠነክረናል (ቁ.11)፤
- የተሰወረን ነገር ይገልጣል ወይም ወደ ብርሃን ያወጣል (ቁ.9)።

አዎ፣ የእግዚአብሔር ድምፅ ሲመጣ አስደናቂ ነው። በማንረሳው መልኩ በልባችን ታትሞ ይቀራል። አስተሳሰባችን፣ አካሄዳችን እና አመለካከታችን፣ ከዚያ ድምፅ በኋላ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ይቀየራል። እምነታችን ይጨምራል። ንስሓ የመግባትና የመመለስ ዐቅም እናገኛለን። በአጭሩ የሚመጣው ለውጥ ቀላል አይሆንም።

የዕንባቆም መጽሐፍ የእግዚአብሔር ድምጽን እንዴት መስማት እንደምንችል እና ማድረግ ስላለብን ነገሮች ጥሩ መርሕ አለው ብዬ አስባለሁ። የእግዚአብሔር ቃል *"በመጠበቂያዬ ላይ እቆማለሁ በአምባ ላይም እወጣለሁ የሚናገረኝንም ስለ ክርክሬም የምመልሰውን አውቅ ዘንድ እመለከታለሁ። እግዚአብሔርም መለሰልኝ እንዲህም አለ፡- አንባቢው ይፈጥን ዘንድ ራእዩን ጻፍ በጽላትም ላይ ግለጠው"* (ዕን.2፥1-2) ይላል። ዕንባቆም የጸሎት ሰው ስለ ነበረ የወሰዳቸው ርምጃዎች ለእኛም ጥሩ ትምህርት ይሰጡናል ብዬ አስባለሁ።

- *በመጠበቂያችን ላይ መቆም* ፡-ይህ የሚያመለክተን በጸሎትና በጾምታ ጌታን እየጠበቅን በፊቱ መሆን እንዳለብን ነው፤

- *የሚናገረኝንም* ፡-እግዚአብሔር በጸሎትና በጸጥታ መንፈሳችንን ነቅቶ ስንጠብቅ ይናገረናል፤
- ራእዩን ጻፍ በጽላትም ግለጠው ፡-እግዚአብሔር የተናገረንን ነገሮችና ያየናቸውን ራእዮች፣ ደጋግመን ስናስባቸውና ስናስተውላቸው፣ የልባችን ጽላት ላይ በማይረሳ መልኩ ይጻፋሉ። ለልባችን የተናገረንን ወዲያውኑ በጽሑፍ ማስፈር ማስተዋል ነው፤ የተናገረን ሲፈጸም ለምሥጋና ይሆናልና!

የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ ሕይወታችን እንዳይመጣ እንዳይባርከንና ሩጫችን እንዳይፈጥን፣ የሚከለክሉ ብዙ ሁኔታዎች አሉ። የሚከተሉት ዋናዎቹ ናቸው፡-

- በእግዚብሔር ፊት በቂ ጊዜ አለመቆየት፤
- ቃሉን አለማጥናትና አለማሰላሰል፤
- ኃጢአትና አለመታዘዝ፤
- አለማመን፤
- አለመጠባበቅ (ኢሳ.42፥20) ወዘተ።

እግዚአብሔር አንዳንዴ አልሰማ ስንል እንሰማው ዘንድ በተለያዩ በአስጨናቂ ሁኔታ (ምድረ በዳ) ውስጥ ያሳልፈናል። ሲ.ኤስ ሌዊስ የሚባሉ የእግዚአብሔር ሰው *"እግዚብሔር በመከራችንና በሕመማችን ጊዜ ጮኾ ይናገራል"* ያሉት ይህንን አስበው ነው የሚመስለኝ። የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ዐመፁበት ስለ እስራኤላውያን ሲናገር፣ *"ስለዚህ እነሆ አባብላታለሁ ወደ ምድረ በዳም አመጣታለሁ ለልብዋም*

*እናገራለሁ።"* (ሆሴ.2፥16-17) ብሏል። ከዚያም ለልባቸው ከተናገራቸው በኋላ ስለሚመጣው መታደስ ሲናገር፣ *"እንደ ሕጻንነትዋ ወራት ትዘምራለች"* (ሆሴ.2፥17) ብሏቸዋል። ይኸው ምዕራፍ እንደሚያሳየን፣ እግዚአብሔር የልቡን ሐሳብ ሲናገረንና እኛም ሊለን የፈለገውን ስናስተውል፣ ኃይላችን ይታደሳል፤ ውስጣችን በሰላምና በደስታ ይሞላል፤ እናም ተስፋችን ያንሰራራል።

እዚህ ሆሴዕ 2 ቁጥር 16 ላይ ያለው አንቀጽ ሲጀምር *«ስለዚህ»* የሚለው ቃል ከላይ ያለውን ሐሳብ ለማገናኘት ጸሐፊው የተጠቀመበት ቃል ነው። እግዚአብሔር ከኃጢአታቸውና ከዓመፃቸው እንዲመለሱ ደጋግሞ ቢናገራቸውም፣ አልሰማ ስላሉ ነው ወደ ምድረ በዳ ሊወስዳቸው የፈለገው። በጊዜው መመለስ ሲያቅተን፣ በእኛም ሕይወት እንዲሁ ይሆናል። ነገር ግን የእግዘአብሔር ከፍ ያለው ሐሳቡ፣ ከቃሉ ውስጥ ድምፁን ሰምተን ፈጥነን እንድንመለስለት ነው። ሆኖም ግን ብዙ ጊዜ እናስቸግረዋለንና፣ እግዚአብሔር እኛን ከጥፋት ለመመለስ በተለያዩ አስቸጋሪ የሕይወት መንገዶች ውስጥ እንድናልፍ የሚፈቅድበት ጊዜ አለ።

ከብዙ ጉዳት እንጠበቃለንና፣ እግዚብአብሔር ሆይ ድምጽህን በመስማት ፈጥነን እንድንታዘዝህ ጆሮዎቻችንን ከፈትልን፤ማስተዋልን ስጠን!

**መዝጊያ ምንባብ፡**-*"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።"* (ዮሐ.10፥27-28)

# ስለዚህ አንታክትም

*"የክርስቲያን ሕይወት ያላሰለሰ ከፍታ ብቻ አይደለም። በግሌ እጅግ ተስፋ የቆረጥሁባቸው ጊዜያት አሉኝ። በእግዚአብሔር ፊት ዓይኖቼ እንባ አቆርዝዘው የተደፋሁባቸውና "ጌታ ሆይ ማረኝ፣ እርዳኝ" ያልሁባቸው ጊዜያት አሉኝ።/ The Christian life is not a constant high. I have my moments of deep discouragement. I have to go to God in prayer with tears in my eyes, and say, 'O God, forgive me,' or 'Help me."* ቢሊ ግራሃም

የእግዚአብሔር ቃል *"ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፥ ጐበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፤ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደክሙም።"* (ኢሳ.40፥30-31) ብሎ ይናገራል። በምንባቡ ውስጥ እንደምናስተውለው፣ መታከት ማለት መሰላቸት፣ መሳነፍ፣ ፍላጎት ማጣት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ኃይል ማጣት የሚሉትን ሐሳቦች ያመለክታል።

በክርስትና ሕይወታችን ሊያታክቱን የሚችሉ ነገሮች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ለውጥ ማጣት፣ የመከራ ብዛት፣ ስደት፣ ደጋግሞ መውደቅ፣ መገፋት ወዘተ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። የኢየሱስን ሕይወት በሥጋችን ተሸክመን ስለምንዞር ለእነዚህ ለተጠቀሱት አደጋዎች መጋለጣችን አይቀሬ ነው፤ ክርስትና ዋጋ ያስከፍላልና (2ቆሮ.4፥10)። ለምሳሌ በጌታ ኢየሱስ ከመሆኔ የተነሣ ድሮ በዓለም ሳለሁ አውቃቸው የነበሩ ብዙ ሰዎች አካሄዴ ስላልጣማቸው እስከ ወዲያኛው ርቀውኛል። ይኼ በክርስትና አንድ

እየከፈልኩት ያለ ዋጋ ነው። እንዲህ ዓይነት መገፋት በሕይወታችን ሲበዛ፣ ወደ መታከት እንድናመራ ሊያደርገን ይችላል፤ ከጌታ ጋር ያለን ኅብረት እስካልጠነከረ ድረስ። ካስተዋልንና የጌታን መከራን የምንካፈል እንደሆነ ከገባን ግን፣ እጅግ ደስተኞች ነው የምንሆነው።

መታከት ከባድ ነው፤ እንደ ቀላል ነገር መታየት የለበትም። ቶሎ መፍትሔ የሚፈልግ ጉዳይ ነው። ሳናስተውል እየጠነከረ ከሄደ፣ የጸሎት ሕይወት መቀዝቀዝ፣ ለዲያቢሎስ ጥቃት በቀላሉ መጋለጥ፣ መሸነፍ፣ ያም ደግሞ የበለጠ መታከትን እየወለደ ሄዶ ጨርሶ መውደቅን ያስከትላል።

በሕይወታችን ለመታከት የሚያጋልጡን ብዙ ምክንያቶች አሉ። እኔ የታዩኝን አንድ ስድስቱን እጠቅሳለሁ፡-

- ተግባር መፍታት (idlness)፡-

ቅዱስ ቃሉ *"ተግባር መፍታት እንቅልፍ ታመጣለች፤ የታካችም ነፍስ ትራባለች።"* (ምሳ.19፥15) ብሎ መክሮናል። ይህንን በውጤት ሂደት ባስቀምጠው ተግባር መፍታት፣ መንፈሳዊ ድንዛዜና እንቅልፍ፣ መታከት፣ መንፈሳዊ ጠኔ፣ ብሎ መንፈሳዊ ሞት ነው የሚከተለው።

- በቂ የሆነ ጊዜ በጌታ ፊት አለማሳለፍ፡-

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ጸጋ ዙፋኑ አዘውትረን እንድንመጣና ጸጋንና ምሕረትን እንደምንቀበል ይመክረናል (ዕብ.4፡16)። ወደ ጌታ በተገቢው መጠን ካልቀረብን ግን፣ ምሕረትና ጸጋ ስለሚጎድሉን በቀላሉ እንታከታለን።

- ከቃሉ ጋር ደካማ የሆነ ኅብረት

እግዚአብሔርን ቃል በበቂ ሁኔታ አለመመገብ፣ አለማጥናትና አለማሰላሰል መንፈሳችን ደካማ እንዲሆን ስለሚያደርገው፣ በቀላሉ ልንታክት እንችላለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች *"በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ እንድትጠነክሩ..."* (ኤፌ.3፥17) ብሎ ጸልዮላቸዋል። ለመሆኑ እንዴት ነው የሚጠነክረው? መንፈሳችን የሚጠነክረው መንፈስ የሆነው ቃል ወደ ውስጣችን ሲገባ፣ ማስተዋል ሲበዛልንና ከጌታ ጋር በጸሎት ያለማቋረጥ ስንገናኝ እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

- የጌታን ምሪት አለመከተል

*ከመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ይልቅ የሥጋንና የነፍስን ድምፅ ስንከተል፣* እምነታችንና ጽናታችን ስለሚሸረሸር በቀላሉ ልንታክትና ተስፋ ልንቆርጥ እንችላለን። ስለዚህ ስሜቶቻችን፣ ነፍሳችንና ሥጋችን የሚሉንን ሳይሆን፣ መንፈስ የሆነው ቃል የሚለንን ለመሆንና ለመተግበር መጨከን ነው የመውጫው መፍትሔ። ይህ ደግሞ ትልቅ ዲሲፕሊን ይፈልጋል።

- የራእይ አለመኖር

ራእይ ወይም መገለጥ ሲጠፋ መታከት ብቻ ሳይሆን፣ የሕይወታችን ጉዞ ይደነቃቀፋል። ቅዱስ ቃሉ *"ራእይ የሌለው ሕዝብ መረን ይሆናል።"* (ምሳ.29፥18) ይላልና። የወንጌል እውነት በበራልንና በተገለጠልን መጠን ነው እየበረታን የምንመጣው። ራእያችንም እየጠለለ የሚሄደው። በተቃራኒው መንፈሳዊ ራእይ፣ መገለጥና መረዳት ከሕይወታችን ሲጠፋ

ሕይወታችን በድግግሞሽ ይዋጥና ልንታከት እንችላለን።

- የአጋንንት ተጽዕኖ

የጨለማው ኃይል መታከትን ሊያመጣ ይችላል፤ ቃሉ *“ባላጋራችን ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራል”* (1ጴጥ.5፥8) ይህንን አስቦ እንደ ሆነ አምናለሁ። ዲያቢሎስ መታከት ላይ እንድደርስ አደረገን ማለት ሊውጠን ትንሽ ነው የቀረው ብዬ አምናለሁ። በዚያ እኩይ ሥራው፣ “አትችልም፣ አይሳካልህም፣ የት አለ ፍሬህ፣ ተሰሚነት የለህም፣ አርፈህ ብትቀመጥ ይሻላል” እያለ አእምሮአችንን በመደብደብ የጀመርነውን ሥራ ሊያስጥለን ይተጋል። ስለዚህ ነቃ ብለን ሥራውን ጸንተን መቃወም አለብን፤ በቃሉ ሰይፍም ጸንተን መዋጋት ይኖርብናል።

እንደ አዲስ ኪዳን አማኝ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልገንን ነገሮች ሁሉ ሰጥቶናል (2ጴጥ.1፥2)። ጸንተን እንድንቆም የሚያደርገው ጸጋው አልጎደለም። ቢሆንም በተግባር ደረጃ መታከት ወደ እያንዳንችን ሕይወት በተለያየ መንገድ ሊመጣ የሚችል ዕውነታ ነው፤ በተለይ ካላስተዋልንና ካልተጠነቀቅን።

ሐዋርያው ጳውሎስ 2 ቆሮንቶስ 4፥1 እና 2 ቆሮንቶስ 4፥16 ያሉትን ክፍሎች ሲጽፍ *‹‹ስለዚህ አንታከትም››* ብሎ ነው የሚጀምረው። እንደዚህ ያለበትም ምክንያት፣ እንዳንታከት የሚያደርጉ ነጥቦችን በዝርዝር ስለ ጠቀሰ ነው። የተጠቀሱት ምክንያቶችም የሚከተሉት ናቸው፡-

- በጸሎትና ከቃሉ ጋር ባለ ኅብረት ከተጋን፣ በውስጣችን ያለ

ማቋረጥ የሚሠራ መንፈስ ስላለ አንታክትም።

የእግዚአብሔር ቃል *“መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።”* (2ቆሮ.3፥18) ይላል። *“መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ”* የሚለውን ሐረግ በልባችሁ አስምሩልኝ። ይህ ማለት በሕይወታችን መታከት እንዳይመጣ፣ ይልቁንም መንፈሳዊ ለውጥና እድገት እንዲኖረን የሚያተጋንና በውስጣችን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው ማለቱ ነው። ለዚህም ነው በሚቀጥለው ክፍል ምዕራፍ ማለትም 2ቆሮንቶስ 4 መጀመሪያ ላይ «ስለዚህ አንታክትም» ብሎ የሚጀምረው። ይህ አባባል ከምዕራፍ ሦስት ጋር ተያያዥነት እንዳለው ያስተውሷል።

- *”...የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ እቃ ውስጥ ስላለን አንታክትም።”* (2 ቆሮ.4፥7)

የመኪና ከመነዳሬ ውስጥ ያለው አየር ተሽከርካሪው ያለ ችግር እንዲሄድና ጎማው ተወጥሮ እንዲጠበቅ እንደሚጠቅመው ሁሉ፣ በውስጣችን ያለው መዝገብ (ባከማቸነው ልክ) ከመታከትና ተስፋ ከመቁረጥ ይጠብቀናል። ሐዋርያው ጳውሎስ የዚህን መዝገብ በውስጣችን የመኖር ጥቅም ሲገልጽ፣ *“በሁሉ እንገፋለን እንጂ ተስፋ አንጨነቅም፤ በእናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም።”* (2ቆሮ.4፥8) ብሏል። ድንቅ ምስጢር ነው። ትልቁ ነገርም ያለው በውስጣችን ያለውን እምቅ ሀብት መንገዘቡ ላይ ነው። ቃሉስ *“በጻድቅ ሰው ቤት ብዙ ኃይል አለ”* (ምሳ 15፥6) ይል የለ?!

- *አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን አንታክትም (2ቆሮ.4፥13)፤*

ምክንያቱም እምነት ጽናትን ያመጣልና ነው (ኢሳ 7፥9)።

- *የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ስለሚታደስ (2ቆሮ.4፥16) አንታክትም።*

ይህ ቃል በተለይ በክርስትና ሕይወታችን ዋና ቁልፍ ነገር ነው። መታከት እና መሰላቸት ወደ ሕይወታችን እንዳይመጣ ጠበቅ ያሉና ተዘውታሪ ጸሎቶች ያስፈልጉናል። ልክ ባትሪ ሲደክም በአሌክትሪክ ቻርጅ እንደሚደረግና እንደ ገና ሊሠራ እንደሚችል ሁሉ፣ ስንጸልይ (በተለይ በመንፈስ ስንጸልይ) እንታነጻለን፤ ኃይላችን ይጨምራል፤ ተስፋችን ይታደሳል፤ ብሎም እንደ ገና ለቀጣይ ሥራዎች እንጠናከራለን። ይህ መሰጠት የሚያስፈልገው፣ ዲሲፕሊን የሚጠይቅና በእግዚአብሔር ጸጋ ተደግፈን በቀጣይነት ያለማቋረጥ መተግበር ያለብን ኃላፊነታችን ነው። ለዚህ ነው *"ዕለት ዕለት ይታደሳል"* ብሎ የሚናገረው፤ ሳናሰልስ ልናደርገው የሚገባን ተግባር መሆኑን ለማመልከት!

በክርስትና ሕይወታችን መታከት ሊመጣ እንደሚችል ከላይ ባሉ አንቀጾች ላይ ጠቅሻለሁ። ላለመታከት የሚጠቀመንን ከጌታ የተሰጡንን በረከቶችም ተናግሬአለሁ። አሁን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ምን እናድርግ ለሚለው ስድስት ተግባራዊ ርምጃዎችን በመጥቀስ ጽሑፌን እጨርሳለሁ፦

1. ጠንከር ያለ የጸሎትና የጽሞና ጊዜዎችን እንያዝ (ከጾም ጋር ቢጣመር የበለጠ ይመረጣል)፤

2. መጽሐፍ ቅዱሳችንን በሚገባ እናንብ፤ ካለንበት ሁኔታ ጋር የሚሄዱ አነቃቂ መንፈሳዊ ጽሑፎችን እናንብ፤ እናጥና እናሰላስል፤

3. ከእኛ በሚሻል የክርስትና ሕይወት ደረጃ ላይ ካሉ ባልደረቦች ጋር በመገናኘት እንመካከርና እንጸልይ፤

4. ከመታከት በስተጀርባ የጠላት ተጽዕኖ ሊኖር ስለሚችል፥ ምሽጉን ለማፍረስ በእምነት እየተቃወምን እንጸልይ፤ ራሳችንን ትሑት አድርገንም ይጸለይልን፤

6. ጤናማ መንፈሳዊ ስብከቶችንና ትምህርቶችን እንስማ።

የኃይል ምንጫችን እግዚአብሔር ነው። ስለሆነም ፊቱን በመሻትና በእግሩ ስር በመሆን ብንጠባበቀውና ብንፈልገው፥ ታማኝ ነውና፥ መጥቶም ያድሰናልና በእግሩ ስር እስክንፈወስ ድረስ እንሁን።

**መዝጊያ ምንባብ፡**-*"እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው አይደክምም አይታክትም ማስተዋሉም አይመረመርም።ለደካማ ኃይልን ይሰጣል ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል ጎበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ እግዚአብሄርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ።"* (ኢሳ. 40፥31)

# የልብ ለውጥ

*“የጸሎት ትልቁና ዋናው ሥራው እግዚአብሔር ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ሳይሆን፣ የሚጸልየውን ሰው ከውስጥ ወደ ውጭ መቀየር ነው።/ The function of prayer is not to influence God, but rather to change the nature of the one who prays.” — ሶረን ኬርኪጋርድ*

በዚህ ዘመን ሳይንሳዊና ማኅበራዊ ተቋማት፣ ጠበብቶች፣ ሳይንቲስቶች እና አዋቂዎች “ለሰው ልጅ የሞራል ማሽቆልቆል እና ጥፋት የሰው ባሕርይ መበላሸት ነው” ይላሉ። እናም “የባሕርይ ለውጥ ላይ መሥራት ነው መፍትሔው” ብለው ይናገራሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ችግር ከዚያ እንደሚጠልቅ እና *“የልብ ለውጥ”* እንደሚያስፈልግ በተለያየ መንገድ ያስተምረናል።

“ልብ” የሰው ሁለንተናዊ ማንነቱን ይወክላል፤ መንፈስን ጨምሮ። ኃጢአተኛው ተፈጥሮአችን (the sinful nature) በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም መወለድ ካልተሸነፈ በስተቀር፣ ባሕርያችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። ስለሆነም አካባቢያችን ላሉ ድምጾች እና ግብዣዎች የምንሰጠው ምላሽና ዝንባሌያችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን አይችልም። ፈቃዳችንም ከራስ ወዳድነት እና ከሥጋዊ ማንነታችን የመነጨ ስለሚሆን፣ አሳዛኝ ውጤቶችን ማየታችን አይቀሬ ነው። ስለዚህም ባሕርይን መለወጥ ሽንፍላን የማጠብ ዓይነት ሥራ ነው የሚሆንብን፤ መቼም አይጠራምና።

የባሕርይ ለውጥ አመጡ የሚባሉ ሰዎች፣ በቀላሉ ወደ አሮጌው ማንነታቸው የመመለስ ዕድላቸው የሰፋ ነው፤ መሠረታዊ የልብ ለውጥ

እስካላገኙ ድረስ። ለምሳሌ ተከታታይ ሙያዊና የጓደኛ ምክሮችን አግኝቼ ሲጋራ ማጨስ ለተወሰነ ጊዜ አቁሜና ባሕርዬ ተስተካክሎ ደስ ብሎኝ ያውቃል። ግን ውጫዊ ለውጥ ስለነበር ባንድ በገጠመኝ ቀውስ ምክንያት ስመለስ፣ እንዳውም ሰባት እጥፍ ይብስብኝ እንደ ነበር ትዝ ይለኛል።

በዓለማችን የምናያቸው ድርጊቶች እና አሳዛኝ ክስተቶች የተጸነሱት በልብ ውስጥ ነውና፣ የልብ ለውጥ ላይ ማተኮር ማስተዋል ነው። የምናደርጋቸው ኢንቨስትሜንቶች ልብ ላይ መሆን ይገባቸዋል፤ አለበለዚያ ለውጣችን ታይታዊ ብቻ ነው የሚሆነው።

የእግዚአብሔር ቃል *"ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው። ከልብ ክፉ አሳብ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣልና።"* (ማቴ.15፥18-19) ብሎ ይናገራል። በዚህ ምንባብ መሠረት፣ ልባችን የክፋት ሁሉ ፋብሪካ እንደ ሆነ በግልጽ እናያለን። ስለዚህ እርሱ ላይ ነው ትኩረት አድርገን ሥራን መሥራት ያለብን፣ ዘለቄታና የሚያሳርፍ ለውጥ እንዲኖረን ካስፈለገ። አለበለዚያ ልፋታችን *"አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ"* ዓይነት ይሆናል።

በዳግም መወለድ ስለሚመጣ ስር ነቀል፣ መሠረታዊና ዘላቂ ለውጥ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር፣ *"አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም እስሄዳችኋለሁ ፍርዴን ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ።"* (ሕዝ.36፥26-27) ይላል። ይህ ክፍል ከድርጊት እና ከተግባር በፊት የልብ ለውጥ አስፈላጊ እንደ ሆነ ያሳየናል። በተቃራኒው የዓለም

ጠበብቶች፣ ፈላስፋዎችና አዋቂዎች ይህንን መርሕ ባለመገንዘብ፣ በድንጋይ ልብ ላይ ዘለቄታዊ ለውጥ እንደሚመጣ ነው የሚሰብኩን። ሐቁ ግን ለሰው ልጅ እጅግ በጣም የሰለጠነ ትምህርት ብንሰጠው፣ አለ የተባለ ሙያዊ ምክር ብንሰጠው፣ ልቡ በእግዚአብሔር መንፈስ ካልተለወጠ ታጥቦ ጭቃ እንደሚሆን ተደጋግሞ ታይቷል።

ለምሳሌ እኔ የሕክምና ባለሙያ ነኝ። በጤና ዙሪያ ብዙ መጻሕፍትን አንብቤአለሁ፤ ነገር ግን ተግባሬ ፈጽሞ ከባለሙያ የሚጠበቅ አልነበረም። ጫት እቅም ነበር፤ አልኮል እጠጣና ሲጋራ አጨስ ነበር። ያነበብኳቸው ነገሮች በፍጹም አልረዱምኝ፤ በወንጌል የልብ ለውጥ ማምጣቴ እንጂ! ወደ ጌታ በዳግመኛ መወለድ ስመለስ ያ ሁሉ ሱስ ባንዴ ነው ቀጥ ያለው። በነጻነት መኖር ምን ዓይነት እንደ ሆነ በተግባር ቀምሼም አይቼዋለሁ። ክርስትና ተረት ተረት ሳይሆን፣ እውነተኛ የልብ ለውጥ የምናገኝበት ሕይወት እንደ ሆነ እመሰክራለሁ።

አንደበታችን ብዙ ክፉ ነገሮችን ያወጣል። ብዙዎችንን ያሳዝናል፤ ብሎም የብዙ ሰዎችን ሩጫ ያሰናክላል። የባሕርይ ለውጥ በማምጣት አንደበታችን ጥቂት ሊሻሻል ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን ለውጡ ምንጩን በማድረቅ ላይ የተመሠረተ ስለማይሆን፣ ወይም ውጫዊ ስለሚሆን፣ ዞሮ ዞሮ ባንድ የሕይወት ቀውስ ሰዓት ሊያገረሽብን እንደሚችል ምንም ጥርጥር የለውም።

የእግዚአብሔር ቃል *"የጠቢብ ልብ አፉን ያስተምራል"* (ምሳ 16፥23) ብሎ ይናገራል። ይህ ቃል የተለወጠ ልብ አንደበት ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ነው የሚያስገነዝበን። ጌታ ኢየሱስም *"በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና፤ መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን*

*ያወጣል።”* (ሉቃ 12፥34) ብሎም ተናግሯል፤ አፍና ልብ የተገናኙ መሆናቸውን ሲያሳይ። ስለዚህ ለዘለቄታዊ ለውጥ ትኩረታችን የልብ ለውጥ ላይ እንጂ ውጫዊ ለውጥ ሊሆን አይገባም።

የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ስለሚደረግ ስር-ነቀል መንፈሳዊ ቀዶ ጥገና ሲናገር፣ *“የሥጋንም ሰውነት (sinful nature) በመገፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ።”* (ቈላ.2፥11፤ አጽንዖት የእኔ) ይላል። ይህ ክፍል ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ በመወለድ ጊዜ ስለሚሆን መንፈሳዊ ሂደት ነው የሚያስረዳን።

የእግዚአብሔርን መንፈስ በእውነተኛ ንስሓ ስናስተናግድና ወደ ውስጣችን ከልብ ፈቅደንለት ሲገባ፣ የሚያደርገው ነገር ኃጢአተኛው ተፈጥሮአችንን ወይም ኃጢአት በመሥራት የሚደሰተው ማንነታችንን በእንግሊዝኛው *“the sinful nature”* በቅጡ ይገርዘዋል ወይም ይገፍፈዋል። ስለዚህ ከእንግዲህ በኋላ ተሳስተን እና ሳናስተውል ኃጢአትን ልንሠራ እንችል እንደሁ እንጂ፣ ኃጢአትን ደስ ብሎንና ያለ ምንም ወቀሳ በደንዳንነት በመሥራት አንቀጥልም።

ይህ ለውጥ ነው ለእያንዳንዳችን የሚያስፈልገን! ይህ ነው ትክክለኛ የልብ ለውጥ! የሞተው መንፈሳችን ስለሚድን፣ የድንጋይ ልባችን ወደ ሥጋ ልብ ስለሚለወጥና ለውጣችን ከውስጥ ወደ ውጭ ስለሚሆን ቀድሞ ባቃቱን ነገሮች ላይ አሸናፊዎች እንሆናለን። ስለዚህ ዘለቄታዊ መፍትሔ ያላቸው የሚመስሉ ነገሮችንና ወንዝ የማያሻግሩ ሙከራዎችን አቁመን፣ ልብን አዲስ አድርጎ የመለወጥ ብቃት ወዳለው አምላካችን እንመለስ!!

**መዝጊያ ምንባብ፡-***“ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ*

*ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል።"* (ቲቶ.2፥11-13)

# ድብርት (mild depression) መድኃኒት አለውን?

*"ብዙ በጸለይን ቁጥር፣ ፍርሃታችንና አለመረጋጋታችን እየቀነሰ ይሄዳል። ብዙ ባመለክን ቁጥር፣ ጭንቀታችን እያነሰ ይሄዳል። በመሆኑም ታጋሽነት እና ጫና አልቦነት ይሰማናል።/ The more you pray, the less you'll panic. The more you worship, the less you worry. You'll feel more patient and less pressured." — ሪክ ዋረን*

በዓለማችን በተለይ በምዕራቡ ምድር እንደምናየው ብዙ ሰዎች በተለያዩ የአእምሮ በሽታዎች ሲጠቁ እናያለን። ዋነኛው የአእምሮ ችግርም ድብታ (depression) እንደ ሆነ በዚህ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ጠበብቶች ይስማማሉ። የድብታ (depression) መንስዔው እንደ ቦታው እና እንደ ሰዉ ዓይነትና አኗኗር ይለያያል። ሁሉንም የሚያመሳስላቸው ግን የችግሩ ስሜቶች እና ምልክቶች መመሳሰላቸው ነው። ማለትም ሁሉም ሰዎች ላይ ደስታ ማጣት እና ኀዘን ይኖራል መጠኑ ቢለያይም። ይህ ችግር ጌታ ኢየሱስን የማያውቁ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን፣ እሱን በሚገባ የሚያውቁ

ሰዎችን ላይ ሳይቀር ይስተዋላል።

ድብታ (depression) ብዙ ዓይነት መልኮች ቢኖሩትም፣ ለመልእክቴ እንዲመች፣ ቀላልና ከባድ የድብታ ዓይነቶች ብዬ ከፍያቸዋለሁ። ከባድ የተባሉቱ የድብታ ዓይነቶች ራሳቸው ብዙ ዓይነት ያላቸው ሲሆኑ፣ የሳይኪያትሪስቶች (የሥነ አእምሮ ባለሙያዎች) ርዳታ የሚያስፈልጋቸው ችግሮች ናቸው። መድኃኒት መውሰድም ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

ቀላል ድብርትን/ ድብታን በተመለከተ ግን በራሴም በግል ሕይወቴ እንዳየሁት፣ ጠንከር ባለ ጸሎትና ከእግዚአብሔር ቃል ባለን ጥብቅ ግንኙነት ይወገዳል ብዬ አምናለሁ። የቀላል ድብርት መገለጫዎችም መነጫነጭ፣ በቀላሉ መድከም፣ ተስፋ መቁረጥ፣ በቀላሉ መከፋት፣ የአእምሮ አለመሰባሰብ፣ ተነሣሽነት ማጣት ወዘተ ናቸው።

አንድ መታወቅ ያለበት ነገር ጊዜያዊ ጭንቀት እና ድብታ ማንኛችንም ላይ በተለያየ ምክንያት ሊመጣ ይችላል፤ ነገር ግን እላያችን ላይ ቤቱን ሠርቶ እንዲረጋጋ እና መጫወቻ እንዲያደርገን መፍቀድ የለብንም። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ችግር ወደ ሕይወታችን እንዳይመጣ ጥሩ መከላከላያ መድኃኒት ያለው ሲሆን፣ ይህ ችግር ካገኘንም በኋላ ባስተማማኝ ሁኔታ የምንወጣበት መፍትሔም በውስጡ ይዟል። እኔ ራሴ በተግባር ከቃሉ ጋር ትክክለኛ እና የጠለቀ ኅብረት ካለን፣ ዝቀን እና ቀድተን የማንጨርሰው የደስታ ምንጭ እንዳለ እኔ በሕይወቴ አይቻለሁ።

ንጉሥ ዳዊት በጭንቀት፣ በድብታና ነፍስን ግራ በሚያጋባ አጣብቂኝ እና ኀዘን ውስጥ ከማናችንም በላይ ያለፈ እንደ ሆነ ይታወቃል። በመሆኑም ችግሩን፣ የችግሩን መፍትሔና የመፍትሔውን ውጤት በመዝሙር 42፥2-

4 በሚደንቅ ሁኔታ ጽፎልናል።

ይህ ክፍል እጅግ ግሩም ትምህርት ያዘለ ሲሆን፣ በሚገባ በሕይወታችን ከተገበርነው ትልቅ በረከት እንዳለው አምናለሁ። ይህንን ምንባብ ወደ ጌታ ከመጣሁ በኋላ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ። አሁንም ደጋግሜ የማነበውና የማሰላስለው ክፍል ነው። እንዳውም በጸሎት ጊዜዬ ምንባቡ ውስጥ ራሴን እያስገባሁ የምጸልይበትም ጊዜ አለ።

ዳዊት *"አንተ አምላኬ ኃይሌም ለምን ትተወኛለህ? ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ? ብርሃንና እውነትህን ላክ እነርሱም ይምሩኝ ወደ ቅድስህናህ ተራራ እና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ። ወደ እግዚአብሔር መሰዊያ ጎልማስነቴንም ደስ ወዳሰኘት ወደ አምላኬ እገባለሁ።"* (መዝ.43፥2-4) ብሎ ይናገራል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የቆየበት የጊዜ ርዝመት ባይታወቅም፣ ትንሽ እንደ ከረመበት መገመት ይቻላል። ይህንን የሚጠቁመን *"ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ"* የሚለው ሐሳብ አገላለጹ ነው። እንደዚህ ዓይነት ኀዘንና ጭንቀት የሚያደርሱበት ደግሞ ጠላቶቹ (ኢጋንንቶች-የሰው ጠላት የለንምና) እንደ ሆኑ ይናገራል። ከዚያም መፍትሔውን ራሱ ያቀርባል፤ *"ብርሃንህንና እውነትህን ላክ"* ብሎ።

ዳዊት መፍትሔው ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃል እንደ ሆነ ነው የሚነግረን። ባጭሩ ክፍሉ በጸሎት መንፈስ ሆነን ፊቱን እየፈለግን፣ እየቃተትን፣ ቃሉን እያሰላሰልን በጽናት ስንጠብቀው መድኃኒት እንደሚላክልን ይጠቁመናል። ዳዊት ክፋትና ጉዳት ወደሌለበት *"ወደ ቅድስና ተራራውና ወደ ሕልውናው (His presence)"* ደጋግሞ ሄዶ ተሰውሮ ያውቃልና፣ ያንን በመሻትና በመጠማት ነው አምላኩን እየተማጸነ የነበረው። እንደምናውቀው በሕልውናው

ውስጥ ሰላም አለ፤ ደስታ አለ፤ ዕረፍት አለ፤ መረጋጋት አለ። ምክንያቱም፣ በእርሱ ፊት ጨለማ መቆም አይችልምና፣ ትካዜና ኀዘንም ይሸሻሉና! ክርስትናን ውብና ልዩ የሚያደርገው ታዲያ ሌላ ምንድነው? የፈውስ ምንጩ ጌታ ኢየሱስ ስላለ አይደለምን?

ስለሆነም በራሳችን መታገል ስለማይጠቅመን፣ ሙሉ በሙሉ ራሳችንን ለእርሱ እንስጠውና በፊቱ እንውደቅ! ለምን? "በመመለስና በማረፍ እንድናለንና በጸጥታና በመታመን (በፊቱ በመሆን) ኃይል ይሆንልናልና (ኢሳ.30፥15)!

ማሳሰቢያ፡- ይህ ጽሑፍ የስፔሻሊስቶች ሕክምና የሚፈልጉ የድብርት ዓይነቶችን አይጨምርም።

**መዝጊያ ምንባብ**፡- *"እግዚአብሔር ሰማ ማረኝም፤ እግዚአብሔር ረዳቴ ሆነኝ። ክብሬ ትዘምርልህ ዘንድ ዝምም እንዳትል ልቅሶዬን ለደስታ ለወጥህልኝ፥ ማቄን ቀድደህ ደስታንም አስታጠቅኸኝ። አቤቱ አምላኬ፥ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ።"* (መዝ.30፥10-12)

# የተትረፈረፈ ሕይወት

*"እምነት የሚወለደውና የሚጸናው በእግዚአብሔር ቃል ሲሆን፣ ከእምነት የተነሣ ደግሞ የደስታ አበባ ይፈካል።/ Faith is born and sustained by the Word of God, and out of faith grows the flower of joy."*
*— ጆን ፓይፐር*

ለአብዛኞቻችን ዓይናችን ተከፍቶ ስላልታየን ነው እንጂ ጌታ ኢየሱስ እረኛችን በፊታችን ድል ያለ ግብዣን አዘጋጅቶልናል። ዳዊት ስለዚህ ድል ያለ ዝግጅት ሲናገር፣ *"በፊቴ ገበታን አዘጋጀልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ ጽዋዬም የተረፈ ነው።"* (መዝ.23፥5) ብሏል። ይህ ቃል ዘወትር ሳነብበው ያስገርመኛል።

ወገኖቼ ቃሉን በአእምሮአችን ብናውቀውም፣ በውስጡ የያዘውን በረከት በሚገባ ስለማናገኘው ነው የምንተላለፈው። በቅጡ ብናገኘው ግን ሕይወታችን እንደሚቀየር አውቃለሁ። ከዚህ ቃል በግልጽ የምንረዳው ነገር፣ በሚገባ ይህንን ግብዣ እንዳናስተውልና የእምነት እጃችንን ዘርግተን በረከታችንን እንዳናፍስ የጠላት አዚምና ከበባ እንዳለ ነው። ይህንን ሐሳብ *"በጠላቶቼ ፊት"* የሚለው ሐረግ ይጠቁመናል።

ዳዊት መንፈሳዊ ዓይኑ የተከፈተ ሰው ስለነበር፣ በዚህ ቃል መሠረት አራት ነገሮችን በመንፈሳዊ አይኖቹ እንዳየ ተናግሯል። እነርሱም፡-

- በፊቱ መንፈሳዊ ገበታ መዘጋጀቱን፤
- ጠላት እንደ ከበበው፤
- የመንፈስ ቅዱስ ቅባት እንደተቀባ፤
- ጽዋው ሞልቶ እንደተረፈ (ለሌሎች የተረፈም በረከት እንዳለው)።

ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሐሳብ በተሳካ ሁኔታ አገልግሎ ያንቀላፋው፣ በፊቱ የተዘጋጀለትን ማዕድ በሚገባ በመንፈስ ማየቱና ሳያቋርጥ መውሰዱ ነበር። የተጻፈው ለትምህርታችን ተጽፏልና፣ የዳዊት

ተግባር የእንዳንዳችን ተግባር ሊሆን ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ።

*“ሕዝቤ ሰምቶኝ ቢሆን እስራኤልም በመንገዴ ሄደው ቢሆን፣ ከስንዴ ስብ ባበላቸው ነበር ከዓለቱም ማር ባጠገባቸው ነበር።”* (መዝ.81፥13-16) የሚለው ምንባብ ከመዝሙር 23፥5 ጋር ተመሳሳይ ሐሳብ አለው። እኔ በግሌ *“ከስንዴ ስብ ባበላቸው ነበር ከዓለቱም ማር ባጠገባቸው ነበር”* የሚለውን የተስፋ ቃል ባነበብሁት ቁጥር ያስደንቀኛል። ይህ ቃል የእግዚብሔርን ድምጽ መስማታችንና ምሪቱን መከተላችን ያለውን መንፈሳዊ በረከት ነው የሚያሳየን። በሁለቱም በተጠቀሱ ምንባቦች ላይ የእግዚአብሔርን መልካም እረኝነት እናያለን። ባግባቡ ድምፁን እየሰማን ከተከተልነው ደግሞ፣ የምናገኘው በረከት በግልጽ ሁኔታ ሰፍሯል። አዎ፣ እርሱ ቸር ነውና ታላቅ ገበታን አዘጋጅቶልናል።

በኢሳይያስ መጽሐፍ *“ሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝብ ሁሉ በዚህ ተራራ ላይ ታላቅ የሰባ ግብዣ ያረጀ የወይን ጠጅ ቅልጥም የምላባቸው የሰቡ ነገሮች የጥሩና ያረጀ የወይን ግብዣ ያደርጋል።”* (ኢሳ.25፥6) የሚል ቃል ግሩም የተስፋ ቃል እናነባለን። ይህ ክፍል ክርስቶስ ከመምጣቱ ከብዙ ዘመናት በፊት የተተነበየ ትንቢት ሲሆን፣ በክርስቶስ መሞት እና ትንሣኤ በከፊልም ቢሆን የተፈጸመ እንደ ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይስማማሉ። በዚህ ቃል ላይ ያሉ አገላለጾች እጅግ የሚያጓጉ ሲሆኑ፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር በሚኖረን የጠለቀ ኅብረት ስለምናገኘው ድል (‘ድ’ ይጠብቃል) ያለ በረከት የሚናገር የተስፋ ቃል እንደ ሆነ አምናለሁ።

ግን ግን ይህን የመሰለ ድንቅ ተስፋ ሳለን፣ ዳር ዳር እያልን ዘመናችን እንደምንፈጅ አይገባኝም። እንዳውም የጌታ መንፈስ *“አድምጡኝ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው። ጆሮአችሁን*

*አዘንብሉ ወደ እኔ ቅረቡ ስሙ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች።”* (ኢሳ.55፥2) ብሎ መክሮናል። ታዲያ ምንድነው በረከቱን እንዳንካፍል የከለከለን? በተለያዩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለእኛ ለሰው ልጆች የቀረበ ግብዣ እንዳለ ተነግሯል። ሆኖም ግን እስክንጠግብ እንድንበላ ተደጋግመን ብንጋበዝም፣ ምላሻችን አሳዛኝ እየሆነ ነው ያለው።

እኔ በዚህ ባሁኑ ዘመን ባለ የክርስትና አካሄድ የጌታ የኢየሱስ ነፍስ ምን ያህል እንደምታዝን በጭላንጭልም ቢሆን እገምታለሁ። የማያጠግቡ፣ የማይረቡ እና ወንዝ የማያሻግሩ ነገሮች ልባችንን ቀምተውታልና። ጉልበታችንን እንግዶች እንደ በሉት ይታያልና። በዚህም ምክንያት ግብዣዎቹ ላይ በሚገባ መገኘት አቃተን። ግብዣው ሳያንሰን አለመብላትን የመሰለ ምን የሚያሳዝን ነገር በምድር ላይ ይኖራል?

*ታዲያ መፍትሔው ምንድነው?* *“ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና።”* (ማቴ.5፥6) የሚለው የጌታችን የተስፋ ቃል የተዘጋጀውን ግብዣ ለማፈስ የመጀመሪያ እርምጃ ይመስለኛል። በክርስትና ሕይወት *«ራብና ጥማት»* ለመንፈሳዊ ለውጥና ዕድገት ትልቅ ሚናን ይጫወታሉ የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን እነዚህ ሁለት ሞተሮች ከሌሉንና፣ ረብ በሌላቸው ነገሮች አእምሮአችንን እና ውስጣችንን የምንሞላ ከሆነ፣ ለመንፈሳዊ ነገር ያለን ጉጉት ስለሚደበዝዝ እና ስለሚጠፋ፣ ከዚህ መለኮታዊ ግብዣ ተቋዳሽ እና ባለ ዕድል መሆን ያቅተናል።

እውነተኛ መንፈሳዊ ለውጥን፣ ዕረፍትንና በረከትን የምንፈልግ ከሆነ፣ በመሠረታዊ ደረጃ ይህ ራብና ጥማት ወደ ሕይወታችን እንዲመጣ ትጉሕ መሆን ያስፈልገናል፤ ቅዱስ ቃሉ *“የትጉ ነፍስ ትጠግባለች”*

(ምሳ.13፥5) ይላልና። ስለሆነም ይህ ራብና ጥማት ወደ ሕይወታችን እንዲመጣ የሚከተሉትን ነገሮች እናድርግ፡-

- የክብርን ጌታ ያለማሰለስ እንሻ፤
- ቢሰማንም ባይሰማንም የጸሎት ዲሲፐሊን ይኑረን፤
- ከቃሉ ጋር ጠንከር ያለ ኅብረት ይኑረን (እንብላው፣እናጥናው፣ ደግሞም እናሰላስለው)፤
- አዚምንና ድንዛዜን (የከፉን ሥራና ተጽዕኖ) እየተቃወምን እንጸልይ፤
- ከጌታ ጋር ያለንን ኅብረት የሚያደበዝዙ ነገሮችን በመጨከን ከሕይወታችን እናባርር።

ለማጠቃለል እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚደንቅ ግብዣ እንዳዘጋጀልን እጅግ ብዙ ማስረጃዎች አሉን። ይህንን ግብዣ ዝም ብለን መካፈል አንችልም። የእግዚአብሔር ቃል *“በቅዱሳን ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን”* (ቈላ.1፥12) ይላልና፣ ከዚህ በረከት የምንካፈለው በብርሃንና በብዙ መረዳት ነው። ስለዚህ ከላይ ከኢሳይያስ በተጠቀሰው ክፍል ላይ *“ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔ ቅረቡ ስሙ፤ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች።”* እንደሚል ወደ እርሱ ያለማሰለስ እንቅረብ!!

**መዝጊያ ምንባብ፡-**“እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ፥ ወደ ውኃ ኑ፥ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ። ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፥ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? አድምጡኝ፥ በረከትንም ብሉ፥ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው። ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ፤ ስሙ

ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች።” (ኢሳ.55፥1-3)

# በሕልውናው የመኖር ጥቅም

*“ጸሎት ያለ እግዚአብሔር ቃል ጥናት ባዶ ነው፤ ጥናት ደግሞ ያለ ጸሎት እውርነት ነው።/ Prayer without study would be empty. Study without prayer would be blind.” —ካርል ባርዝ*

ይህ ጽሑፍ ዮሐንስ 15፥1-11 ባለው ክፍል ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ኢየሱስ ምሳሌያዊ ቋንቋ በመጠቀም ከእርሱ ጋር የምናደርገው የጠበቀ ኅብረት፣ በክርስትና ሕይወታችን ወሳኝ እንደ ሆነ ያሳየናል። የመጀመሪያው መርሕ *“በእኔ ብትኖሩ እኔም በእናንተ”* (ቁ.4) የሚል ሲሆን፣ አያይዞም *“ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም።”* (ቁ.4) በማለት ከእርሱ ጋር ያለን ኅብረት ለፍሬ ማፍራታችን ወሳኝ እንደሆነ ያስገነዝበናል።

አዎ፣ በሕይወታችን ትልቅ ቦታ ሊይዝና እንቅስቃሴዎቻችንን ሁሉ ሊቆጣጠር የሚገባው *“በእኔ ብትኖሩ እኔም በእናንተ”* (ቁ.4) የሚለው የፍቅር መርሕ ነው። በመቀጠልም *“በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።”* (ቁ.7) የሚል እጅግ ድንቅ ተስፋ አለ። ማለትም የስኬታችን ቁልፍ ሚስጥር ያለው በእርሱ ሕልውና ውስጥ መኖራችን መሆኑን ልብ ይሏል።

ባጭሩ ክፍሉ የሚጨበጥ ፍሬ ያለው ክርስትና ለመኖር፣ የሚከተሉት

ሁለት የፍቅር መርሖዎች በሚገባ መተግበር እንዳለባቸው ያሳስባል፡-

- በእርሱ መኖር፣
- ቃሎቹ በእኛ ውስጥ መኖራቸው።

*"በእኔ ብትኖሩ"* (ቁ.7) የሚለው ሐሳብ በዳግመኛ ልደት መንፈስ ከሆነው ቃል በመወለድ ይጀምራል (ዮሐ.3፥5)። ይህ አስደናቂ መንፈሳዊ ለውጥ በውስጣችን ከተከናወነ በኋላ፣ ሕልውናው ውስጥ እንድንኖር የሚያደርገን ከቃሉ ጋር የምናደርገው ኅብረት እና ቀጣይነት ያለው ጸሎት ነው።

በትጋት እየጸለይን በፊቱ በቂ ጊዜን ስናሳልፍ፣ እያወቅነው፣ ከእርሱ ጋር እየተጣበቅንና ጸጋው በሕይወታችን እየበዛልን ይመጣል። ከዚህም የተነሣ ከዓለም እየተለየንና፣ መንፈሱን ከሚያሳዝኑ ነገሮች እየራቅን ስለምንመጣ፣ ሕልውናው በሚገባ እየታወቀን ወይም አብሮነቱን እየተሰማን መዋል ማደር እንጀምራለን። ይህ በረከት በሚገባ ወደ እኛ እንዲመጣ የሰው ኀላፊነት መኖሩ ምንም አያጠያይቅም። ማለትም አዘውትረን በጸጋው ዙፋን ስር መውደቅና ፊቱን መፈለግ ይኖርብናል።

*"ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ"* (ቁ.7) የሚለውን ሐሳብ እንደዚህ ማስቀመጥ ይቻላል። በተለያየ መንገድ ማለትም በስብከት፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናትና የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸውን መጻሕፍት በማንበብ ወደ ውስጣችን የሚገቡት የእግዚአብሔር ሐሳቦች፣ መጀመሪያ በአእምሮአችን በኩል ነው ወደ መንፈሳችን ወይም ወደ ውስጥ ማንነታችን የሚገቡት። በአእምሮአችን የተቀበልነው ቃል ወደ ውስጥ ወደ መንፈሳችን የሚወርደው ደግሞ ቃሉን ስንረዳውና ስናስተውለው ነው። ደግሞም ያስተዋልነውና የተረዳነው፣ እናም በብዙ ትጋት ከውስጣችን ጋር

ያዋሃድነው ቃል ነው፣ ውስጣችን ሊቆይና ሊኖር የሚችለው፤ *“በማያስተውል ላይ ሌባው ይመጣል”* (ማቴ.13፥19) ተብሎ ተጽፏልና። አዎ፣ ያስተዋልነውን ሌባው በፍጹም ሊነጥቀን አይችልም። ስለዚህ እዚህ ጋ ጥሩ ዋጋ መክፈል ይኖርብናል።

በዕብራውያን መጽሐፍ *“የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሀደ አልጠቀማቸውም።”* (ዕብ.3፥2) የሚል ጠንከር ያለ ምንባብ እናገኛለን። አእምሮአችን ውስጥ የሚዘሩት ቃሎች ወደ ውስጣችን ዘልቀው እንዲዋሃዱ ብዙ ማሰላሰል፤ ብዙ ጥናት እና በተግባር ላይ መዋል ይገባቸዋል። እንዲህ ስናደርግ ነው፣ ቃሉ በእኛ ውስጥ የሚኖረው። በተለይ ያነበብነውን ቃል በተግባር ማዋል፣ ውስጣችን በማይረሳ መልኩ እንዲታተም ያደርገዋል።

ስጀምር በጠቀስኩት ምንባብ (ዮሐ.15፥1-11) የእግዚአብሔር ቃል አስረግጦ ያለ እርሱ ምንም ዓይነት እመርታ እና ስኬት እንደማይኖረን ሲመክር፣ *“ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።”* (ቁ.5) ብሎ ይናገራል። *“ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም”* የሚለው ሐሳብ በሕይወታችን በሚገባ እስካልበራልን ድረስ፣ ያለ እርሱ ብዙ ልንኳትን እንችላለን። እጅግ ወሳኝና ጠንካራ ምክር ነው ለማለት ነው። እግዚአብሔር በሕይወቴ ይህንን ቃል በሚገባ እስካየውና እስኪታዘዘው ድረስ ጉልበቴን፣ ገንዘቤን እና ጊዜዬን ጨርሻለሁ። አሁን ጌታ ይመስገን ይህ ሐሳብ በመጠኑም ቢሆን የገባኝ ይመስለኛል፤ ገና የሚቀሩኝ ነገሮች ቢኖሩም።

በነገራችን ላይ ከላይ በተጠቀሱት የቃል መርሖዎች ሕይወታችን ሲለካ፣

አብዛኞቻችን ያለነው ታች እንደ ሆነ በመንፈሴ አስተውላለሁ። ለምን ቢባል፡-

- ከጌታ ጋር በቂ የሆነ የጸሎት ኅብረት የለንም፤
- ቃሉን በቂ ጊዜ ሰጥተን አናነብብም፣ አናጠናውም አናሰላስለውምም (ጊዜያችንን የሚቀሙ ብዙ ነገሮች አሉና)፤
- ቃሉን በተግባር ደረጃ አንለማመደውም።

ከዚህ የተነሣ በአካባቢያችንና በኅብረተሰባችን ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣ ፍሬ አይታይብንም። የሰማዩ አባታችን በሕይወታችን እንዲከብር፣ ሰዎች በእኛ ሕይወት እርሱን እንዲያዩ፣ ደግሞም ወደ እርሱ ዘወር እንዲሉ ካስፈለገ፣ ከላይ ወደ ተጠቀሱት ትእዛዞችና መርሖዎች በሚገባ መመለስ ይኖርብናል። አለበለዚያ ዝም ብለን ልናስመስል እንችል ይሆናል እንጂ፣ እነዚህን መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች በእግዚአብሔር ጸጋ ሥራ ላይ ሳናውል፣ በፍጹም ፍሬ የሚባል ነገር መጠበቅ የለብንም።

ታዲያ በእርሱ ስንኖር እና ቃሎቹ በእኛ ውስጥ ሲኖሩ፡-

- ከግንዱ ጋር ተጣበቅን ማለት ይቻላል፤
- እውነተኛ ፍሬም የማፍራት ችሎታ ይኖረናል።

ይህንን ፍሬ በሦስት ከፍለን ልናየው እንችላለን፤ ምንም እንኳ አንድ የሚያመሳስል ግብ ቢኖራቸውም (ክርስቶስን ማሳየት)፡-

1. *የመንፈስ ፍሬ ፡-*

*"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።"* (ገላ.5፥22)

2. *በበጎ ሥራ የምናፈራቸው ፍሬዎች* ፡-

“በጎ *ሥራ*” የሚለው ቃል የሕጻናትን፣ የአዛውንትን፣ የድሆችን፣ ማየት የተሳናቸውን ወዘተ ሕይወት የሚለውጥ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ሁሉ ይወክላል። ለዚህ ነው ቃሉ *“በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ.....።”* (ቈላ.1፥10-11) ብሎ የሚመክረው።

*3. የወንጌል ሥራ ፍሬዎች*

*“በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ”* (ቁ.7) የሚለውን የፍቅር ትእዛዝ ስንተገብር ስለሚገጥመን በረከት እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

- የምትወዱትን ለምኑ ይሆንላችኋል (ቁ.8)፤
- ደስታችሁም ሙሉ ይሆናል (ቁ.11)። ማለትም አገልግሎታችን ይሰፋል፤ ብዙዎቹ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይመጣሉ። ቤተ ክርስቲያን የተጽዕኖ ማዕከል ትሆናለች!

ስለሆነም ይህንን  ይህንን ሰፊ መንፈሳዊ በረከት በሕይወታችን ለማየት ሳንታክት በትጋት ፊቱን እንፈልግ!!!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*“በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ፥ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።”* (ቈላ.1፥10-12)

# ውስጥን የሚለውጥ መንፈሳዊ እርምጃ

*“ጸሎት እና ኃጢአት በአንድ ልብ ውስጥ አብረው አይኖሩም። ጸሎት ኃጢአትን ይበላዋል፤ አሊያም ኃጢአት ጸሎትን ያንቀዋል።/ Praying and sinning will never live together in the same heart. Prayer will consume sin, or sin will choke prayer.”*— ጄ.ሲ.ራይል

በሕይወታችን እውነተኛ መንፈሳዊ ለውጥ እንዲመጣ ካስፈለገ፣ ከምር መወሰን ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ። ብዙ ጊዜ ውጫዊ ነገሮች በመቀየራቸው ብቻ፣ እውነተኛ መንፈሳዊ እድገት ላይ ያለን እየመሰለን ልንታለል እንችላለን። እንደ ያዕቆብ ማንንም እያታለልንና እያስመሰልን ዘመናችንን ልንጨርስም እንችል ይሆናል። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሐሳብ ግን ውስጣችን በትክክል ተለውጦ እና እርሱን አንግሦ፣ ከዚህ በሚመነጭ ፍሬ እርሱን በዙሪያችን አስከብረን እንድናልፍ ነው። ለእዚህ ዓይነት ውጤት ደግሞ የጨከነ ማንነት እና ሁለንተናችንን በጸጋው ዙፋን ፊት ሙሉ በሙሉ መጣል ይኖርብናል። እንደዚያ ስናደርግ ብቻ ነው፣ እውነተኛ ፍሬን በሕይወታችን ማየት የምንችለው።

ከላይ ለተጠቀሰው የለውጥ እርምጃ፣ ዘፍጥረት 32፥22-32 ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። በዚህ ክፍል የምናየው፣ ያዕቆብ በሕይወቱ የወሰደውን እርምጃ እና ውጤቱን ነው። ለዚህ ክፍል ዳራ የሚሰጠን፣ በዘፍጥረት መጽሐፍ የተለያዩ ክፍሎች ያዕቆብ በሰዋዊ መንገድ ያሳለፋቸው ውጣ ውረዶች ናቸው። ያዕቆብ በእነዚያ የሕይወት ውጣ የሕይወቱ ጉዞዎች፡-

- አታላይ ነበር፤

- ከማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ላይ ማትረፍ የሚወድ ራስ ወዳድ ሰው ነበረ፤
- አስቸጋሪ ነገሮችን ከመጋፈጥ ይልቅ ይሸሽ ስለ ነበር እውነተኛ ሕይወት አልነበረውም፤
- በራሱ በመደገፍ ማንኛውንም ጉዳይ በራሱ የመፍታት አካሄድ ነበረው፤
- በመጨረሻም በምድራዊ ሀብት ደረጃ ባለጸጋ ሆኗል፤ነገር ግን ያልተፈቱ እንቆቅልሾች ነበሩት።

በዚህ ክፍል ያዕቆብ ወደ እናትና አባቱ ምድር ለመመለስ ጉዞ እያደረገ ነው። ከፊት ለፊቱ ኤሳው ወንድሙ እንደ ትልቅ ጋሬጣ በመንገዱ ላይ አለ። ይህንንም ጋሬጣ እንዴት እንደሚያልፍ ጭንቅ ስለሆነበት፣ በዘፍጥረት ምእራፍ 32 ላይ አንዴ ይጸልያል፣ አንዴ በእጅ መንሻ ለማምለጥ ይዘይዳል። ከፊት ለፊቱ ያለውን አስቸጋሪ ሁኔታ ለማለፍ የሚችለውን ያህል መፍትሔ እያበጀ ነው ያለው። ነገር ግን ይህ ሁሉ ዝየዳ መጨረሻ ላይ እንደማይጠቅመው ከተረዳ በኋላ ይመስለኛል፣ እጅግ አስደናቂ እርምጃዎችን መውሰድ የጀመረው፡-

- አብረውት ያሉትን ሁሉ ከፊት አስቀድሞ የያቦቅን ወንዝ አሻግሮአቸው ለብቻው ቀረ። ያቦቅ ማለት ራስን ባዶ ማድረግ ማለት ነው፤
- ካንድ ሰውም ጋር እስከ ንጋት ይታገል ነበር። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይህ ሰው ኢየሱስ ነው ይላሉ፤

- ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ ሲለው ያዕቆብ *"ካልባረክሽኝ አልለቅህም"* (ቁ.26) ብሎ ውስጣዊ መሻቱን ገለጸ፤ እጅግ በሕይወታችን የሚያስፈልገን ድንቅ ውሳኔ እና ጸሎት!

- ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ማንነቱን ተናገረ። ሰውየው "ስምህ ማን ነህ?" ሲለው ያዕቆብ ነኝ አለ፤ ያዕቆብ ማለት አታላይ ማለት ነው። ስለዚህም እውነተኛ ለውጥ ፈላጊም እንደሆነ አስመሰከረ።

ይህ ያዕቆብ የታገለው ትግል፣ ኢየሱስ በጌተሰማኒ ከጸለየው እና ራሱን ለኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ ለመስጠት፣ካማጠበት እና ከቃተተበት የጸሎት ትግል ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይናገራሉ። ኢየሱስ ከዚያ ምጥና መሥዋዕትነት በኋላ ያፈራውን ፍሬ ነቢዩ ኢሳይያስ *"ነፍሱን ስለ ኃጢአት መስዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል ዕድሜውም ይረዝማል የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፤* ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን *ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሸከማል።"* (ኢሳ.53፥10-11) ብሎ ገልጾታል።

ያዕቆብም ከዚያ መንፈሳዊ ትግል የተነሣ ስሙ ተለወጠ። እስራኤል ተባለ። እስራኤል ማለት *"ከእግዚአብሔር ታግሎ ያሸነፈ/ Triumphant with God"* ወይም *"who prevails with God"* ማለት ሲሆን፣ ከዚያ አስደናቂ ትግል በኋላ ሲመሰክርም *"እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት ሰውነቴም ድና ቀረች"* (ቁ.30) ብሎ ውጤቱን ተናግሯል። ዘፍጥረት ምዕራፍ 33 ላይ እንደምናየው ከኤሳውም ጋር በሰላም ነው ተሳስመው የተለያዩት፤ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ስንስማማ፣ ጌታ ጠላቶቻችን ከእኛ ጋር እንዲስማሙ

ማድረግ ይችላልና (ምሳሌ 16፥7)።

ያዕቆብ የወሰዳቸው እርምጃዎች እግዚአብሔርን በሕይወቱ ፊት ለፊት እንዲያይ አድርገውታል። በእኛም ሕይወት እንዲህ ዓይነት ጊዜዎች እንዳይኖሩን ራሳችንን መከልከል፣ የጠለቀ ግንኙነት እንዳይኖረን ያደርጋል። ያለ እውነተኛ መንፈሳዊ ትግልም ለውጥ የለም። በእርሱ ፊት ራሳችንን ባዶ የምናደርግበት፣ በፊቱ ወድቀን እውነተኛ መዳሰስ እንዲመጣ፣ ፊቱን ከምር የምንፈልግባቸው ጊዜያት ያስፈልጉናል፤ አንዴ ሳይሆን በርከት ያሉ ጊዜያት! ጥቂት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ተደጋግሞ!

ሁላችንም የምንታገልባቸው ብዙ ነገሮች አሉን። የአብዛኛዎቻችን ሕይወት ከያዕቆብ ጋር በሚገባ ይመሳሰላል ብዬ አምናለሁ። የያዕቆብ ልቡ፣ አካሄዱ እና ስሙ እንደተለወጠ ጌታ አምላክ ሊለውጠንና የፍሬ ሰዎች ሊያደርገን ይፈልጋል። ነገር ግን አንድ ነገር ከእኛ ይፈልጋል ብዬ አምናለሁ፤ በበቂ ሁኔታ ለእርሱ መገኘታችንን፣ ለመለወጥ ፈቃደኝነታችንንም ጨምሮ!!

*“ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ አሸነፈ”* የሚለው ሐሳብ እግዚአብሔርን ማሸነፉ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መሰጠቱ እና መገዛቱ ነው እንደ ማሸነፍ የተቆጠረለት። ታሪኩ ላይ እንዳየነው፣ ያዕቆብ እውነተኛ መንፈሳዊ ለውጥን ፈለገ። እግዚአብሔር በሕይወታችን የበላይ መሆኑም የአሸናፊነታችን ሁሉ ምንጭ ነውና፣ ያዕቆብ “ከሰውም ከእግዚአብሔርም ጋር ታግለህ አሸነፍህ” ተባለ። የወሰዳቸው እርምጃዎቹ እና ያሳለፈው ያ ድንቅ የሌሊት ትግል፣ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዲያይ አደረገው።

እኛም በእንደዚህ ዓይነት ውሳኔና ራብ በፊቱ ብንሆን እና ሳናቅማማ እራሳችንን በፊቱ ብንጥል፣ እናየውና ተለውጠን እንቀራለን ብዬ አምናለሁ። አለበለዚያ ግን ሕይወት የሌለን፣ ሃይማኖተኛ፣ ግብዝ፣ አስመሳይ እና ከእውነት የራቅን ሆነን ነው የምንቀረው። በተቃራኒው ደግሞ በላይ በተጠቀሱት መንፈሳዊ ሂደቶች ውስጥ በእውነት ስናልፍ እምነታችን ይጠነክራል፣ያድጋል፣ ብሎም አስመሳይነት፣ ግትረኝነትና እልህ ከሕይወታችን ይወገዳሉ። እውነተኛ የልብ መሰበርና ትሕትናም መገለጫችን ይሆናሉ።

አሳዛኙ ነገር በሕይወታችን ብዙ ጊዜ *"ኤሳው"* እንዲለወጥ ነው የምንፈልገው፤ ቢሆንም አንዱ *"ኤሳው"* ከሕይወታችን ቢወገድ ሌላው ይመጣል በምድር እስካለን ድረስ። ነገር ግን እግዚአብሔር በማንኛውም የሕይወት ውጣ ውረድ ነጥሮ የሚወጣ ማንነትን ሊሰጠን ስለሚፈልግ፣ እኛን ከውስጥ መለወጥ ነው የሚፈልገው። ለዚህ ደግሞ የእኛን ፈቃደኝነት ይፈልጋል። ስለዚህ "እሺ እነሆኝ" ብንለው ነው የሚያዋጣን። "እጆህ ይሥሩኝ ያበጃጁኝ" ብንለው ነው የሚጠቅመን፤ መሥራትና መለወጥ ያውቅበታልና! ቅዱስ ቃሉ *"እንዳላሸነፈውም ባየ ጊዜ የጭኑን ሹልዳ ነካው"* (ቁ.25) እንደሚል ሰባብሮ የራሱ ገንዘብ ሊያደርገን፣ ደግሞም ትሑት አድርጎ የሚጠቅም የክብር ዕቃ አድርጎ ሊሠራን ይመኛልና እንፍቀድለት።

በመጨረሻም እጅግ ለጸሎት ሕይወቴ መሠረት የሆነኝ ሐሳብ ላይ ልናገር እና ጽሑፌን ልጨርስ። ያዕቆብ ካደረጋቸው እርምጃዎች እጅግ የሚያስደስተኝ *"ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ"* (ቁ.24) የሚለው ሐሳብ ነው። ያዕቆብ በዚያች አመሻሽ ቀን በሐሳብ እና በጉልበት ሊረዱት የሚችሉ

ሰዎችን ሁሉ አሻግሮ ለብቻው ሆነ። እውነተኛ ውስጣዊ ለውጥን ፈልጎአልና ውጫዊ ከበባንና ግርገርን አስወገደ። ትልቅ ውሳኔና እርምጃ!

በዚህ ግርግር በበዛበት እና የሰውን ቀልብ በተለያየ መልኩ የሚስቡ ነገሮች በበዙበት ዓለም፣ ብቻን በመሆን ለጌታ መገኘት የሚቻልባቸው አጋጣሚዎች የጠበቡ ናቸው። ቢሆንም እንደ አጋጣሚ እንደዚህ ዓይነት ጊዜዎች ሲገኙ መታለፍ የለባቸውም እላለሁ። ጨክኖም እነዚህን ጊዜዎች ማመቻቸት ማስተዋል ነው። በእነዚህ ጊዜዎች የምናሳልፋቸው በርከት ያሉ ሰዓታት፣ ወደ ፊት የሚኖረንን ሕይወትና አገልግሎት በእጅጉ ይወስኑታልና፣ ያለመሰሰት እራሳችንን ከእግሩ ስር እንጣል። እግዚአብሔር ሆይ እንደ ያዕቆብ በፊትህ የከበረን ጊዜ ስጠን!!

**መዝጊያ ምንባብ፡-** *"እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ። አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ።"* (ፊል.3፥10-12)

# ለውጠት

የቃሉ ብርሃን ቦግ ሲል፣ የልባችንን ደጅ ሲከፍተው

ያልተረዳነውን ግድፈት፣ ባልቃኘነው መንገድ ስናየው

የቃሉ ፍቺ ተፈልቅቆ፣ ውስጣችንን ሲያበራ

የምንሄድበት መንገድ ሲገባን፣ ከፊት ይልቅ ሲጠራ

መላምቶች ሲቆሙ፣ አስተውለውን ስንራመድ

ምልልሳችን ሲቀና፣ እየደረቀ መንጋደድ

ከፋትንና ከፉውን፣ አንቅረን ስንተፋው

ምርጫችን ሲስተካከል፣ የበደል ጉዞን ስናቆመው

የምሩን መኖር ስንጀምር፣ ከድንብርብር ስንወጣ

ደስ ይለናል በለውጡ፣ አዲስ መታዘዝ ሲመጣ!

## የመከራ እሳት እና የእኛ አቀባበል

*"ቀላል ሕይወት እንዲኖርህ አትጸልይ፤ ተግዳሮት መቋቋም የሚችል ብርታት እንዲኖርህ ጸልይ።/ Do not pray for an easy life, pray for the strength to endure a difficult one"* — ብሩስ ሊ

ወደ ሕይወታችን የማይመጣ የፈተናና የመከራ ዓይነት የለም። መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና አብዛኛዎቹ የእምነት አባቶች በብዙ ፈተናና መከራ ውስጥ እንዳለፉ እናስተውላለን። ያለፉባቸውን ስቃዮችና ከባድ የጠጧቸውን የመከራ ጽዋዎች በአእምሮ ማሰቡ ራሱ ከባድ ይመስለኛል። ቅዱስ ቃሉ *"...የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፤*

*ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ....።"* (ዕብ.11፥35-37) እያለ ዘከሯቸዋልና!

ለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል "ወዳጆች ሆይ፥ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ፥ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ።" (1ጴጥ.4፥12-13) ብሎ የሚመክረው። አዎ፣ መከራን በእግዚአብሔር ቃል መነጽር ካየነው በሚገጥሙን ተግዳሮቶች ሁሉ እንደምንጸናና አትራፊዎች እንደምንሆን አምናለሁ። እያንዳንዱን ፈተና በእግዚአብሔር ጸጋ እና ምሪት ተደግፈን እና ኢየሱስን እያየን ከተጋፈጥነው፣ እምነታችን እየጠነከረ ይሄዳልና። ወደ ፊትም ተመሳሳይ ነገሮች ቢገጥሙን አዲስ አንሆንም፤ ፈተናው ልምድን ይሰጠናልና፤ የምንወጣበትን አቅምና ጥበብ ይጨምርልናልና።

በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ወንጌል እጅግ ከፍ ያሉ መሥዋዕቶችን እንደ ከፈለ በመልእክቶቹ ውስጥ እናስተውላለን። እነዚያን መከራዎች በእግዚአብሔር ጸጋ ተቋቁሟቸው እንዳለፈም ነው የጻፈው። በውስጣችን እግዚአብሔር ካስቀመጠው መዝገብ የተነሣ ሊደርሱብን የሚችሉትን የመከራ ዓይነቶችን እንደሚከተለው ዘርዝሯቸዋል፡-

- እንገፋለን፣

- እናመነታለን፣ እንሰደዳለን፣
- እንወድቃለን፣
- የኢየሱስን ሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን፣
- እናም ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለን (2ቆሮንቶስ 4፥7-10) ።

እርግጥ ነው፣ የመከራው እና የፈተናው መጠን እንደ እንቅስቃሴያችን መጠን ቢወሰንም፣ ክርስቲያን ከመሆናችን የተነሣ ብዙ ነገሮች ይደርሱብናል። በተለይ አብዝተን ለወንጌል የምንሮጥ ከሆነ የተግዳሮቱና የስቃዩ ብዛት እንደ እዚያው ያይላል። ጌታን ለማገልገል ደፋ ቀና በምንል ክርስቲያኖች ላይ ሰልፉ እጅግ ብርቱ ነው። ጠላት በተለያየ መንገድ ተስፋ ለማስቆረጥ እና ሩጫችንን እንድናቆም የማይልከውና የማያመጣው ተግዳሮት የለም።

የሐዋርያው ጳውሎስ በመከራ ውስጥ የነበረው ጽናት እጅግ ያስገርማል። መከራ ሲገጥመው የነበረው ምላሽ፣ *"...አንታክትም ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።"* (2ቆሮ.4፥16-17) የሚል ነበር እንጂ፣ ማለቃቀስና ማጉረምረም አልነበረም። በነገራችን ላይ *‹‹የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ››* የሚለው ሐረግ የሰውነታችን መጎሳቆል ብቻ የሚወክል ሳይሆን፣ ማንኛውንም የምናጣቸውንና የሚጎድሉብንን ውጫዊ ነገሮችን ሁሉ ይወክላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን፣ ትኩረት አድርገን መሥራት ያለብን የውስጡ ሰውነታችን ላይ እንደ ሆነ ነው አጽንዖት የሰጠው። ልክ ነው፣ የውስጡ ሰውነታችን ላይ ነው ትኩረት አድርገን ኢንቨስት ማድረግ ያለብን። በተለያዩ ጫናዎች ውስጥ ስናልፍ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በቂ ኅብረት እያደረግን ከከበረው አምላካችን ጋር

ከተጣበቅንና በጸሎት ከተጋን፣ የውስጡ ሰውነታችን እየታደሰና እየጠነከረ ስለሚሄድ፣ የጠለቀ ኅብረት ውስጥ እራሳችንን እናገኘዋለን። የዚያም ውጤቱ ጌታ ኢየሱስን ልዩ በሆነና በጨመረ መንገድ እያወቅነው እንድንሄድ ያደርገናልና ነው።

ሮሜ.5፥3-5 ያለው ምንባብ የመከራን መንፈሳዊ ጥቅም እንዲህ ባለ የውጤት ተዋረድ ያስቀምጠዋል፡-ፈተና----›ጽናት----›ጠባይ/መገለጫ ባሕርይ-----›ተስፋ!

ተስፋ የምናደርግበት ይህ ሕይወት በፍጹም የሚያሳፍር አይደለም፤ በጭራሽ ዝም ብለን በጨበጣ እየተነዳን የምንሄድበት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። የሚጨበጥ የውስጥ ማስረጃ ስላለው። እንዴት? ማረጋገጫ የሚሆነን የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር በሚታወቀን መልኩ በልባችን ፈስሷልና (ቁ.5)። በመከራ ማዕበል ስንናጥ ይህ መረዳት ነው የነፍሳችን መልሕቅ ሆኖ የሚያቆመን!

ወደ ሕይወታችን የሚመጣው ፈተናና ተግዳሮት ያለንን እምነትና ጽኑነት በሚገባ ይፈትሸዋል። ወርቅ በእሳት እንደሚነጥርና፣ በላዩ ላይ ያሉት የማይረቡ ነገሮች እንደሚወገዱ ሁሉ፣ የሚመጣው የመከራ እሳት አላስፈላጊ ነገሮችን እየጣልን ከጌታ ጋር የበለጠ እንድንጣበቅ ያደርገናል። ካለንበትም የመከራ ሁኔታ ስንወጣ፣ ያለን ምሥጋና፣ አምልኮና ምሥክርነት ልዩ ይሆናል፤ የጌታን የማዳን እና የማጽናናት ክንዱን በሚገባ እናጣጥማለንና!

ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህንን ሐሳብ እጅግ በሚገርም መንገድ ገልጾታል፤ *"በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ*

*የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል።”* ብሎ። ምንባቡ እንደሚነግረን፣ ፈተናው እምነታችን እንዲጠነከር እና ከጌታ ጋር እንድንጣበቅ ትልቅ አጋጣሚን ፈጥሮልን ነው የሚያልፈው። ስለዚህ ያለው መንፈሳዊ ትርፍ ቀላል አይደለም። ስለዚህ ፈተናን በዚህ አተያይ (perspective) መመልከት እጅግ ይጠቅማል ብዬ አስባለሁ። እርግጥ ፈተናው ለጊዜው ያሳዝነናል፤ ልባችን ይሰብረዋል፤ እንዳውም የማንነሣ እስኪመስለን ተስፋ ልንቆርጥም እንችላለን። ቢሆንም ግን መከራው ለወደፊቱ ጉዟችን፣ አስፈላጊ የሕይወት ቅመሞችን ሰጥቶን እንደሚያልፍ አያጠያይቅም።

በራሴ ሕይወት አንገት የሚያስደፉ ብዙ ችግሮች ደጋግመው ደርሰውብኛል። በእነዚያ ጊዜዎች እንደ ሰው በኃይል አዝኛለሁ። ተስፋ እስከ መቁረጥ የደረስኩባቸውም ጊዜያትም ነበሩ። ወደ ልቤ ተመልሼ እርሱ የመፍትሔ አምላክ መሆኑን እና ከእነዚያ ጉዶች ሊያወጣኝ እንደሚችል በማስተዋሌና በመረዳቴ አትርፌአለሁ። እራሴን በጸጋው ዙፋን ፊት “እንደ ፈለግህ አድርገኝ” ብዬ በመጣሌ፣ ከብዙ ሰዋዊና ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ እርምጃዎችም ተቆጥቤአለሁ። ደግሞም ችግሩ እስኪያልፍ በጸሎት መንፈስ ውስጥ በመሆኔና ከቃሉ ጋር በቂ ጊዜን በማሳለፌ፣ የሚገርመውን የማጽናናት ክንዱን፣ ቸርነቱንና ምሕረቱን በሚገባ ደጋግሜ አይቻለሁ። ለመሆኑ እርሱን ማን ይመስለዋል? እንደ እሱ አጽናንቶና ሕይወትን አድሶ እንደገና የሚያቆምስ ማን አለ?

ልላችሁ የምችለው አንድ ነገር ነው። በእርግጠኝነት አብዛኞዎቹ መከራዎቻችን ያልፋሉ። “አሁን በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ሳለን ምን

እያደረግን እንቆይ?” የሚለው ነው ትልቅ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባው ቁም ነገር። በዚህ ጊዜ የመጽናናት አምላክ እንደ ሐሳቡ፣ ከእሳቱ ውስጥ እስኪያወጣን ድረስ ሙሉ በሙሉ የጸሎት ክተት ማወጅ አለብን ብዬ ነው የማምነው። ሁለተንተናችን ጸሎት መሆን አለበት!

በእነዚህ ጊዜያት ጠንከር ያሉ ጸሎቶችን ለረጅም ሰዓታት መጸለይ እጅግ ይጠቅመናል። ለምን ቢባል በሥጋችን እና በነፍስ ትግል ፈተናውን መቋቋም አንችልምና ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሰዓት ነው ከምንም ጊዜ በላይ የእግዚአብሔር ጸጋና ጥበብ የሚያስፈልገን። በተለይ የእግዚአብሔር ጸጋ የምናልፍበት እሳት እንዳይሰማን ያደርገናል። ለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ *“እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ።”* (ማቴ.11፥28) የሚለው፤ በችግር ውስጥ ተከብበን እንኳ እያለ፣ ማረፍ እንደሚቻል ሲያሳየን።

በግሌ እዚህ ቃል ውስጥ ያለው በረከት ታላቅ ነው እላለሁ። በትንሹም ቢሆን ቀምሸዋለሁና እጅግ ደጋግሜ የማነሣውና የምወደው ቃል ነው። አዎ፣ ማሳረፍ ብቻ ሳይሆን ይገላግል። ስለዚህ በራስ ከመታገል እና ሰዋዊ መፍትሔዎችን በመዘየድ የዕረፍት ዘመናችንን ከማርዘም ይልቅ፣ በልዑሉ መጠጊያ ውስጥ መጥተን ዕንረፍ፤ ሁለንተናችንንም ለእርሱ እንስጥ!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*“እስራኤልም ሆይ፥ የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ፤ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ። በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፥ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፥ ነበልባሉም አይፈጅህም።”* (ኢሳ.43፥1-2)

# የንስሓ ጥቅሙ

*“የኃጢአት መኖርና አለመኖር አይደለም የእግዚአብሔር የሆንነውን ከባዶ ለፋፊዎች የሚለየው፣ በሠራነው ኃጢአት መጸጸት መቻላችን ነው።/ It is not the absence of sin but the grieving over it which distinguishes the child of God from empty professors” ኤ.ወ.ፒንክ*

ንስሐ ማለት ወደ እግዚአብሔር በሚገባ መመለስ ሲሆን፣ እንደገና ወደ ኋላ ላለመመለስ መወሰንና መሰጠትም ጭምር ነው። ንስሐን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን። የመጀመሪያው የንስሐ ዓይነት፣ ሥር ነቀል ዋጋ ከፍለን ወደ ጌታ ለመመለስ የምንከፍለው እርምጃ ነው። ይህ መንፈሳዊ እርምጃም፣ ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃኑ እንድፈልስ ያዘጋጀናል። ከነበርንበት ማጥ አውጥቶ ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት እንድንገባ ልባችንን ያመቻቻል። ይህ የንስሐ ዓይነት በሕይወታችን ትልቅ እና ወሳኝ እርምጃ ከመሆኑም የተነሣ፣ ጨክነን ካደረግነው ወደ ሕይወታችን የሚመጣው መንፈሳዊ ለውጥ ቀላል አይደለም። የመጀመሪያው ለውጣችንም፣ አእምሮን የሚያልፍ ሰላም ይሆናል (ሮሜ.5፥1-2)።

ሁለተኛው የንስሐ ዓይነት ወደ ጌታ ኢየሱስ ከላይ በተጠቀሰው ውሳኔና እርምጃ አንዴ ወደ ቤቱ ከመጣን በኋላ፣ ወደ እርሱ እስከምንሄድበት ቀን ድረስ ዕለት ዕለት የምናከውነው የክርስትናችን ዋና መሠረት ነው።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው እግዚአብሔር የሚከተሉት ሁለት ነገሮች

ያሉትን ሰው በእጅጉ እንደሚባርክ የተናገሩት ነገር ውስጤ ታትሞ ቀርቷል። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው (repentant and expectant heart)፡-

- በንስሐ የሚመለስ ልብ፣
- ጌታን በመጠባበቅ የተሞላ ልብ።

እውነተኛ ንስሐን የሚለማመድ ሰው በሕይወቱ ለሚገርም በረከት የእግዚአብሔርን ልብ ያዘነብላል። ይህ ዓይነቱ ንስሐም ሕይወትን አድሶ ለማቆም ዋነኛው መንገድ ነው፤ የእግዚአብሔርን የማጽናናት ክንድ የምንቀምስበት መንገድ ነውና። መኪና እንደ ልብ እንዲንሸራሸር የተደፈኑት የዘይት ቧንቧዎቹ መጠረግ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ፣ ከተጠላለፍንባቸው እግዚአብሔርን ከሚያሳዝኑ ኃጢአቶች እና ርኩሰቶች፣ የምንጠራበት መንገድ ንስሐ ነው። ይህንን አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቃል *"በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።"* (1ዮሐ.1፥9) ይላልና!

እጅግ የሚደንቅ ቃል ነው። *"ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን"* የሚለው ቃል ላይ እንድታሰምሩልኝ እፈልጋለሁ። ከአንዳንድ ኃጢአት ሳይሆን እግዚአብሔርን ካሳዘንባቸው ማንኛውም ነገሮች ሁሉ እንደሚል እናስተውል። *"ሊያነጻን"* የሚለው ቃል ሊያጥበን፣ ሊፈውሰን፣ ሊያጠራን ወዘተ የሚል ትርጉም ይዟል። ይህ ምንባብ የመንፈስ ቅዱስን ውስጥን የማጽዳትን ኃይል እና የማሣመር ሥራ ነው የሚናገረው።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለነበሩ እስራኤላውያን *"ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ*

*ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።"* (ኢሳ.1፥18) ይላቸው ነበር። ይህ ምንባብ የንስሐን ውስጥን የመለወጥ ኃይል ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁለት በምንም መልኩ የማይገናኙ ነገሮችን እያወዳደረ እናያለን። እንደዚህ አስቀምጫቸዋለሁ፡-

❖አለላ (ደማቅ ቀይ)----------› አመዳይ (እንደ በረዶ ነጭ)

❖ደም (ደማቅ ቀይ) ----------› ባዘቶ (እንደ ሐር ነጭ)

ከላይ ያሉት ንጻጽሮች በምንም መልኩ እጅግ የተራራቁ ናቸው። ጽንፎች ናቸው ማለት ይቻላል። ምንባቡ በዚህ አነጻጽሮት ሊነግረን የፈለገው ነገር፣ ከልብ የተደረገ ንስሐ ውስጣችንን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ችሎታ ሊቀይር እንደሚችል ነው። እርግጥ ነው፤ ንስሐ ውስጣችንን የማጽዳት፣ የማሳመርና የማስተካከል ችሎታ ነው። ያንን የሚያደርገው ግን መንፈስ ቅዱስ ነው። ከጌታ ኢየሱስ ጋር ያለንን ያልተስተካከለ መንፈሳዊ ኅብረት በሚገባ የማስተካከል፣ የማስዋብና የማደስ ኃይል ያለው እርሱ ነው።

ንስሓ ማለት ምን ማለት ነው? ተብዬ ብጠየቅ መዝሙር 51 ነው ብዬ የምመልስ ይመስለኛል። የመዝሙር 51 መግቢያ ላይ እንደተገለጸው፣ *"ንጉሥ ዳዊት ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ፣ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ የዳዊት መዝሙር"* ብሎ ነው የሚጀምረው። ዳዊት ያንን እጅግ ከባድ የሆነ ኃጢአት ካከናወነና እና የግድያ ወንጀልን በኦርዮ ላይ ከፈጸመ በኋላ፣ ኃጢአቱን ሳይናዘዝ ከዓመት በላይ በላይ እንደ ቆየ የተወለደው ልጅ ዕድሜ ይነግረናል። እግዚአብሔር ነቢዩ ናታንን የላከው፣ ንጉሥ ዳዊት ኃጢአቱን የመናዘዝ አቅም ስላጣ ይመስለኛል።

ዳዊት በኃጢአት ውስጥ መሆን ያለውን የሕይወት አስቀያሚና ጎጂነት በመዝሙር 38፥4-10 ላይ *“አቤቱ፥ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፥ በመዓትህም አትገሥጸኝ። ፍላጻችህ ወግተውኛልና፥ እጅህንም አከብደህብኛልና። ከቍጣህ የተነሣ ለሥጋዬ ጤና የለውም፤ ከኃጢአቴም የተነሣ ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም። ኃጢአቴ በራሴ ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና፥ እንደ ከባድ ሸክምም በላዬ ከብዶአልና። ከስንፍናዬ የተነሣ ቍስሌ ሸተተ በሰበሰም፤ እጅግ ጐሰቈልሁ ተዋረድሁም፥ ሁልጊዜም በትካዜ እመላለሳለሁ። ነፍሴ ስድብን ተሞልታለችና፥ ለሥጋዬም ጤና የላትምና። ታመምሁ፤ እጅግም ተቸገርሁ፥ ከልቤ ውዝዋዜም የተነሣ ጮኽሁ። አቤቱ፥ ፈቃዴ ሁሉ በፊትህ ነው፥ ጭንቀቴም ከአንተ አይሰወርም። ልቤ ደነገጠብኝ፥ ኃይሌም ተወኝ፥ የዓይኖቼም ብርሃን ፈዘዘ።”* (መዝ.38፥1-10) ብሎ ዘርዝሮታል።

አዎ፣ ኃጢአት ጉስቁልና አለው፤ ኀፍረትና የውርደት ስሜት አለው፤ ጭንቀት አለው፤ ትካዜ አለው፤ ድካም አለው፣ ሕመምና ድንጋጤ አለው (እነዚህን ችግሮች ምንባቡ ውስጥ አንድ ባንድ ማየት ይቻላል)። ባጠቃላይ ሁከት ነው። ከላይ እንደጠቀስሁት፣ ዳዊት ለብዙ ወራት በእንደዚህ ያለ ከባድ ስሜት ውስጥ ሰንብቷል። እግዚአብሔር የምሕረት አምላክ ስለሆነ፣ ነቢዩ ናታንን ላከበትና ጉዱን ገለጠበት። ከዚያም ዳዊት በእንዴት ዓይነት የልብ መሰበር ውስጥ እንዳሳለፈ ነው መዝሙር 51 የሚነግረን። የጸለየውም ጸሎት ወደር የለውም፤ እጅግ የእግዚአብሔርን ልብ የሚያዘነብል ነበር። ይህን ክፍል ብዙ ጊዜ አንብቤዋለሁ። በእንደዚያ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ስሆን፣ መጀመሪያ የማነብበውም ክፍል ነውና በኃይል እወደዋለሁ።

በዚህ መዝሙር ንስሓ ውስጥን ለማንጻት እጅግ ጠቃሚ እንደ ሆነ

የሚያሳየን ቁጥር 7 ነው። ዳዊት *“በሂሶጵ እርጩኝ እነጻማለሁ እጠበኝ፣ ከበረዶ ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።”* ብሎ ነው አምላኩን የሚማጸነው፤ የውስጡን መቆሸሽ ተረድቶታልና። ይህ ምንባብ ከላይ ከጠቀስኩት ከኢሳይያስ 1፥18 ጋር ተመሳሳይነት አለው። አዎ በቅንነት እና እግዚአብሔርን በመፍራት የተጸለየ እውነተኛ ጸሎት፣ ከብዙ የከፋት ትርፍ ይገላግላል፤ ውስጥን ይለውጣል፣ ያስተካክላል፣ ይቀይራል፣ ያሳምራልም።

ዳዊት ላለበት መንፈሳዊ ሁኔታ መፍትሔውን በመዝሙር 51፥8 ላይ *“ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ የሰበርሃቸውም አጥንቶቼም ደስ ይላቸዋል።”* ብሎ ነው የሚገልጸው።

*“የሰበርሃቸው አጥንቶቼ”* የሚለው ሐረግ ሳነብብና ሳሰላስል፣ የተሰበረ አጥንት ምን ያህል እንደሚያም በራሴ ስለማውቀው፣ ያ ነው ወደ አእምሮዬ ቶሎ የሚመጣው (በሕክምና ሙያ ባገለገልኩባቸው ጊዜያት፣ በሠራሁባቸው ሆስፒታሎች በከባድ የአጥንት ሕመምና ስቃይ ያለፉ ሕሙማን ወደ አእምሮዬ ይመጣሉ)። ይህ አገላለጽ በኃጢአት የምንከፍለውን ዋጋ እጅግ በጣም ከባድ መሆኑን ያሳያል። ቃሉ *“የእግዚአብሔር መስዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው”* (መዝ.51፥17) ይላልና፣ ዳዊት በተሰበረ መንፈስ የእግዚአብሔርን ፊት ፈለገ፣ አነባ፣ ቃተተ፣ ጾመ፣ ብሎም በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ጣለ። ዳዊት አንዴ ብቻ ሳይሆን ደጋግሞ የጌታን የማዳን፣ የማጽናናት፣ የማደስና ደግፎ የማቆም ጉልበት፣ በሕይወቱ መቅመሱን በዚህ መዝሙር ውስጥ ያሉ እያንዳንዱ አገላለጾች በግልጽ ያሳያሉ፡፡

ምንድነው በዚህ ጽሑፌ ላሳይ የፈለግሁት ዋናው ቁም ነገር?

ለትምሕርታችን የተጻፉትን የንስሐ መርሖዎች በማስተዋልና ተግባራዊ በማድረግ፣ ግልብ ከሆነ የንስሐ ሕይወት ወደ ጠለቀ ኅብረት የሚከት የንስሐ ሕይወት እንዲኖረን ለማሳሰብ ነው።

በተለያዩ ስሕተቶች ከጌታ መንገድ መስመር ወጥተን ያለንና መንፈሱን የሚያሳዝኑ ነገሮችን እያደረግን ያለን ሰዎች መታደስ ከፈልግን ምን እናድርግ? የመጀመሪያው እርምጃ ዋጋ ከፍለን በፊቱ መሆን ነው። ከዚያም መንፈሱ እንደሚመራን በመሆንና በግልጽ ያደረግነውን በመናዘዝ፣ የመመለስ ርምጃዎችን መውሰድ ይኖርብናል። በመቀጠል በንስሓ ዙሪያ የተጻፉ ሐሳቦችን ከጌታ ቃል በማሰላሰልና በማጥናት፣ በጸጋው ዙፋን ፊት ሆነን ልባችንን ማፍሰስ ነው። ካስፈለገም እንደ ጴጥሮስ ምርር ብለን እናንባ፣ እናልቅስ። በአጭሩ የምር ተሐድሶ ፈላጊዎች እንሁን ማለቴ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ከ12 ዓመት ጀምሮ ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት *"ከስቃይዋ እንደ ዳነች በሰውነቷ አወቀች"* (ማር 5፥29) እንደሚል፣ በውስጡ መንፈሳችን የጌታ ፈውስ እስኪታወቀን ፊቱን እንፈልግ፤ ከወደቅንበትም አንነሣ። ኃጢአቶቻችንንም ስም ሰጥተን በእውነትና በቅንነት እንናዘዝ፤ እናም ሙሉ በሙሉ ለመመለስ እንወስን። ያኔ በሚያስደንቅ ምሕረቱ ይገናኘናል፣ ይጠግነናል፣ ያስደንቀል፣ መልሶም ያቆመናል። የ*"እንደ ገና"* አምላክ ነውና፣ እንደ ገና ሌላን ዕድል ይሰጠናል። ፍቅሩ እጅግ ታላቅ ነውና፣ ጸጋን ደርቦ ያቆመንና ካሰብነውና ከለመንነው በላይ የፍሬ ሰዎች ያደርገናል። ስለሆነም በዚህ መንፈስ ፊቱን እንፈልግ!

**መዝጊያ ምንባብ**፡- *"በደልን ይቅር የሚል፥ የርስቱንም ቅሬታ ዓመፅ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው? ምሕረትን*

*ይወድዳልና ቍጣውን ለዘላለም አይጠብቅም። ተመልሶ ይምረናል፤ ክፉታችንንም ይጠቀጥቃል፥ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል።”* (ሚክ.7፥18-19)

# የኃጢአት ሥርና መፍትሔው

*“ጸሎት ሰውን ኃጢአትን እንዲያቆም ያደርገዋል፤ ወይም ኃጢአት ሰውየውን መጸለይ እንዳይችል ያደርገዋል።/ Prayer will make a man cease from sin, or sin will entice a man to cease from prayer.”*
— ጆን ቡንያን

የኃጢአት መርዝ በውስጣችን አለ። ንጉሥ ዳዊት ከኃጢአት ጋር እንደ ተፈጠርን ተናግሯል (መዝ.51፥5)። ልክ እንደ ማግኔት ሕግ ሁለንተናችን ወደ ክፋት በመጎተት፣ ከእግዚአብሔር እንድናፈነግጥ ይስበዋል። በእንግሊዝኛው *‹‹indwelling sin››* ተብሎ ነው የሚታወቀው፤ በውስጣችን አብሮን ነዋሪ መሆኑን ለመግለጽ። ለዚህ ነው በጎን ከማድረግ ይልቅ ክፋትን ማድረግ የሚቀለን። እግዚአብሔር በምሕረቱ አስቦ ካልሳበን በስተቀር፣ በውስጣችን ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት የሚሻ ልብ የለንም። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ያንን በግልጽ አስቀምጦታል፤ *“ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይ የለም፤እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም፤ ሁሉም ተሳስተዋል በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም አንድ ስንኳ የለም።”* ብሎ! ይህ ነው ትክክለኛ ማንነታችን። ውጫችን የእምነት ሰው ቢመስልም፤ ውጫችን የሞራል ሰው ቢመስልም፣ እግዚአብሔር በቸርነቱ

ካልሳበንና ካላወጣን በስተቀር፣ ከዚህ ማጥ የመውጣት አቅሙም ሆነ ዝንባሌውም የለንም።

አንድ የእግዚአብሔር *ሰው "በግብዣ ብቻ ወደ እርሱ እንድንመጣ ብንጋበዝ ሁላችንም እንጠፋ ነበር"* ብለዋል። በዕዝራ መጽሐፍ እግዚአብሔር *"የሕዝቡን መንፈስ አነሣሣ"* (ዕዝ.1፥5) እንደሚል፣ የሞተውን መንፈሳችንን ሕይወት በመስጠት፣ ድነትን የሚሰጠን እሱው ነው፤ *"መፈለግንም ማድረግንም በእኛ ውስጥ የሚሠራው"* (ፊል.2፥13) ራሱ ነውና። የተወደደችው ሰዓት ስትመጣ ልባችን ለጥሪው ያነሣሣል። ይህም የሚያሳየን ሰው ወደ ጌታ ለመምጣት ያለበትን የተጋረጠ የውስጥ አደጋ ነው። ምሕረቱ ብዙ ነው እንጂ ብዙዎቻችን የት ነበርን? እውነቱን ነው የምለው፣ ይህ በሚገባ ሲገባን በኃይል አመስጋኞች እንሆናለን።

ኃጢአት ብዙ ውጤቶች አሉት። መዝሙር 38፥3-10 የኃጢአትን ውጤቶች በሚገባ አስፍሮልናል ብዬ አስባለሁ። በእያንዳንዱ ጥቅስ ላይ የተዘረዘሩትን ትኩረት ሰጥታችሁ ብታጠኑ፣ በኃጢአት ሊመጡብን የሚችሉትን አደጋዎችና ፍሬዎች በሚገባ መገንዘብ ትችላላችሁ። ዳዊት በዚህ ክፍል ውስጥ፡-

- ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም ይላል፤
- ቁስሌ ሸተተ፣ በሰበሰም በማለት የውስጥ መንፈሳዊ ሁኔታውን በግልጽ ሳይደብቅ ይናገራል፤
- ጎሰቆልሁ ተዋረድሁም በማለት የኃጢአትን የማሸማቀቅና የመከራ መዘዝ ያሳየናል፤
- በማኅበራዊ ሕይወቱ ስድብን እንደጠገበም ይመሰክራል፤

- ጤና እንደሌለው ወይም እንደታወከ ይገልጻል፤
- በድንጋጤ ውስጥ እንዳለም አልሸሸገም፤
- ኃይል እንዳልቀረለትም ተናግሯል፤
- ማየት እንደተሳነውም ጽፏል፤
- ከነዚህም የተነሣ ማኅበራዊ ሕይወቱ እንደተበላሸ እና ዘመድ አዝማድ እና ጓደኛ እንደራቀው መስክሯል።

ሙሉ ምዕራፉን ስናነብ የምንገነዘበው፣ ኃጢአትንና ኃጢአት የሚያመጣውን መዘዝ ነው። ማለትም ኃጢአት ፡-

- ነፍስን ያደክማል፤
- ኃይልን ያሳጣል፤
- ስብራትን ወደ ሕይወታችን ያመጣል፤
- መንፈሳዊ ዕይታችንን ይጋርዳል (መዝ.40፥12)
- ማኅበራዊ ሕይወታችንን ያበላሻል።

ሰው በተፈጥሮው የኃጢአት ባሪያ ነው (ዮሐ.8፥36)። ለዚህ ነው ከዚህ ባርነት ለመላቀቅ፣ ዳግመኛ መወለድ የሚያስፈልገን (ዮሐ.3፥3-8)። ለዚህ ነው የልብ መገረዝ የሚያስፈልገን (ቈላ.2፥11-13)። ለዚህም ነው ሐዋርያው ዮሐንስ *"ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ዘሩ በእርሱ ይኖራልና ከእግዚአብሔር ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።"* (ዮሐ.3፥9) ብሎ የጻፈልን። ስለዚህም ነው ዳግመኛ ስንወለድ ድንገት ተሳስተን እንጂ፣ ወድደን፣ ደስ ብሎን፣ ተስማምተን እና ውስጣችን ፈቅዶ ያለ ምንም ወቀሳ ኃጢአትን መሥራት የምናቆመው። እንዳውም

በሕይወታችን እሱን ደስ ለማሰኘት የምንቀና ሰዎች እንሆናለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን መጽሐፍ፣ ዳግመኛ ከመወለዳችን በፊት ያለንን መንፈሳዊ ሁኔታ ግሩምና ግልጽ በሆነ መንገድ ይገልጸዋል። *"በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ስልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።በእነዚህ ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበር እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።"* (ኤፌ.2፥1-2) ብሎ!

ምንባቡ የሰው ልጅ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ ነው የሚያበስረን። የሥጋችንንና የልቡናችን ፈቃድ መሪያችን፣ አለቃችን ደግሞ በአየር ላይ የሚሠራው የመንፈስ አለቃ ነው። ወደ ጌታ ኢየሱስ በትሕትና እጅ ወደ ላይ ብንል ግን፣ ከዚህ ዓይነት ዘግናኝ ወኅኒ ውስጥ በማውጣት ነው የሚገላግለን። ኢየሱስ ወደ እዚች ምድር በዋናነት የመጣውም ለዚህ ተልዕኮ ነውና። የእግዚአብሔር ቃል ስለ ኢየሱስ ተልዕኮ ሲናገር፡- *"እኔ እግዚአብሐር በጽድቅ ጠርቼህማለሁ፤ የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ።"* (ኢሳ.42፥6-7) ብሎ ይናገራልና!

ይህ ክፍል ወደ ጌታ ያልመጣ ሰው የኃጢአት ወኅኒ ውስጥ እንዳለ ነው የሚነግረን፤ ዕውሮችም ጭምር እንደሆንን። ነገር ግን ከእሱ ጋር ስንስማማ፣ *«እነሆኝ»* ብለን ራሳችን ለዚህ የሕይወት ጌታ

ስንሰጥ፣ ከዚህ ኃይለኛ የግዞት ሰፈር እንደሚያወጣን አምናለሁ፤ አውጥቶኛላ! ያኔ ነው ሁሉ ነገር ግልጥልጥ ብሎ የሚገባን፤ ዓይኖቻችንም ተከፍተው የት እንደነበርንም የምናስተውለው። በዚህ ድንቅ ድነትም፣ የነጻነት አየር መተንፈስ እንጀምራለን። ከወቀሳ እና ከኀፍረት እንድናለን። ማኅበራዊ ግንኙነታችን ይታደሳል። መለኮታዊ ሰላምና ደስታን ምን እንደሚመስልም የመቅመስ ባለ ዕድለኞች እንሆናለን።

ተግተን ከቀጠልንም፣ ወደ ሰፊ ስፍራ እየወጣንና (መዝ.18፥19) እየተለወጥን መምጣታችን አይቀሬ ይሆናል። ዳዊት እጅግ ከብዙ ድሎቹ በኋላ *"ክብሬ ትዘምርልህ ዘንድ ዝምም እንዳትል ልቅሶዬን ለደስታ ለወጥህልኝ፤ ማቄን ቀድደህ ደስታን አስታጠቅኸኝ።"* (መዝ.30፥11) ብሎ እንዳዜመው ኀዘናችንና ትካዜያችን ሁሉ በደስታና በዝማሬ ይቀየራል። ይህንን ስጽፍ የራሴን ሕይወትም አስቤ እንደ ሆነ ልብ በሉ። ዝም ብሎ ወሬ ሳይሆን በተግባር በሕይወቴ ያየሁትንና የቀመስሁትን ነው የምናገረው። በድፍረትም ሕያው ምስክር ነኝ እላለሁ። ስለዚህ ሳታቅማሙ በፊቱ በትሕትና ኑና ውደቁ ይገላግላችኋል፤ በቃላት ሊገለጽ የማይችል ነጻነትን ያጎናጽፋችኋል!!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*"የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥ ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል።....በአመድ ፋንታ አክሊልን፥ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፥ በኀዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል።"* (ኢሳ.61፥1-30)

# የምናልፍባቸው ጎዳናዎች

*“እጅግ ብዙ ጊዜ ምንም መሄጃ እንደሌለኝ አጥብቄ በመረዳቴ ጉልበቴን ለጸሎት አጥፌአለሁ–ደጋግሜ። የራሴ ጥበብና ችሎታዬ ሁሉ ለዚያ ቀን ረብ እንዳልነበረው ገብቶኝ ነበርና።/ I have been driven many times upon my knees by the overwhelming conviction that I had no where else to go. My own wisdom and that of all about me seemed insufficient for that day.” —አብርሃም ሊንከን*

እግዚአብሔር እኛን ለመሥራት ወደድንም ጠላንም በተለያዩ የሕይወት ጎዳናዎች ያሳልፈናል። የልቅሶ ዘመን አለ፤ የመከራ ዘመን አለ፤ የጭንቅ ዘመን አለ፤ የእጦት ዘመን አለ ደግሞም የዕረፍት እና የበረከት ዘመን አለ። ለዚህ ነው ቅዱስ ቃሉ *“በልቅሶ ሸለቆ በወሰነው ስፍራ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና ከኃይል ወደ ኃይል ይሄዳሉ።”* (መዝ 84፥6) በማለት የልቅሶ ወራት እንዳሉ የሚያበስረን።

እግዚአብሔር ሊሠራን፣ ሊያበጃጀን (መዝ.119፥73) እና ከእኛ ላይ አላስፈላጊውን እንደ እልህ፣ በገዛ ፈቃድ መሄድ እና ትዕቢትን ሊያራግፍ እና ሊያሸነቅጠን በብዙ ነገሮች ውስጥ ያሳልፈናል። መዝሙር 66፥10-12 *“አቤቱ ፈትነኸናልና፤ ብርን እንደሚያነጥሩት አንጥረኸኛልና። ወደ ወጥመድ አገባኸን፤ በራሳችን ላይ ሰውን አስረገጥኸን፤ በእሳትና በውኃ መካከል አለፍን፤ ወደ ዕረፍትም አወጣኸን።”* ይላልና!

አዎ፣ የፈተና፣ የንቀት፣ የስድብ እና የመከራ ዘመን አለ። የጌታ ጊዜ ሲደርስ ደግሞ ግሩም የሆነ የዕረፍት ዘመንም ይመጣል። የፈተናው እና የመከራው ዘመን ያማል፤ አንገትን ያስደፋል፣ ያስለቅሳል፣ ግራ ያጋባል ወዘተ። ሆኖም ግን በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ ከእሱ ጋር ተጣብቀንና አጥብቀን የጌታን ፊት የምንፈልግ ከሆነ፣ እግዚአብሔር እንደሚደግፍ፣ እንደሚያጽናና፣ እንደሚረዳ በተግባር ደረጃ የምናውቅበት ጥሩ አጋጣሚ ይሆንልናል።

በሆሴዕ ምዕራፍ ሁለት፣ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከነበሩበት የሞራል ውድቀት ለመመለስ ወደ ምድረ በዳ ሊወስዳቸው እንዳሰበ እንገነዘባለን። *"አባብላታለሁ ወደ ምደረ በዳም አመጣታለሁ፤ ለልብዋም እናገራለሁ።"* (ሆሴ. 2፥16) በማለቱ! *"ለልብዋም እናገራለሁ"* የሚለውን ቃል ሳስበው ያስደንቀኛል። *"በመከራ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ከወትሮው ጮክ ብሎ ይሰማል"* ብለዋለ ሲ.ኤስ ሉዊስ። ትክክል ነው፤ በመከራ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ስንሆን፣ በሚገባ ስንጠጋውና በቂ ጊዜ ከእርሱ ጋር ስናሳልፍ፣ ድምፁን የመስማት ስሱነታችን (our sensitivity/ receptivity) ከፍ ይላል። የእግዚአብሔር ድምጽ ሲመጣ ደግሞ ልዩ ነውና (መዝ 29፥1-11 ያንብቡ)፣ በሕይወታችን ብዙ ለውጦችን እናያለን። ለመጥቀስ ያህል፣ ጌታ ለልባችን ሲናገረን እምነታችን ያድጋል፣ ይጠነክራል፣ ሰላማችን ይበዛል፣ ሕይወታችን ይታደሳል፤ መንፈሳዊ ሕይወታችን ይለወጣል፣ ያድግማል።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ምድረ በዳ አባብሎ ከከተታቸው በኋላ በሕይወታቸው ስለሚመጣው አስገራሚ መንፈሳዊ ልውጠት (transformation) እንዲህ ብሎ ነው የሚናገረው፡- *"ከዚያም የወይን ቦታዋን የተስፋ በርም እንዲሆንላት የአኮርን ሸለቆ እሰጣታለሁ፤ በዚያም*

*ከግብጽ ምድር እንደ ወጣችበት ቀን እንደ ሕጻንነትዋ ወራት ትዘምራለች። በዚያ ቀን ባሌ ብለሽ ትጠሪኛለሽ እንጂ ዳግመኛ በኣሌ ብለሽ አትጠሪኝም ይላል እግዚአብሔር፤የበአሊምን ስም ከአፍሽ አስወግደዋለሁና በስማቸውም እንግዲህ አይታሰቡምና።"* (ሆሴ.2፥17-19)!

ከክፍሉ እንደምንረዳው፣ ያ ምድረ በዳ እና የመከራ ቦታ፣ ለእስራኤል ትልቅ መንፈሳዊ ለውጥንና በረከትን እንዳመጣ እንገነዘባለን። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት እንደ ተለወጠ፣ አምልኮአቸውና ከጌታ ጋር ያላቸው ግንኑነት እንደታደሰና እንደጠለቀ እናያለን። አስደናቂ ለውጥ!

ከድሎት ዘመን ይልቅ በዚህ ጊዜ፣ ብዙ ጸሎትና የጌታን ፊት መፈለግ ይስተዋላል። ና አይባልም እንጂ የመከራ ጊዜ የመማሪያና የመሞረጃ ጊዜ መሆኑን ብዙ ሰዎች ይስማማሉ። ጊዜው መርዘሙ ቢያታክተንና ጉስቁልናው ተጭኖ ቢያስጨንቀንም፣ ደግሞም ብዙ ጊዜ የምንሸሸው ጉዳይ ቢሆንም፣ ለመንፈሳዊ ዕድገት ትልቅ አጋጣሚ መሆኑ የሚያስማማን ይመስለኛል፤ ለዚህ ነው ሐዋርያው ያዕቆብ *"ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግስትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት። ትዕግሥትም ምንም የሚጎደላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።"* (ያዕ.1፥1-4) ብሎ የመከረው።

ይህ የፈተናና ጊዜ የምንሠራበት፣ ጌታን በሚገባ የምናውቅበት፣ ግንኙነታችን የሚጠልቅበትና ዕውቀታችንን ወደ ጥበብ ለመለወጥ ጊዜ የምናገኝበት መልካም አጋጣሚ ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከጌታው ጋር ተስማምቶ፣ በጌታ መንፈስ እና ምሪት፣ ይህንን የፈተና ጊዜ ዘልቆ

የወጣ ሰው፣ ሕይወቱ፣ ምልልሱና ምስክርነቱ ለሚያዩት ሁሉ ጠንከር ያለ መልእክት ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

ከላይም እንደጠቀስሁት፣ በተፈጥሮአችን ድሎተ-አፍቃሪ ስለሆንን፣ በፍጹም እንዲህ ዓይነቱን ነገር ስንሸሽ ነው የምንኖረው። እጅግ ፈሪዎች ነንና። ምክንያቱም አንድ ነገር ይመስለኛል፤ ስለሚያመን! እኛ ብንሸሽም ጌታ በማይደረስበት ጥበቡ፣ ወዳልጠበቅነው የሕይወት ሁኔታ ውስጥ እያባበለና እየከተተ ይለውጠናል። ከድሎት ሰፈር ወደ ተግዳሮት ሰፈር እየወሰደ ይቀርጸናል።

ደስ የሚለው ነገር በመከራና በተግዳሮት ውስጥ ሳለን የአጽናኙ የመንፈስ ቅዱስ ድጋፍ አብሮን መሆኑ ነው። በፍጹም ለደቂቃም ቢሆን አይለየንም። በተለይ በጸሎት በሚገባ ለምንተጋ ሰዎች ተግዳሮቱን የምንጋፈጠው፣ የጌታ ሕልውና እየታወቀን ስለሆነና ልባችን በእግዚአብሔር ሰላም እየተጠበቀ ስለሆነ፣ በተገላቢጦሽ በሕይወታችን የማይረሳ የበረከት ጊዜ ሁሉ ሊሆልንን ይችላል የሚል ምልከታ አለኝ። እንዲህም ዓይነት ምስክርነት ያላቸው ብዙ ሰዎችንም አውቃለሁ።

በእንደዚህ ዓይነት የፈተና ሰዓት ሰዋዊ፣ ሥጋዊ፣ እና ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስልቶችንና አካሄዶችን በመጠቀም፣ ከእግዚአብሔር መለኮታዊ አጀንዳ እንዳናፈነግጥና የበረከታችን ዘመን እንዳይረዝም፣ ከጌታ ጥበብና ጸጋ እንዲበዛልን ብዙ መቃተትና መጮኽ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። ወደ ድሮው የምቾት ቀጠናችን (our comfort zone) የሚመልሱ አቋራጮችን ተጠቅመን፣ ከመለኮታዊ አሠራሩና ሐሳቡ ሾልከን እንዳንወጣም ልንጠነቀቅ ይገባል የሚል ሐሳብ አለኝ።

ለማጠቃለል በመከራና በፈተና ጊዜ፣ በተግባር ደረጃ የሚከተሉትን እናድርግ፡-

- በእርሱ ፊት ያለማቅማማት ጨክነን እንውደቅ፤
- *ያ*ምን እንለማመድ፤
- በተመሳሳይ የሕይወት ሁኔታ ካሉና ካለፉ ሰዎች ጋር አብረን በመሆን የጌታን ፊት እንፈልግ፤
- ከቃሉ ጋር ያላሰለሰ ቁርኝት እናድርግ፤
- ያለንበትን የሕይወት ሁኔታ በድል እስክንወጣው ድረስ ከእርሱ ጋር እንጣበቅ!!

**መዝጊያ ምንባብ፡-** *"ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፤ ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።"* (ያዕ.1፥2-4)

# የምሥጋና መጎናጸፊያ

**(ሶሻል ሚዲያ ላይ የተነበበ)**

> *"ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር አገናኝ መሰላል ነው።/ Prayer is the link that connects us with God."* ኤ.ቢ.ሲምሰን

እለቱ ሰኞ ነበር፣ በ2016 ዓ.ም ነው (እ.ኤ.አ)። ከሥራ አድሬ ቤት

የደረስሁት እጅግ ማለዳ ጧት ነበርና፣ ለአምስት ሰዓታት ገደማ ተኝቼ ከአልጋዬ ተነሣሁ። እንደተነሣሁም ቤት ያፈራውን ቀማምሼ ኮምፒዩተሬ ፊት ካለው ወንበር ላይ ተቀመጥሁ። በቀደሙት ሰሞናት ያለምኳቸውና ያሰብኳቸው ነገሮች ነበሩ። ተከናውነው አላለቁምና ድንገት ትዝ ብለውኝ በኃይል አስተከዙኝ። ምኑም አልጥመኝ ብሎኝ እጅግ ተጫጭኖኛል። መግለጽ የማልችለው ስሜት ከብቦኝና ማሰብ አቅቶኝ ደንዝዤ ነበር ማለት ይቻላል። ጨንቆኝም ነበር። ዳዊት ያንን ዓይነት ስሜቱን *"አንተ አምላኬ ኃይሌም ለምን ትተወኛለህ? ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ?"* (መዝ.43፥2) በማለት ገልጾ አምላኩን ተማጽኗል። እኔ ግን ያንን የምልበት አቅም አልነበረኝም።

በእንደዚህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ስከበብ የሚታየኝ ነገር መጸለይ ነው። ነገር ግን መጸለይ አቅቶኛል፤ አስጠልቶኛልም። በቅጽበት አንድ የእግዚአብሔር ሰው *‹‹የመጸለይ ፍላጎት ስታጣና መጸለይ ሲያቅትህ ራስህን ካገኘኸው መጸለይ ያለብህ ያኔ ነው››* ያሉት ትዝ አለኝ። ከሰውየው ሐሳብ ጋር በመስማማት እንደ ምንም ሸርተት ብዬ ለጸሎት በጉልበቴ ተንበረከክሁ። የምተነፍሰው ነገር ግን አንደበቴ ላይ አልነበረም። ለረጅም ጊዜ ጸጥታ ሆነ። ከብዙ ጸጥታ በኋላ አንድ አምልኮ መዝሙር ከፍቼ መጸለይ ጀመርሁ፤ አልፎ አልፎም መዝሙሩን አብሬም መከተል ጀመርሁ።

ትንሽ ቆይቼም በመኻል በመኻል በልሳን ረዘም ላሉ ደቂቃዎች መጸለዬን ቀጠልሁ። እላዬ ላይ የነበረው የከበደኝ ጉም እስኪገፈፍ ላልነሣም ጨከንኩ። ታምኜ በእምነት እንጂ በማየት ላለመላላስ (2ቆሮ.5፥6)፣ በመንፈስ ዓይኖቼን ወደ ጌታዬ አነሣሁ። ለተወሰነ ጊዜ በመቃተት አሳልፌ

ለደቂቃ ከተንበረከኩበት ተነሥቼ መብራት ላበራ ስል፣ የሆነ ለየት ያለ ቀድሞ ያልነበረ ጉልበትና መታደስ ወደ ውስጤ እንደመጣ ታወቀኝና ደነቀኝ።

የከበበኝ ጉም ተበትኖ እና *“በኀዘን መንፈስ ፋንታ የምሥጋና መጎናጸፊያ”* (ኢሳ.61፥1-3 ያንብቡ) ተደርቦልኝ በሚያማምሩ ድንቅ ዝማሬዎች ታጅቤ፣ አመሻሹ ላይ ወደ ሥራዬ አመራሁ። ለመሆኑ ይህንን ሕክምና የት አገኘው ኖሯል? እርሱን የሚወዳደር ሐኪምስ የት ይገኛል?

ዋናው ላንባቢዎቼ ያለኝ መልእክት እንዲህ ነው። የእግዚአብሔር ቃል *“ውኃውንም ከመድኃኒት ምንጮች በደስታ ትቀዳላችሁ።”* (ኢሳ.12፥3) ይላልና፣ የመጀመሪያው ምክሬ በእንደዚህ ዓይነት ከባድ ሁኔታ ውስጥ ስትገቡ፣ በነፍሳችሁ መታገሉን አቁሙና የዓለሙን መድኃኒት አስቡ የሚል ነው። በሁለተኛ ደረጃ ወደ ጸጋው ዙፋኑን ኑና (ዕብ.4፥16) ይህንን ማለቂያ የሌለውን መድኃኒት ከማያልቀው ፋርማሲ ቅዱና ተጠቀሙ የሚል ነው። ቅዱስ ቃሉ፣ *“በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም”* (ዘካ.4፥6) ይላልና!

**መዝጊያ ምንባብ**፦“እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል። ወደ ዕረፍቱ የገባ፥ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና። እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።” (ዕብ.4፥9-11)

# እገሥግሣለሁ

*“ጸሎት ልመና ብቻ አይደለም። የነፍስ ራብና ናፍቆት ነው። የራስን ድካምም በየቀኑ መቀበል ነው።/ Prayer is not asking. It is a longing of the soul. It is daily admission of one's weakness.” — ማሃትማ ጋንዲ*

መዝሙር 63 ድንቅ የጸሎት መርሖዎች ያሉት ምዕራፍ ነው። በዚህ ምዕራፍ አንዴ ሳነብብ ሦስት ምንባባት በተለየ መልኩ አይቼ ነው ይህንን አጭር መልእክት ልጽፍ የቻልሁት። በምዕራፉ ውስጥ

1. *“ነፍሴ አንተን ተጠማች”* (ቁ.1)

2. *“ነፍሴ በኋላህ ተከታተለች”* (ቁ.8)

3. *“ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች።”* (ቁ.5) የሚሉ ክፍሎች ይገኛሉ።

እነዚህ ምንባባት በከፊልም ቢሆን የጸሎትን ደረጃ ያሳያሉ ብዬ አስባለሁ። ጸሎት ወደ ውስጠኛው የእግዚአብሔር ማደሪያ የሚደረግ ግሥገሣ እንደ ሆነ፣ *“አምላኬ አምላኬ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ”* (ቁ.1) የሚለው ቃል ያመለክተናል። ጉዞ መነሻ እንዳለው ሁሉ ጸሎታችንም ከላይ ላይ ዓይነቱ አደባባይ ወደ ጠሊቁ ያነጣጠረ ነው። ለዚህም ነው ዳዊት *“ኃይልህንና*

*ክብርህን ለማየት ዘንድ እንዲሁ በመቅደስህ ውስጥ ተመለከትሁ።" (መዝ.63፥2)* ብሎ የሚናገረው። ምንባቡ እንደሚጠቁመን፣ ጸሎታችን እየጠለቀ ሲሄድ፣ የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብሩን የማየት በረከታችን እየጨመረ እንደሚሄድ እናስተውላለን። ስለሆነም ነው በግልብ (superficial) ጸሎት *"ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች።"* (መዝ.63፥5) ማለት የማንችለው።

*«እገሥግሣለሁ»* (ቁ.1) ስንል የጸሎት እርምጃችን ጽናት፣ መሰጠት፣ ትግዕሥት፣ ንቁነት ወዘተ እንደ ግብዓት እንደሚያስፈልጉት መገንዘብ ይኖርብናል። ብዙ ጊዜ ለጸሎት ስንደረደርና ለመገሥገሥ ስናስብ፣ *"ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች።"* (መዝ.63፥1) የሚል መንፈስን ይዘን ነው የምንቀርበው፤ በተጓዳኝ ተግዳሮቶቻችን እያሰብን፤ ሕመማችን እያሰብን፤ ፈተናዎቻችን እያሰብን፣ መከራዎቻችን እያሰብን ወዘተ። ባለፉት የጸሎት ጊዜያት የነበሩንን ግሩም ልምምዶች እያሰብንም ነው አምላካችን አሁንም እንዲደግመው በመማጸን ነው በፊቱ የምንሆነው።

ጸሎትን ስንጀምር የመጸለይ ፍላጎታችን እጅግ ዝቅ ያለ ስለሚሆን፣ ቶሎ እንድናቋርጥ ፈተናዎች ይመጣሉ። ድካም ይጫጫነናል፤ አእምሮአችን ይበታተናል ሌላም ሌላም። ነገር ግን በጽናት ይህንን ተግዳሮት አሸንፈን ከዘለቅን፣ የእግዚአብሔር ሕልውና የሚታወቀን ደረጃ ውስጥ እንገባለን። በዚህ ደረጃ ላይ ሆነን ነው፣ *"ነፍሴ በኋላህ ተከታተለች"* (መዝ.63፥8) የምንለው። በዚህ ደረጃ ላይ ሆነን ነው *"ሳበን ካንተም በኋላ እንሮጣለን.....ከወይን ጠጅ ይልቅ ፍቅርህን እናስባለን።"* (መኃ.1፥4) የምንለው። በዚህ ጊዜ ትንሽ ትንሽ ዝማሬና ምሥጋናም ያምረናል፤

ጸሎታችንንም ሳናቋርጥ መቀጠል ያምረናል። ቢሆንም ብዙ ሰዎች በሚገባ የጸለዩ ስለሚመስላቸው እዚህ ደረጃ ላይ ያቋርጣሉ። እንዳውም ስለነበራቸው ድንቅ የጸሎት ጊዜም ለሰዎች ሊመሰክሩ ይችላሉ ብዬም አስባለሁ። ይህንን ደረጃ ስናልፍ ሦስተኛው ደረጃ ውስጥ እንገባለን።

ሦስተኛው የጸሎት ደረጃ፣ ከጌታ ጋር እጅግ አስደናቂ ኅብረት የምናደርግበት የጸሎት ደረጃ ሲሆን፣ እውነተኛ የሕይወት ለውጥ (transformation) ለማየት መልካም ዕድሎችን ይፈጥርልናል። በዚህ የጸሎት ደረጃ አዘውትረን ስናሳልፍ ነው *"ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች፤ ከንፈሮቼም ስምህን በደስታ ያመሰግናሉ"* (መዝ.63፥5) ብለን በእውነት እና በድፍረት መናገር የምንችለው።

ጌታ ሆይ እባክህ ወደ ጠለቀ ጸሎት ሳበን!

*መዝጊያ ምንባብ፡- "ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች፤ መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ? ዘወትር። አምላክህ ወዴት ነው? ሲሉኝ እንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ።"* (መዝ.42፥1-3)

# ጉልበቴን ይያዝ

*"ጸሎት የእግዚአብሔርን ዳተኝነት ማሸነፍ ሳይሆን፣ የእርሱን ፈቃድ ይዞ በፊቱ መሆን ነው።/ Prayer is not overcoming God's reluctance. It is laying hold of His willingness." — ማርቲን ሉተር*

ለጸሎት የሚያነሣሣኝና በልቤ ላይ በማይረሳ መልኩ ታትሞ የሚገኝ ቃል ኢሳይያስ 27፥5-6 ነው። ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ስላጠናሁት፣ ለነፍሴ መልሕቅ ሆኗል ማለት እችላለሁ። እጅግ በጣም ግሩም ቃል ነውና እርሱን ላስቀድም። *“ወይም ጒልበቴን ይያዝ፣ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ፤ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ። በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፣ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።”* (ኢሳ.27፥5-6)!

*“ጒልበቴን ይያዝ”* የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ላይ *“መሸሸጊያው ያድርገኝ”* የሚል ትርጉምን እንደ ያዘ አንብቤአለሁ። *“ጒልበቴን ይያዝ ከእኔም ጋር ሰላም ያድርግ”* የሚለው ሐሳብ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረትና ቁርኝት ከሰላማችን ጋር የተያያዘ መሆኑን በግልጽ ያሳየናል። አዎ፣ የጌታን ጉልበት በጸሎት በያዝን ቁጥር ሰላማችን እየበዛ፣ እየተረጋጋን እና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እየተለወጥን መምጣታችንን በተግባር በራሴ ሕይወት አይቼዋለሁ። ይህንን እውነት ለ22 ዓመት በተግባር ዳስሼ ቀምሼዋለሁ።

ከመቼውም ዘመን ይልቅ የእግዚአብሔር ጉልበት በጸሎት መያዝ ያለበት ዘመን ቢኖር የአሁኑ ዘመን ነው ብዬ አምናለሁ። ለምን ቢባል የክፋት መጠን በኃይል እየጨመረና እያየለ መጥቷልና ነው። ሰይጣን ከእያንዳንዱ ክፋት በስተጀርባ በታላቅ ቁጣ ምድሪቷን እያመሳት ስላለ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በውጭ ባሉት በማያምኑ ሰዎች ሕይወት ብቻ ሳይሆን፣ “ጌታን እናውቃለን” በሚሉት ላይም በገሃድና በብዛት ስለሚታይ፣ ያለውን የክፋት መጠን በኃይል ያጎላዋል። በአሁኑ ሰዓት በክርስቲያን ወገኖች መካከል፡-

- ፍቅርና መዋደድ እጅግ ቀዝቅዟል፤
- ውሸት ነግሗል፤
- ግብዝነት ሰፍኗል፤
- ራስ ወዳድነት አግጥጦ ወጥቷል፤
- አለመተማመንና ጥርጣሬ በዝቷል ....ሌላም ሌላም(ዝርዝሩ ረጅም ነው)።

ከዚህም የተነሣ የሰዎች የልብ ስብራት ከመጠን በላይ ሰፍቷል። እናም ያለንበትን ዘመን አስፈሪነት ቋንቋ የሚገልጸው አይመስለኝም። ለዚህ ነው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበሩትን የናሆም ዘመን ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ *"የሚቀጠቅጥ ባንተ ላይ ወጥቷል፥ ምሽግህን ጠብቅ፥መንገድህን ሰልል፥ ወገብህን አጽና፥ኃይልህን እጅግ አበርታ።"* (ናሆ.2፥1) ብሎ የመከራቸው። *"ኃይላችንን እጅግ ማበርታት"* የምንችልበት ዋነኛው መንገድ ደግሞ፣ የጌታን ጉልበት በጸሎት ስንይዝ ነው። ድምጹን ስንሰማ ነው። የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ሲታደስ (2ቆሮ.4፥16) ነው። ከቃሉ ጋር ስንጣበቅ ነው።

ከላይ እንደጠቀስሁት *"ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና"* (ኤፌ.5፥16) የጌታን ጉልበት በጸሎት መያዝን ግድ ይለናል። ታዲያ ጉልበቱን ይዘን ሙጭጭ ስንል፣ *"ካልባረክኸኝ አልለቅህም"* (ዘፍ.32፥26) ስንለውና ጠንከር ያሉ የጸሎት ጊዜዎች ሲኖሩንና በፊቱ ስናሳልፍ፡-

- መንፈሳችን ይጠነከራል፤
- አረማመዳችን ይጸናል፤

- እምነታችን ያድጋል፤
- በምናየው ነገር መሸበራችን ይወገዳል፤
- 
- መረጋጋት የሕይወታችን መገለጫ ይሆናል፤
- የራእይ ሰዎች እንሆናለን፤
- ለሌሎች የምንተርፍ የበረከት ሰዎች እንሆናለን።

በዚሁ ምንባብ መጨረሻ ላይ ያለው የጌታን ጉልበት የመያዝ አስደናቂ ውጤት *"በፍሬአቸውም የምድርን ፊት ይሞላሉ"* የሚል ነው። ይህን ሰፊ በረከት ሳጤነውና ሳስበው እጅግ በጣም ያስደንቀኛል። እጅግ የሚገርም ተፅዕኖ ነው እኮ! እስቲ እናንተ ይህ በተግባር ሆኖ ለሰከንድ በዓይነ ሕሊናችሁ ዕዩት። ይህ ሲሆን የማይነካ የማኅበረ ሰብ መዋቅር የለም።ይህ ሲሆን ብዙ ሰዎች ጉልበታቸውን ለጌታ ያንበረክካሉ። ይህ ሲሆን ብዙ መንፈሳዊና ማሕበራዊ ችግሮች ይወገዳሉ። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር በመካከላችንም ሆነ በውጭ ባሉት ዘንድ በሚገባ ይከበራል።

ባጭሩ ቃሉ አራት መንፈሳዊ እመርታዎችን በግልጽ ያሳየናል (ማሳሰቢያ፡- ጉበዝ አራቱም እመርታዎች የተያያዙ ናቸውና መዝለል አይቻልም)፡-

- የእግዚአብሔርን ጉልበት በጸሎት መያዝ፤
- ከእርሱ ጋር ለመሄድ መስማማት፤
- ጤናማ መንፈሳዊ ዕድገት፤
- መንፈሳዊ ፍሬዎች።

በዚህ ምንባብ ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ሂደት እጅግ ድንቅ ነው። ከላይ እንደጠቀስኩት እመርታዎቹ ተያያዥነት ያላቸው ስለሆኑ፣ የእርሱን

ጉልበት በመያዝ ጀምረን ወደ ፍሬ እንደምንመጣ ሊስተዋል ይገባል። በፍጹም ሌላ አቋራጭና አማራጭ መንገድ እንደሌለም ማወቁ ማስተዋል ነው እላለሁ። እዚህ ጋ ነው ዋጋ የምንከፍለው። እዚህ ጋ ነው ዲሲፕሊን የምንጠየቀው። እዚህ ጋ ነው ትልቁ ትግል፤ ተስማምቶ ለመሄድ መወሰኛው፤ ብዙ ረብ የሌላቸውን ነገሮች ለመጣል የምንገደደው፤ እንደ ሐና በመንፈስ የምንቃትተው። እዚህ ጋ ነው እንደ ያዕቆብ እስኪነጋ ነ የምንፋለመው። ስለሆነም የሚከፈለውን ዋጋ ሳናቅማማ እንክፈል። ያንን በቁርጠኝነት ካደረግን፣ ጌታ ኢየሱስ በፍሬና በበረከት ተገልጦ ያስደንቀናል። ስለሆነም፣ ወገኖቼ የጌታን ጉልበት በጸሎት እንያዝ!!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*"እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ።"* (ዕብ.5፥7-10)

# "አቅቶኛል" በለው

ሁለትነት ተጠናውቶህ፣ ሲጠፋህ ውሉ የምትረግጠው

መዋለል አስቸግሮህ፣ የምትመርጠውን ስታጣው

አሥሩን በልብህ አማትረህ፣ አሥሩን ስታነሣ

ግራ ሲገባህ ሕይወት፣ ስትባክን በኀሣሣ

ፍልስፍናህን ጣልና.....

*“አቅቶኛል”* ብለህ ጨኽ፣ አልቻልኩም ብለህ ተጣራ

ድካምህን አስተውለህ፣ እየፈቀድህ እንዲሠራ

ትሑት ሆነህ ለቅቀህ ቦታ፣ እንዲረዳህ ብትጋብዘው

ዝቅ ብትል፣ ብትዋረድ፣ “ናልኝ” ብለህ ብትጠራው

ያሳይሃል ጥበቡን፣

ብርታት ክንዱን ቻይነቱን!

# ለጌታ የመገኘት በረከት

*"እውነተኛ ጸሎት የአእምሮ ልምምድ ወይም ድምፅን የማውጣት ክንውን አይደለም። ከዚያ የሚጠልቅ ተግባር ሲሆን፣ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረው ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር የሚደረግ መንፈሳዊ ግንኙነት ነው።/ True prayer is neither a mere mental exercise nor a vocal performance. It is far deeper than that - it is spiritual transaction with the Creator of Heaven and Earth."* ቻርለስ ስፐርጀን

ለጌታ መገኘት ልዩ በረከት አለው። የመጀመሪያው በረከት ጌታን በሚገባ ማወቃችን ሲሆን፣ ሌሎች ፍሬዎች ግን እርሱን ከማወቅ የሚመነጩ ናቸው። ለእግዚአብሔር የተገኘ ሰው ደግሞ ጌታን በሁሉ ነገር የበላይ

ያደርጋል፤ በነገሩ ሁሉ የአምላኩን ፈቃድ ያስቀድማል፤ የጌታን ድምፅ ሰምቶ ይታዘዛል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ሐሳብ ይወርሰዋል። እናም ሙሉ በሙሉ ትኩረቱ አምላኩ ላይ ይሆናል። ለጌታ የተገኘ ሰው የራሱን አጀንዳ ይተዋልም።

ለጌታ ለመገኘት ባጭሩ የሚከተሉትን ነው ማድረግ ያለብን ይመስለኛል። የመጀመሪያው እንዲህ ዓይነት ሰው ለመሆን ጥሩ ውሳኔና መሰጠት ይፈልጋል። ሁለተኛው ለእርሱ ልንገኝባቸው የምንችላቸውን መንገዶች ሁሉ መጠቀምን ይጨምራል። ዋናዎቹም ለብቻ የምንሆንበት ጊዜ ወስኖ፣ ቃሉን ባልተከፋፈለ ልብ ማንበብ፣ ማጥናት፣ ማሰላሰልና የጌታ መንፈስ ከውስጥ ወደ ውጭ እንዲለውጠን ራሳችንን በፊቱ በመጣልና *"እነሆኝ"* ማለት ሲሆን፣ ድምፁን ስንሰማ ደግሞ ወዲያው መታዘዝን ያካትታል።

ታዲያ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ቁልፍ ተግባራዊ ነገሮች በዋናነት ጊዜን እንድንሠዋ ግድ ይሉናል። ቢሆንም በዚህ ግርግርና ወከባ በበዛበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ውስጣችንን እንደ ሐሳቡ በመለወጥ የፍሬ ሰዎች እንዳያደርገን ትልቁ ተግዳሮታችን ጊዜ ማጣታችን ነው። ሞባይሉ፣ ኮምፒዩተሩ፣ ሶሻል ሚድያው ወዘተ ለብቻ የሚወስዱ ጊዜያትን በከባድ ተፎካካሪነት እየነጠቁን ስለሆነ፣ ለውጥ አልባ፣ የላይ ላይ ሰዎች እያደረገን ይገኛል። እኔም የዚህ ሰለባ ስለ ሆንሁ አንዱ ዘወትር የምወቀስበትና የማዝንበት ጉዳይ ነው።

የጽሑፍ አርዕስቴ የተወሰደበት፣ ሳነበው ጉጉትን የሚያሳድርብኝና፣ የሚያስደንቀኝ ቃል መዝሙረ ዳዊት 89 ላይ ይገኛል። *"ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት፤ ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት። እጄም ትረዳዋለች፤ ክንዴም ታጸናዋለች። ጠላት በእርሱ ላይ አይጠቀምም፤ የዓመፃ ልጅም*

*መከራ አይጨምርበትም። ጠላቶቹን ከፊቱ አጠፋለሁ፥ የሚጠሉትንም አዋርዳቸዋለሁ።"* (መዝ.89፥20-23) ነው የሚለው።

ይህ የተጠቀሰው ቃል ለእግዚአብሔር የመገኘትን በረከት በግልጽ ያሳየናል። ንጉሥ ዳዊት ለእግዚአብሔር ሊገኝ የቻለበት ምክንያቶች በርከት ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ እንደ ልቤ የተባለ ሰውም ነበር። እኔ በበኩሌ በመዝሙራቱ ውስጥ ደጋግሜ የተገነዘብሁት ነገር ንጉሥ ዳዊት በጸሎት በጌታው ፊት ወድቆ ሌት ተቀን የሚያነባ፣ በጌታው ፊት የሚጮኽ፣ ለረጅም ሰዓታት የሚቃትትና ጌታውን የሚጠብቅ ሰው እንደ ነበረ አስተውያለሁ። ለአብነት ያህል የተወሰኑትን እነሆ፡-

*"ሁልጊዜ ከመጮኼ የተነሣ ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ።"* (መዝ.32፥3)

*"አቤቱ ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና ማረኝ።"* (መዝ.86፥3)

*"ይህ ችግረኛ ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው፣ ከመከራውም ሁሉ አዳነው።"* (መዝ.34፥6)

*"አቤቱ የመድኃኒቴ አምላክ፣ በቀንና በሌሊት በፊትህ ጮኽሁ።"* (መዝ.88፥1)

ከልምድ እንዳየሁት እውነተኛ በሆነ መገኘት የሚመጣ መንፈሳዊ ለውጥ ቆራጥነትን፣ መጨከንን፣ ትኩረትን፣ መወሰንንና ያለንበትን መንፈሳዊ ይዘት በመንፈስ ዐይቶ መጥላትን ይፈልጋል። ለነገሩ ያለንበትን መንፈሳዊ ሕይወት ጌታ ዓይኖቻችንን ከፍቶ ሲያሳየን ነው ካለንበት የሚሻል ሕይወትን የምንመኘው። አለበለዚያ ከሌሎች ጋር እያስተያየን የተሻልን

መስሎንም ልንኮፈስና ልንገበዝ እንችልም ይሆናል።

በኢሳይያስ ሕይወት እንዳየነው ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ እስከ አምስተኛው ምዕራፍ ድረስ፣ የነበረው ትንቢት ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ነበር። ስድስተኛው ምዕራፍ ላይ ግን ጌታ በክብሩ ተገልጦ፣ የቅድስናውን ከፍታ ሲያሳየውና፣ እርሱ ደግሞ ያለበትን መንፈሳዊ ሁኔታ ሲገልጽለት ደንግጦ የሚገባበት የጠፋው። ከዚያማ በጌታ የተገኘ ሰው ቋንቋ ከልቡ ፈለቀ። *"ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፣ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ። (Woe* is *me! For I am undone!)!"* (ኢሳ.6፥5) ብሎ ተናገረ።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው *"ዋና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች (በተለይ መድረክ ላይ የሚወጡ አገልጋዮች) ኢሳይያስ በምዕራፍ ስድስት የነበረውን ዓይነት ተመሳሳይ ልምምድ ሳይኖራቸው መድረክ ላይ መውጣት የለባቸውም"* የሚል አቋም እንዳላቸው ተናግረዋል። እኔም ይህንን ሐሳባቸውን እጋራለሁ። ልክ ናቸው፣ አገልግሎት የእሳቱ ጉጠት ከንፈሮቻችንን ካገኘው በኋላ ነው እንጂ!

ለጌታ የተገኘ ሰው በነገር ሁሉ ራሱን በቅድሚያ ይመለከታል። ጥሩ የንስሐ ሕይወት ይኖረዋል። አምላኩን በመማጸንም ከዚያ ካለበት መንፈሳዊ ሁኔታ ለመውጣትና የተሻለ ሰው ለመሆን ይቃትታል። ይጮኻልም። የአምላኩን ጉልበት በጸሎት ይይዛል።

ውስጣዊ ለውጣችን ቀዳሚ ቢሆንም፣ ለጌታ በመገኘት የሚመጣው በረከት ብዙ ነው። ከበረከቶቹ ሁሉ ዋነኛው ጨክነን እንደ እርሱ ሐሳብ

ስንገኝለት፣ የክብር ዕቃዎቹ መሆናችን ነው። እናም ምልልሳችንና አገልግሎታችን ውበትን ያገኛል። ለሰዎች ጥሩ የሚታይና የሚነበብ መልእክትም እንሆናለን።

ከብዙ ትግል በኋላ ለጌታው ስለ ተገኘ ሰው ትንሽ ልበል። ያም ሰው ያዕቆብ ነው። ዋናው ሐሳቤም ያዕቆብ ከብዙ የራስ ወዳድነት እርምጃዎችና ማታለሎች በኋላ፣ እጅ ወደ ላይ ያለበትን የመጨረሻ ትግል ላነሣ ፈልጌ ነው። ባለፉት ርዕሶችም ላይ አንስቼዋለሁ። ዘፍጥረት ምዕራፍ 32፥22-30 እንደሚተርከው፣ ያዕቆብ ከብዙ ያለመገኘት ጊዜያት በኋላ፣ በቃኝ ያለበትና ለመገኘት የቆረጠበትን እርምጃ የሚያሳይ ክፍል ነው። *"ያዕቆብም ለብቻው ቀረ"* (ቁ.22) የሚለው ሐሳብ፣ የያዕቆብን ቆራጥ ውሳኔ በግልጽ ያሳየናል።

ያዕቆብ ከአጠገቡ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ለጊዜውም ቢሆን አርቆ ለብቻው ለእግዚአብሔር ተገኘ። ወስኗልና፣ ጨክኗልና፣ ለውጥ ፈልጓልና *"ካልባረክኸኝ አልለቅህም"* (ዘፍ.32፥26) አለ። እናም ውጤቱ አስደናቂና ከአእምሮ በላይ ነው። ለእግዚአብሔር በመገኘት ያገኘውን መንፈሳዊ ለውጥ ሲናገር እንዲህ ነበር ያለው፦*"እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት፣ ሰውነቴም ድና ቀረች።"* (ዘፍ.32፥30)!

ስለዚህ ወገኖቼ በተግባር ደረጃ ጌታ ጥሩ ጊዜያትን ለብቻችን ሲሰጠን ወይም እኛም ብንሆን ካለን ጊዜ ላይ ጨክነን ቀንሰንም ቢሆን፣ ከእግሩ ሥር በርከት ላሉ ሰዓታት መውደቅ ማስተዋል ነው እላለሁ። በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራን ሆነንና የአእምሮአችንን በር ለውጫዊ ድምፆች ጠርቅመን፣ እንደ ያዕቆብ ጌታን ፊት ለፊት እስክናየው በፊቱ እንሁን። እውነተኛ መነካት በውስጡ ሰውነታችን ሳይታወቀን

ከወደቅንበት አንነሣ። ለምን ብትሉ እንዲህ ዓይነት ጊዜዎች ተደጋግመው ሲበዙልን ነው፣ መንፈሳዊ ለውጣችንና ዕድገታችን እውነተኛና ዘላቂ የሚሆነው።

በመጨረሻም ከላይ እንደጠቀስሁት እግዚአብሔር ፈቅዶና ሁኔታዎች ተመቻችተውልን፣ በጸጋ ዙፋኑ ፊት ከተገኘን፣ በተግባር ደረጃ እንዲህ እናድርግ፡-

- እግዚአብሔር እንዲነካን፣ እንዲመራንና እንዲለውጠን በፍቃደኝነት ልባችንን እንክፈት፤
- እንደ መንፈስ ቅዱስ ምሪት ጥልቅ ንስሐዎችን በፊቱ እንግባ፤
- ቢያስፈልግ የምር የሆኑ እንባዎችን በፊቱ እናፍስ፤
- እውነተኛ ማንነታችንን ገልጠን እናሳየው፤
- ድምፁን ለመስማት ሁለንተናችን እናረጋጋ፤
- ከጌታ እንደሚቀበል ሰው ሆነን እንጠባበቅ፤
- ጽኑ በሆነ ጸሎት ወደ ማደሪያው እንገሥግሥ፤
- እናም በቂና ጥራት ያለው ጊዜን በርሱ ፊት እናሳልፍ።

ወገኖቼ የውሳኔ ሰዎች ሆነንና፣ ለውጥን ፈልገን በጸጋው ዙፋን ፊት ያለ ምንም ስስት ራሳችን ብንጥል ያስደንቀናል!!

**መዝጊያ ምንባብ**፡-*"እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።"* (ሮሜ.12፥1)

# መሪውን እንስጠው

*“መጸለያችንን መቼም ቢሆን አንርሳ፤ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ አለና። እርሱ ከእንስትፋሳችን ይልቅ ቅርብ ነውና። ሕያው ነውና። ተግተው ለፈለጉት ሁሉ ይገኛልና።/ Let us never forget to pray. God lives. He is near. He is real. He is accessible to all who will seek Him.” —ጎርዶን ቢ.ሂንክሌይ*

በመካከላችን ብዙ የነፍስ ክሳት መኖሩ፣ ጸሐይ የሞቀው ሃቅ ነው። ይህ ያላሳዘነን ምን እንደሚያሳዝነን አይገባኝም። ይህ ያላስጮኸን፣ ሌላ ምን አንገብጋቢ ጉዳይ እንዳለም በፍጹም አይገባኝም። አሳዛኙ ነገር ደግሞ ይህ የነፍስ ክሳት የተጠናወተን፣ ከጌታ ዘንድ ድንቅ የሆኑ የግብዣ ጥሪዎች ሞልተውልን ሳለ በመሆኑ ነው። የሚያረካ፣ ነፍስን የሚያሳርፍ፣ ልባችንን አእምሮን በሚያልፍ ሰላምና ደስታ የሚባርክ ጌታ እጁን ዘርግቶ ሳለ በመሆኑ ነው። እንቆቅልሾቻችን የሚፈታ፣ በከፍታዎች የሚያስሄደን ክንደ ብርቱ አምላክ ሳለ በመሆኑ ነው። ለናሙና የሚከተሉት ድንቅ ግብዣዎቹን እነሆ፡-

*“ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፣ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? አድምጡኝ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁ በጮማ ደስ ይበለው።” (ኢሳ.55፥2)*

*“ወደ ዘለፋዬ ብትመለሱ መንፈሴን አፈስስላችኋለሁ።” (ምሳ.1፥23)*

*“ልጄ ሆይ መልካም ነውና ማር ብላ፣ ወለላም ለጣዕምህ ጣፋጭ ነው።*

*ጥበብም ለነፍስህ እንዲሁ እንደሚሆን እወቅ፤ብታገኘውም ፍጻሜህ መልካም ይሆናል፣ ተስፋህም አይጠፋም።" (ምሳ.24፥13-14)*

*"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ፣እኔም አሳርፋችኋለሁ.......ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ።" (ማቴ.11፥28-30)*

የጌታ መንፈስ ደግሞ ደጋግሞ *"ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም"* (ዮሐ.15፥5) ነው የሚለን። ሆኖም ግን አሳዛኙ ነገር አለመስማታችን ነው፡፤ እርሱ "ከእኔ ጋር ተጣበቁ" ብሎ ቢመክረንም፣ እኛ ግን ሰዋዊ ነገሮችንና ዓለማዊ ዘዴዎችን አስቀደመን ከመካከላችን አስወጣነው። ነገር ግን ያለ እርሱ ሕልውና ሕይወት ጣዕም-አልባ መሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል። እንደ ፈለገ ምድራዊ ነገሮች ቢኖሩን፣ እንደ ፈለግን በዙሪያችን ደጋፊዎች ቢከብቡን፣ እንደፈለግን ቁሳዊ ነገሮችን ቢተርፉን፣ ያለ አብሮነቱ ኑሮ ባዶ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል።

እስቲ ጎበዝ ቆም ብለን እናስብ። ግሩም ሆኖ የተዘረጋ እጅ እያለ ምነው በራብ ማለቃችን? ምነውስ መንፈሳዊ ችግሮቻችን መብዛታቸው? በብዙ አሳዛኝ ሁኔታዎች ተከብበን፣ ምንም ነገር እንዳልሆነ እየቆጠርንና ሁኔታዎችን እየካድን ዝም ብለን ለምን ነፋስን እንጎስማለን? ጌታ በልባችን ደጅ ቆሞ ከፈቱልኝ ልግባና ልሥራ (ራእ.3፥20) እያለ ያለበት ጊዜ ነው፤ እኛ ግን በእምቢተኝነት አለን። ወገኖቼ ይህ በየቦታው የሚታይ እምቢታና እልኸኝነት ካላስለቀሰን ሌላ ምን ሊያስለቅሰን እንደሚችል እኔ አይገባኝም።

እስቲ አስቡት ያለ እርሱ የትኛው ሰልፍ ይከናወናል? ያለሱስ ዘዴዎቻችንና ብልሃቶቻችን የት ያደርሱናል? የትኛው የአምልኮ ጉባዔስ ያለ እርሱ ይደምቃል? ያለ እርሱ መገኘትስ የትኛው እንቆቅልሽ ይፈታል? ኧረ እባካችሁ ወደ ልባችን እንመለስ! ደግሜ ላስታውሳችሁና እየሆነ ያለው እንዲህ ነው፡-

- ልፈውሳችሁ በጸጋው ዙፋኔ ፊት ኑና ውደቁ ሲል፣ ለደቂቃዎች እንኳ መገኘት አቃተን፤
- ልምራችሁ ሲለን እምቢ አልን፤
- ልቅደምና ልሥራ ተከተሉኝ ሲለን እኛ ቀደምነው፤
- ታዘዙኝ ሲለን በልባችን እምቢተኝነት ሸምጥ ጋለብን።

እርሱ ግን እጅግ ትሑት ነውና አሁንም እጁን ዘርግቶ ይጠብቀናል (ኢሳ.9፥12፣17)። "አስቀድሙኝ" እያለ እየለመን አጠገባችን አለ፤ አልተለየንም። "እሺ በሉኝና ልሥራ" እያለን ነው። "መሪውን ስጡኝና እኔ ልምራችሁ" እያለ በብዙ እየተናገረን ይገኛል። ነገር ግን ባዶ ዕውቀትና ፍልስፍና ይዞን አለቅን፤ ማስተዋል እርቆን ሳትን። ሁለት ትልልቅ ክፉ ነገሮችን አደረግን። *"የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተናል፤ ውኃውን ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን ጉድጓዶች ለራሳችን ቆፍረናል።"* (ኤር.2፥13)። የራሳችንን እሳት አንድደን ባነደድነው ወላፈን እየሄድን ነው (ኢሳ.50፥11)። ስለዚህም ኀዘናችን፣ እንቆቅልሾቻችንና ስብራቶቻችን በዝተዋል።

ታዲያ አሁን መፍትሔው ምንድነው? መፍትሔውማ በብዙ ጥልቅ ንስሐና ልቅሶ አምርረን ፊቱን መፈለግ ነው። በድለንሃል ብሎ ምሕረቱን

እንዲያበዛልን መለመን ነው። *"ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደምትናፍቅ ነፍሴ አንተን ትናፍሃለች።"* (መዝ.42፥1) ብሎ መጮኹ ነው። በትሕትና ከፈለግነው፣ በጥልቅ ንስሐ ከተመለስን፣ በብዙ ዕንባ በፊቱ ከቀረብን፣ ከምር በረከቱን እንደ ያዕቆብ ከፈለግን ወገኖቼ ምንም ጥርጥር የለውም፤ ተገኝቶ ያስደንቀናል። እውነተኞች ከሆንንና አሁን ያለንበትን መንፈሳዊ ሕይወት ከጠላነውና፣ ወደ ፊት እንዲስበን እጃችን ከሰጠነው፣ ለእርሱ መሸነፋችንን በግልጽነትና በቅንነት ካሳየነው፣ እንዲሁም ከመሪው ላይ እጆቻችን ካነሣን፣ በአስደናቂ መገኘቱ ይባርከናልና እጅ ወደ ላይ እንበል!!

**መዝጊያ ምንባብ፡-** *"ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።"* (ምሳ.28፥13)

# የመንፈሳዊ ራብ በረከት

*"ጸሎት ለነፍሳችን እውነተኛው መሻቷ ነው። መሻታችን ጸሎታችን ነው። እሱ ደግሞ ከጥልቁ ማንነታችን የሚወጣ ጉጉት ሲሆን፣ በሕይወታችን እውን እንዲሆንልን የምንናፍቀውን ይገልጻል።/ Prayer is the soul's sincere desire. Your desire is your prayer. It comes out of your deepest needs and it reveals the things you want in life."*
*— ጆሴፍ መርፊ*

መንፈሳዊ ራብ ጌታን መናፈቅን፣ እርሱን ለማግኘት መጓጓትን፣ ወደ እርሱ ለመጠጋት ማሰብን ወዘተ ያመለክታል። በግለሰብ ይሁን በወል ደረጃ መንፈሳዊ ራብና ጥማት ለእግዚአብሔር መለኮታዊ ጉብኝት እጅግ ወሳኝ

ናቸው። አውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ ራብና ጥማት እግዚአብሔርን እንድንሻው፣ እንድንፈልገውና እንድንጠጋው ኃይል ይሆኑናል። ቃሉ *"ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው።"* (ማቴ.5፥6) የሚለንም ለዚህ ነው። *"ብፁዓን"* የሚለውን ቃል ድረ-ገጽ ላይ ያገኘሁት አምሊፋይድ መጽሐፍ ቅዱስ "ደስተኞች፣ በመንፈስ ባለጸጋ የሆኑ፣ የረኩ፣ የተባረኩ" ብሎ ነው የሚገልጸው።

ሐና መንፈሳዊ ራብ ያላቸው ሰዎች በጌታ ፊት ዋጋ ያላቸውና በፍጹም የማይረሱ እንደ ሆነ ስትናገር፣ *"ተርበው የነበሩ ከራብ አርፈዋል።"* (1ሳሙ.2፥5) ብላለች፤ አምላኳ የሚያረካ፣ የሚያጠግብና የሚያሳርፍ መሆኑን በማወደስ። መንፈሳዊ ራብ በራሱ ትልቅ በረከት ነው፤ ወደ ፊት እንድንዘረጋ፣ እንድንቃትት፣ እንድንጮኽና ፊቱን አንድንፈልግ ያደርገናል። የምር የሆነ መንፈሳዊ ራብ የሚመነጨው ደግሞ ያለንበትን መንፈሳዊ ሁኔታ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲያሳየንና ያለንበትን አዘቅት ስንጠላው ነው።

መንፈሳዊ ራብ በተፈጥሮው ይጐተጉተናል፣ አያስተኛንም፤ ቅዱስ ቃሉ *"የሠራተኛ ራብ ለርሱ ይሠራል አፉ ይጐተጉተዋል።"* (ምሳ.16፥26) ይላልና። *"ለርሱ ይሠራል"* የሚለውን አስምሩልኝ። ለማን? ለራብተኛው! ምን ያደርገዋል? አያስተኛውማ! ሳያገኝ አያሳርፈውማ! ለዚህ ነው መንፈሳዊ ራብ በራሱ የሚጓጓለት በረከት የሆነው። በውስጣችን ያለው ራብ ልክ እንደ ኤርምያስ ጌታን በትጋት እንድንፈልገው ያደርገናል። እርሱ ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሕይወት የሚሰጠውን፣ መንፈስ የሆነውን፣ የጊዜውን ቃል ሲያገኝ እንዲህ *"ቃልህ ተገኘቷል እኔም በልቼዋለሁ፤ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃል ሐሤትና የልብ ደስታ ሆነኝ።"*

(ኤር.15፥16) ብሏል! ከዚህ ምንባብ በጥቂቱ እንደምንረዳው፣ ኤርምያስ ቃሉን በትጋትና በተራበ መንፈስ ሲፈልግ የቆየ ይመስላል። ባገኘውም ጊዜ ከነበረው ናፍቆት የተነሣ ለመብላት ፋታ ያገኘ አይመስልም። እናም እስከሚረካና በሐሤት እስኪጥለቀለቅ ድረስ በላው።

መዝሙረኛ መንፈሳዊ ራብ ያላቸውን ሰዎች እግዚአብሔር እንዴት እንደሚባርክ ሲመሰክር፣ *"የተራበችን ነፍስ አጥግቦአልና፤ የተራቈተችንም ነፍስ በበረከት ሞልቶአልና።"* (መዝ.107፥9) ብሎ ተናግሯል። አዎ፣ መንፈሳዊ ራብ በውስጡ የገባበት ሰው ሲቆፍር፣ ሲፈልግ፣ ሲቃትት ወዘተ ያድራል፤ ምንም ዕረፍት አይኖረውም ያንን ራብ ሳያስታግሥ። ራቡ ጒትጓች ነውና፣ አያስተኛውምና።

ታዲያ ይህንን መንፈሳዊ ራብ በማቀጣጠል የሚታወቁ ሦስት ነገሮች አሉ። እነርሱም፡-

- የእግዚአብሔር ቃል አብዝቶ ማጥናትና ማሰላሰል፤
- ደጋግሞ ለረጅም ጊዜ መጾም፤
- ቢሰማንም ባይሰማንም በጌታ ፊት በውሳኔ መውደቅ።

ጌታ እንደ ተስፋ ቃሉ መንፈሳዊን ነገር በሚራቡና በሚጠሙ ሰዎች ሕይወት፣ ከብዙ መሻት በኋላ ሲገለጥ አስደናቂ ነገር የሚሆነው። ለዚህ ነው ሰፋ ካለ መንፈሳዊ መነቃቃት በፊት፣ ጌታ በቤተ ክርስቲያን እርሱን የሚራቡና የሚጠሙ፣ እናም በጓዳ እርሱን የሚሹና የሚፈልጉ ሰዎች አስቀድሞ የሚያስነሣው። በግሌ አንድ ክርስቲያን ይህ ራብ በውስጡ ለረጅም ጊዜ ከጠፋ፣ ለመውደቅ እየተንሸራተተ እንደ ሆነ ሊያስብ

ይገባዋል የሚል አመለካከት አለኝ። እኔ ራሴ ይህ ራብ ከውስጤ ሲጠፋ ያለማጋነን እደነግጣለሁ፤ ግራ ይገባኛል። እናም ሁሉን ነገር አቁሜ ወደ ቦታዬ ለመመለስ ብዙ ነገሮች አደርጋለሁ። ከወትሮውም ብዙ እጸልያለሁ፤ ብዙ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ ራሴን አነቃቃለሁ።

በጌታ ቤት በቆየሁበት ዘመን መንፈሳዊ ራብ የሚያስደንቅ ኡደት (positive cycle) እንዳለው ተገንዝቤአለሁ። መንፈሳዊ ራቡ ልባችንን ባሰፋነው መጠን ያድጋል። አብዝተን እንድንቃትት ያደርገናል። አብዝተን ስንጸልይ ደግሞ ጸሎቱ ሌላ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ራብን ይወልዳል። የሚመጣው መንፈሳዊ ራብ ደግሞ አብዝተን እንድንጸልይ ያደርገናል። ወገኖቼ አንዱ አንዱን እየጨመረ ማብቂያ የሌለው አስደናቂ ነገር ውስጥ ነው የምንገባው፤ እኛ በሥጋዊ አካሄዶች መንፈስን እስካላጠፋን ድረስ።

ጌታ ሆይ ከፍ ያለ አንተን የሚሻና የሚፈልግ ልብ ስጠን!

**መዝጊያ ምንባብ**፡- *"አምላኬ፥ አምላኬ፥ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ፤ ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች እንጨትና ውኃ በሌለበት በምድረ በዳ። ኃይልህንና ክብርህን አይ ዘንድ እንዲሁ በመቅደስ ውስጥ ተመለከትሁህ።"* (መዝ.63፥1-2)

# የጸሐፊው ማሳረጊያ

ጌታ ኢየሱስ ሊባርከን፣ ተፈትተን በነጻነት እንድንኖርና፣ ለሌሎች እንድንተርፍ ሊያደርገን እጁን ዘርግቶ ይገኛል። ለዚህ ደግሞ ያጎደለብን ነገር የለም፤ የሚያስፈልገን ሁሉ ተሰጥቶናልና (2ጴጥ.1፥2)። አዎ፣

በሰጪው በኩል ምንም የቀረ ነገር የለም። የጎደለው ነገር በእኛ በኩል እርሱን መፈለግ ነው፤ የጠፋው ነገር ትጋት ነው፤ ያጣነው ነገር መሰጠት ነው፤ የራቀብን ነገር በፊቱ መሆን ነው።

እንደ ልቡ ሐሳብ ልባችንን ወደ እሱ አዘንብለን፣ ብንቀርበው ብዙ መልካም ነገሮች በሕይወታችን ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ። በረከቱ ሰፊ ነውና፣ ሊያስደንቀን በደጅ ነው (ራእ.3፥20)። እንግዲህ የእርሱ በረከት ታገኘን ዘንድ ከእኛ የሚጠበቅ አንድ ኅላፊነት አለ። እሱም ሳያሰልሱ፣ ሳይታክቱና ሳይወላውሉ በፊቱ መሆን ነው።

በእነዚህ በተለያዩ ግን በይዘት አንድ ዓይነት በሆኑ መጣጥፎች፣ ልባችሁ ወደ ጌታ ያዘነብል ዘንድ ጉጉትን፣ ናፍቆትንና ራብን ውስጣችሁ ልቆሰቁስ ተጋሁ። የተሳካልኝ ከሆነ ወደ ፊት ባለ ዘመን ከእናንተ የምሰማው ይሆናል። ግን ምናልባት ከሚሠራ ሰው ጥፋትና ግድፈት አይጠፋምና፣ በቅድሚያ ላገኛችኋቸው ግድፈቶችና የተዛነፉ ሐሳቦች ራሴን ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ እንደማደርግ ይታወቅልኝ። እናም የምትሰጡኝን ትችቶች፣ ገንቢ ሐሳቦችና ተግሣጾች ለመቀበል ዝግጁ መሆኔን እንድታውቁ ለማረጋገጥ እወዳለሁ። ስለሆነም በቅንነትና በትሕትና ሐሳባችሁ እንድታጋሩኝ እጠብቃችኋለሁና፣ በሐሜት ደረጃ ከማብጠልጠል ይልቅ፣ በልባችሁ ያላችሁን ሐሳብና ቅሬታ ደፍራችሁ እንድትነግሩኝ በጌታ ፍቅር እለምናችኋለሁ።

እነዚህን መጣጥፎች ጊዜያችሁን ሰጥታችሁ ስላለነበባችሁ በጌታ በኢየሱስ ስም ተባረኩ!!

በቀለ ብርሃኑ (ዶ/ር)

-----------------

አ፣ እንዴት ታላቅ አምላክ ነው?! ስለ እርሱ ቢነገርና ቢወራ ምንስ መጽሐፍስ ይበቃዋል?! *"የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም። የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"* (ሮሜ.11፥33-36)

# የመዝጊያ ጸሎት

*ጌታ ሆይ እባክህ ዓይኖቻችንን ክፈትልህን። አባት ሆይ ከዚህ ያነሰ ራዕይ እንዳኖረን አንፈልግምና የልባችን ዓይኖች አንተን ያዩ ዘንድ ይብሩ። ያኔ እውነተኛ የሆነ፣ ግብዝነት የሌለበትና ንጹሕ አምልኮን እናቀርብልሃለን፤ ያኔ ቀድመው እንደ ነበሩ አንተን በሕይወታቸው እንዳስከበሩ የእምነት አባቶች በፊትህ በግምባራችን እንደፋለን፤ ያኔ ሁለንተናችን ያንተ ይሆናል።*

*እግዚአብሔር ሆይ ከዳር ዳር፣ ከግርግርና ላይ ላዩን ከሆነ ጸሎት ወደ ጠለቀ ነገር ውስጥ ክተተን። አባት ሆይ ለውጠን፤ በጸሎት ጉልበትህን የምንይዝበትን ጸጋ አብዛልን። እንደ ያዕቆብ "ካልባረክኸኝ አልለቅህም" (ዘፍ.32፥26) የምንልበትን ቅናትና የጋለ ፍላጎት ሙላብን። ያኔ ሙሉ ፈውስን እናገኛለን፤ ያኔ ለብዙዎችም በረከት እንሆናለን።*

*ጌታ ሆይ መንፈስህን እንዳናናሳዛንና እንዳናስመርር፣ ለመንፈስህ ንቁ*

*አድርገን። ጥልቅ የንስሐ ሕይወትን ስጠን። የተሰወሩ በደሎቻችን በፊትህ ብርሃን አሳየን፤ እባክህ ከዓለም በግብር ለየን፤ ቀድሰን። ያኔ አንተን የማየት ዕድል ይኖረናል። አንተን ዐይቶስ የማይለወጥ፣ ክብርህንስ ዐይቶ የማይሰግድልህ ማን ነው?*

*አባት ሆይ ከልማዳዊና ሕይወት ከሌለበት ድግግሞሽ አውጣን። የመንፈስህን ራብ በውስጣችን አብዛው። በናፍቆት ውለን በናፍቆት በምናድርበት፣ ቅዱስ አለመርካት (Holy dissatisfaction) ባርከን። በጉብኝትህ አስደንቀን! ኦ፣ ጌታ ሆይ ክብርህን አሳየን! አሜን!*

# አብሮነቱ

የራቀን ዓይነት ተሰምቶን አሰብነው

ዱካውን ማግኘት ተስኖን ናፈቅነው

ራቡ ጥማቱ ከርሮብን ልንደርስበት አሰስን

እናየው ዘንድ በተማጽኖ ከጓዳችን ቃተትን

ወደ እርሱ ገሠገሥን

ጮኽን--አማጥን

ጊዜ ሰጥተን ደጅ ጠናነው

ያለ እርሱ እንደማይሆን አውቀነው

ለካስ እዚያው ሆኖ በውስጣችን ከእኛው መኻል

ሊፈታታን ሊጎበኘን ከተፍ ብሏል

ይህ የሩቅ ቅርብነቱ (the paradox)

ደግሞም በእራሱ ሰዓት መገኘቱ

እያስደነቀን ይቀጥላል----ጥበቡ አይደረሴነቱ

(His transcendence)

ደግሞም ታናሽ አይንቄነት አብሮነቱ!

---------------------ተፈጸመ----------------------------------